ኢፕድ

# አዲስ ዘመን


ሐሙስ

83ኛ ዓመት ቁጥር 066 ኅዳር 6 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




# ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እና አልቡርሃን በጋራ ጉዳዮች ላይ ውይይት አደረጉ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



አዲስ አበባ፡- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እና የሱዳን ሪፐብሊክ ሉዓላዊ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት አብዱልፈታህ አልቡርሃን የጋራ በሆኑ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ ገንቢ ውይይት አደረጉ።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ለሱዳን ሪፐብሊክ ሉዓላዊ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት አብዱልፈታህ አልቡርሃንና ልዑካን ቡድናቸው ትናንትና ቦሌ አለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ሲደርሱ አቀባበል አድርገውላቸዋል።

ሁለቱ መሪዎች በጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ተገናኝተው የጋራ በሆኑ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ መምከራቸውን የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት መረጃ ያመላክታል፡፡

የሱዳን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርና፣ የዳርፉር አስተዳዳሪ እንዲሁም የአገሪቱ ደኅንነት ኃላፊን የያዘ የልዑካን ቡድን ከ አልቡርሃን ጋር ወደ ኢትዮጵያ መምጣቱ ታውቋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) ከሱዳን የሽግግር መንግሥት ሉዓላዊ ምክር ቤት ሊቀመንበር አብዱልፈታህ አል ቡርሃን ጋር ሰኔ 28 ቀን 2014 ዓ.ም መወያየታቸው የሚታወስ ነው።









ፎቶ - አዮብ ተፈሪ

# "ቀይ ባሕርን ለጋራ ዕድገት ለማዋል በሰጥቶ መቀበል መርሕ መሥራት ያስፈልጋል"

## - አረጋዊ በርሄ (ዶ/ር)

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- ቀይ ባሕርን ለጋራ እድገት ለማዋል በሰጥቶ መቀበል መርሕ ተግባብቶ መሥራት ያስፈልጋል ሲሉ ፖለቲከኛ አረጋዊ በርሄ (ዶ/ር) ገለጹ፡፡

አረጋዊ በርሄ ዶ/ር ለኢፕድ እንደገለጹት፤ የባሕር በር ጥያቄን በሕጋዊና በሰላማዊ መንገድ ማንሳት የጋራ ተጠቃሚ የምንሆንበትን ሁኔታ ይፈጥራል፡፡ በተለይ የባሕር በር በሰጥቶ መቀበል መርሕ ለጋራ ዕድገትና ብልጽግና እንዲውል ተግባብቶ መሥራት ያስፈልጋል፡፡

ሀገሮች አርቀው በማሰብ የቀጠናው ሀገራት ዜጎች እንዲጠቀሙ፣ ከችግርና ከኋላ ቀርነት ለመውጣት የባሕር በርን አብሮ መጠቀም ይገባል ያሉት ዶክተር አረጋዊ፤ የባሕር በር አብሮ ተጠቃሚ የመሆን ጉዳይ በጋራ የማደግ አጀንዳ ነው ብለዋል፡፡

የባሕር በር ጥያቄን በሰላምና በሕግ አግባብ መጠየቅ መብትም፤ አስፈላጊም መሆኑን ጠቅሰው፤ ጥያቄን በሰላማዊና በሕግ አግባብ ማቅረብ ተገቢ መሆኑን

"ቀይ ባሕርን ...ወደ ገጽ 6 ዞሯል

# 56 ሺህ አርሶ አደሮች ከሁለት ቢሊዮን ብር በላይ ብድር ተጠቃሚ ሆነዋል

ገጽ 6

# በሠላም ማስከበር ተልዕኮ የትም ቢዘምት ዲሲፕሊኑ የተረጋገጠ ሠራዊት ተገንብቷል

**አዲሱ ገረመው**



አዲስ አበባ፡- በሠላም ማስከበር ተልዕኮው የትም ቢዘምት ሕዝብ ሲራብና ሲገፋ ማየት የማይፈልግና ዲሲፕሊኑ የተረጋገጠ የመከላከያ ሠራዊት መገንባቱ ተገለጸ፡፡ ጠንካራ የባሕር ኃይል እንዲደራጅ አቅጣጫ ተቀምጧል፡፡

የኢፌዴሪ መከላከያ ሚኒስቴር የ2016 ዓ.ም የመጀመሪያ ሩብ ዓመት እቅድ አፈጻጸምን ትናንት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የውጭ ግንኙነት እና የደህንነት ቋሚ ኮሚቴ አቅርቧል፡፡

በወቅቱ የኢፌዴሪ የሀገር መከላከያ ሚኒስትር አብርሃም በላይ (ዶ/ር)፤ የሠላም ማስከበር ሥራችን ፀጥታን የማረጋገጥ ቢሆንም፤ በሂደቱ ላይ ያለው ስምሪት እንዲደናቀፍ በከፍተኛ ሁኔታ ስም የማጠልሸት ሥራዎች እየተሠሩ እንዳለ ገልጸዋል፡፡ በተለይ ደግሞ ሀገር ውስጥ ባለ ግጭት ምክንያት የሚሰነዘሩ የፈጠራ ውንጀላዎች ሂደታችንን ለማደናቀፍ ያለሙ ናቸው ብለዋል፡፡

በሠላም ማስከበር ...ወደ ገጽ 6 ዞሯል








አቶ ሐሰን ሞሐመድ

## በአምራች ኢንዱስትሪው ከ18 ሺህ 800 በላይ ለሆኑ ዜጎች የሥራ ዕድል ተፈጥሯል

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዳማ፡- በኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ የኢንቨስትመንት ፍሰቱ በመጨመር እና የተዘጉ ኢንዱስትሪዎች ሥራ እንዲጀምሩ በማድረግ ከ18 ሺህ 800 በላይ የሥራ ዕድል መፍጠር መቻሉን የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ገለጸ። 370 የአምራች ኢንዱስትሪዎችን ወደ ሥራ መመለሳቸው ተመልክቷል።

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ሐሰን ሞሐመድ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የ2016 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት አፈፃፀም ትናንት ሲገመግም እንደገለፁት፤ በኢትዮጵያ ታምርት ሀገራዊ ንቅናቄ ሥራ ያቆሙ አምራች ኢንዱስትሪዎችን ወደ ሥራ የመመለስ እና ምርታማነታቸውን የማሳደግ ሥራ ተሠርቷል። የኢንቨስትመንት ፍሰቱ በመጨመር እና የተዘጉ ኢንዱስትሪዎች ሥራ እንዲጀምሩ በማድረግ ከ18 ሺህ 800 በላይ የሥራ ዕድል መፍጠር ተችሏል።

በንቅናቄው 370 በተለያዩ ምክንያቶች ሥራ አቁመው የነበሩ አምራች ኢንዱስትሪዎችን ወደ ሥራ እንዲመለሱ ማድረግ ተችሏል ብለዋል።

በግብዓት፣ በብድር እና በውጭ ምንዛሪ እጥረት እንዲሁም በምርት አቅርቦት እና መሥሪያ ቦታ ችግር በርካታ አምራች ኢንዱስትሪዎች ሥራ አቁመው እንደነበር አውስተው፤ በተጨማሪም ኢንዱስትሪዎቹ በመሠረተ ልማት መጓደል እና በአላስፈላጊ የመንግሥት ቢሮክራሲዎች ሥራ አቋርጠው የነበሩ ናቸው ብለዋል።

የነበሩባቸውን ችግሮች በመፍታት ወደ ሥራ እንዲመለሱ ማድረግ መቻሉን አብራርተዋል።

በኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ ሥራ ያቆሙ ኢንዱስትሪዎች ወደ ሥራ ማስገባት ብቻ ሳይሆን ኢንዱስትሪዎች የማምረት አቅማቸው እንዲሻሻል እየተሠራ መሆኑን የተናገሩት ሚኒስትር ዴኤታው፤ የኢንዱስትሪዎች የማምረት አቅም ከነበረበት 48 በመቶ ወደ 55 ነጥብ 79 በመቶ ማደጉን ገልጸዋል።

በተለያዩ የንቅናቄ መድረኮች አዳዲስ ኢንቨስትመንቶች መሳብ መቻሉን የጠቀሱት ሚኒስትር ዴኤታው፤ የኢንቨስትመንት ፍሰቱ ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር በ200 ጭማሪ አሳይቷል ብለዋል።

በኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ በተኪ ምርቶች ላይ ትኩረት ተሰጥቶ ሲሠራ መቆየቱን ጠቅሰው፤ በተያዘው በጀት ዓመት ሦስት ወራት ውስጥ 94 ሚሊዮን ዶላር መገኘቱን ተናግረዋል።

እንደ አቶ ሐሰን ገለፃ፤ ፈጣን የኢንዱስትሪ ዕድገት ማስመዝገብ የቻሉ ሀገራት ተፅዕኖ ፈጣሪነታቸውን አረጋግጠዋል። ኢትዮጵያም በዘርፉ ትኩረት ሰጥታ በመሥራት ላይ ትገኛለች። ሀገሪቷ ከግብርና ወደ ኢንዱስትሪ መር ለምታደርገው ሽግግር የፖሊሲ ቁርጠኝነት አሳይታለች ።

የአምራች ኢንዱስትሪው የሁሉንም ርብርብ የሚጠይቅ ዘርፍ መሆኑን ጠቅሰው፤ ለዘርፉ ዕድገት ሁሉም የበኩሉን እንዲወጣ ጥሪ አቅርበዋል።

## በመዲናዋ የሚካሄዱ አብዛኞቹ ግንባታዎች ሠራተኞችን ለአደጋ የሚያጋልጡ ናቸው

**ተስፋ ፈሩ**



አዲስ አበባ፡- በመዲናዋ የሚካሄዱ አብዛኞቹ ግንባታዎች የሥራ ላይ ደህንነት መርሆችን የጠበቁ ባለመሆናቸው ሠራተኞችን ለአደጋ የሚያጋልጡ መሆናቸውን የአዲስ አበባ እሳትና አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን አስታወቀ።

የኮሚሽኑ የሕዝብ ግንኙነት ባለሙያ አቶ ንጋቱ ማሞ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ኮሚሽኑ አደጋ ሲደርስ ከሚሰጠው ምላሽ ባሻገር በአደጋ ቅነሳ ሥራ ባደረገው ቅኝት አብዛኞቹ የግንባታ ሥራዎች የሥራ ላይ ደህንነት መርሆችን ጠብቀው የሚሠሩ አለመሆናቸውን ገምግሟል።

በግለሰብም ሆነ በመንግሥት በሚሠሩ የሕንጻና የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶች ተጀምረው እስኪጠናቀቁ ድረስ የበርካታ ባለሙያዎች ሕይወት በሥራ ላይ አደጋ እየጠፋ ነው ያሉት አቶ ንጋቱ፣ "አደጋዎቹ የሚከሰቱት ለጉዳዩ ትኩረት ባለመስጠትና ከዚህ በሚመነጭ ቸልተኝነት ነው" ብለዋል።

አብዛኞቹ በግንባታ ሥራ ላይ የሚሳተፉ ሠራተኞች ኤርጌንዶ የሚባለውን ነጠላ ጫማ፣ የጸሐይ መከላከያ ኮፍያና የራሳቸውን ልብስ ለብሰው ነው ሥራ የሚሠሩት። ርዳታ ለመስጠት አደጋ የደረሰባቸው ቦታዎች ላይ ስንሄድ የምንረዳው በአደጋ ጊዜ የጉዳት መጠንን የሚቀንሱ ሔልሜንት፣ ጫማ፣ ቀበቶ እና መነጽርን የመሰሉ የደህንነት መጠበቂያዎችን የመጠቀም ባሕል አልዳበረም ብለዋል።

እንደ እርሳቸው ገለጻ፣ የሥራ ላይ ደህንነት መርሆች ባለመጠበቃቸው ምክንያት አደጋ መድረስ የሚጀምረው ገና የሕንጻው መሠረት ሲቆፈር ነው። ሠራተኞች ተቆፍሮ የወጣው አፈር ላያቸው ላይ ተደርምሶባቸው ይሞታሉ ከዚያ በኋላ ባሉት የተለያዩ የግንባታ ምዕራፎችም የአካል ጉዳትና ሞት የሚያስከትሉ አደጋዎች ይደርሳሉ።

"እኛ የምንጠራው የሞት አደጋ ሲያጋጥም ነው ወይም ተጎጂዎችን አፈርና ድንጋይ ተጭኗቸው አስከሬናቸውን ማንሳት የማይችሉበት ሁኔታ ሲፈጠር ነው" ያሉት የሕዝብ ግንኙነት ባለሙያው፣ ኮሚሽኑ መዝግቦ የሚይዘው ተጠርቶ አገልግሎት የሰጠበትን አደጋ ብቻ መሆኑን አመልክተዋል።

"ብዙ ጊዜ በተለየም ከሞት አደጋ በመለስ ያለን ጉዳት የግንባታ ሥራ ተቋራጮች ይደብቃሉ። የተጎዱትን ሰዎች አፋፍሰው ወደ ሆስፒታል በመውሰድ ፖሊስም ሆነ እሳትና ድንገተኛ አደጋዎች ጋር መረጃው እንዳይደርስ ያደርጋሉ" ብለዋል።

አደጋ ሲከሰት በግንባታ ሥራ ተቋራጮች ወይም አሠሪዎች ላይ የሚጣለው ቅጣት አነስተኛ መሆኑ ለጉዳዩ ትኩረት እንዳይሰጡት ማድረጉን የገለጹት አቶ ንጋቱ፣ "ከግንባታ ሥራ ተቋራጮች ጋር ለመወያየት መድረኮችን ለመፍጠር ብንሞክርም ስንጠራቸው ሊመጡ አልቻሉም" በማለት ኮሚሽኑ በራሱ በኩል ለአደጋ አጋላጭ የሆኑ ሁኔታዎችን ተመልክቶ ግንባታውን ለሚያከናውነው ድርጅትና ፈቃድ ለሰጠው አካል ምክረ ሀሳብ የማቅረብ ሥራዎችን እየሠራ እንደሚገኝ ተናግረዋል።

በቅርቡ በአዲስ አበባ ኮልፌ በግንባታ ሥራ ላይ የነበሩ ሦስት ሰዎች ሕይወት ማለፉ ይታወሳል።

## ጥምረቱ በአፍሪካ ከሚገነባቸው አንድ ሺህ መንደሮች ትልቁን ድርሻ ለኢትዮጵያ ይሰጣል

**ዳግማዊት አበበ**




አዲስ አበባ ፡- የቻይናው የንግድ ሥራ በአፍሪካ ለማኅበራዊ ኃላፊነቶች ጥምረት በአፍሪካ ሊገነባ ካቀደው አንድ ሺህ ዘመናዊ መንደሮች ትልቁን ድርሻ ለኢትዮጵያ እንደሚሰጥ ቃል መግባቱን የጥምረቱ ሥራ አስፈፃሚ ዲያዮ ቹንሄ ገለጹ ።

በጥምረቱ ሥራ አስፈፃሚ ዲያዮ ቹንሄ የተመራ የልዑካን ቡድን ከሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ከፍተኛ አመራሮች ጋር በትላንትናው እለት መክሯል ።

የቻይና የንግድ ሥራ በአፍሪካ ለማኅበራዊ ኃላፊነቶች ጥምረት ሥራ አስፈፃሚ ዲያዮ ቹንሄ ጂያኦ ቻንሒ እንደገለጹት፤ በአፍሪካ የአንድ ሺህ መንደሮች ግንባታ ፕሮጀክት ይፋ የሆነው በ3ኛው የአፍሪካ ቻይና ሮድ ኤንደ ቤልት ጉባዔ ላይ ነው። ጥምረቱ በ51 የአፍሪካ ሀገራት ሊገነባ ካቀዳቸው አንድ ሺህ መንደሮችም ትልቁን ድርሻ ለኢትዮጵያ ይሰጣል።

የመንደሮች ግንባታ ፕሮጀክትም በኢትዮጵያና ቻይና የግንኙነት እድገት ማሳያ ነው ያሉት ሥራ አስፈፃሚው፤ ለፕሮጀክቱ መሳካት የኢትዮጵያ መንግሥት አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲያደርግ ጠይቀዋል።

ፕሮጀክቱ የሥራ እድልን በመፍጠር ማኅበራዊ ኃላፊነትን በመወጣት እና በቀጣይ ትውልድ ተስፋ ላይ ከፍተኛ አስተዋፅዖ ይኖረዋል ሲሉም ገልጸዋል ።

ፕሮጀክቱን ስንተገብር ከሴቶች እና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ይሆናልም ያሉት ሥራ አስፈጻሚው፤ የመኖሪያ መንደሮች ሲገነቡ ለኑሮ የሚያስፈልጉ ሁሉም ነገሮችን ባካተተ መልኩ መሆኑን ተናግረዋል ።

የቻይና የንግድ ሥራ በአፍሪካ ለማኅበራዊ ኃላፊነቶች ጥምረት በአፍሪካ ውስጥ በኢንቨስትመንት እንዲሁም በኢኮኖሚ እና ንግድ ትብብር ላይ በተሰማሩ የቻይና ኢንተርፕራይዞች በፈቃደኝነት የተቋቋመ መሆኑን ገልጸው፤ በአፍሪካ ውስጥ ለማኅበራዊ ሕይወት መሻሻል ያግዛሉ ያላቸውን አንድ ሺህ መንደሮችን ለመገንባት እየሠራ መሆኑን አመልክተዋል ።

የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታ ሁሪያ አሊ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ የቻይና መንግሥት እና ኢንተርፕራይዞች ኢትዮጵያ የሴቶችና እና ሕፃናት እንዲሁም የአጠቃላይ ማኅበረሰቡን ሕይወት ለማሻሻል የምታደርገውን ጥረት በመደገፍ እያበረከቱ ያለው አስተዋፅዖ ከፍተኛ ነው። ለዚህም ምስጋና ይገባቸዋል ።

ወይዘሮ ሁሪያ ፤ ቻይና እና ኢትዮጵያ ሁሉን አቀፍ ግንኙነት እንዳላቸው ገልጸው፤ ግንኙነታቸው በማኅበራዊ፣ በምጣኔ ሀብት እና ንግድ ላይ ያተኮረ መሆኑን ጠቅሰዋል። ይህ ትስስር አድጎ የቻይና ኩባንያዎች ማኅበራዊ ኃላፊነታቸውን መወጣት በሚችሉበት ደረጃ ላይ ደርሷል ብለዋል ።

ዜና

# የኢትዮጵያ አየር መንገድ በአፍሪካ ታሪክ የመጀመሪያውን የቦይንግ አውሮፕላኖች የግዢ ስምምነት አደረገ

**ሞገስ ጸጋዬ**




አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ አየር መንገድ በአፍሪካ የአቪዬሽን ታሪክ ትልቁና የመጀመሪያ የሆነውን 67 ቦይንግ ጀት አውሮፕላኖች ለመግዛት ከቦይንግ ኩባንያ ጋር ስምምነት መፈራረሙን አስታውቋል።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በላከው መግለጫ እንዳስታወቀው፤ 11 አዲስ 787 ድሪምላይነርና 20 አዳዲስ 738 ማክስ አውሮፕላኖችን ከቦይንግ ኩባንያ ለማዘዝ ከቦይንግ ኩባንያ ጋር ስምምነት በዱባይ ተፈራርመዋል። እንዲሁም ተጨማሪ 15 ድሪምላይነሮችንና 21 ተጨማሪ ማክስ አውሮፕላኖችን የማዘዝ ዕድል ሊኖረው እንደሚችል በላከው መግለጫ ገልጸዋል።

በዱባይ ዓለም አቀፉ የአየር ትርኢት ላይ የተፈረመው ስምምነት በአየር መንገዱ ታሪክ ትልቁ ግዢ የተፈጸመበት መሆኑን መግለጫው ጠቁሟል። ይህም በአፍሪካ ታሪክ ትልቁንና የመጀመሪያው የቦይንግ አውሮፕላኖች ግዢ መሆኑ ተጠቁሟል።

የአውሮፕላኖች ትዕዛዝ የኢትዮጵያ አየር መንገድን ለማሳደግና ለማዘመን የተያዘውን የ2035 ስትራቴጂ ዕቅድ ራዕይ እውን ለማድረግ ያስችላል። እንዲሁም ከቦይንግ ኩባንያ ጋር የቆየውን ግንኙነት ይበልጥ እንደሚያጠናክር ጠቁሟል።

ድሪምላይነርና ማክስ አውሮፕላኖች ዘመናዊ፣ ነዳጅ ቆጣቢና የካርበን ልቀታቸው ከ20 እስከ 25 በመቶ የሚቀንስ መሆኑን መግለጫው አመልክቶ፤ አዲሱ ስምምነት የኢትዮጵያ አየር መንገድን የበለጠ ለማጠናከር፣ ለማስፋፋትና የደንበኞቹን ምቾት ለመጠበቅ ያስችላል። በአፍሪካ ቀዳሚነቱን አጠናክሮ ለማስቀጠል ያስችለዋል። በነባር አውሮፕላኖች ላይም አዳዲስ ማሻሻያዎችን ለማድረግም መስማማቱን ገልጿል።

# የሲዳማ ባንክ ከሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አገልግሎት ጋር በጋራ ለመሥራት ተስማሙ

## - ስምምነቱ ለባንኩ የሚቀርቡ ሰነዶች ትክክለኛ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ያግዛል

**መስከረም ሰይፉ**



አዲስ አበባ፡- የሲዳማ ባንክ ከፌደራል የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አገልግሎት ጋር በጋራ ለመሥራት የሚያስችላቸውን የመግባቢያ ሰነድ ተፈራረሙ። ስምምነቱ ለባንኩ የሚቀርቡ ሰነዶች ትክክለኛ መሆናቸውን ለማረጋገጥ እንደሚያስችል ተገልጿል።

ሲዳማ ባንክ ከፌደራል የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አገልግሎት ጋር በጋራ ለመሥራት የሚያስችል የመግባቢያ ሰነድ በትላንትናው እለት ተፈራርሟል።

የፌደራል ሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር ዳንጋቶ ኩንቤ እንደገለጹት፤ አገልግሎቱ ሰነዶችን የማረጋገጥና የተረጋገጡ ሰነዶች በመመዝገብ የዜጎችን መብት ያረጋግጣል። ከሲዳማ ባንክ ጋር የተደረገው ስምምነትም ለብድርም ሆነ ለሌሎች አገልግሎቶች ወደ ባንኩ የሚመጡ ሰነዶች በሕጋዊ መንገድ የተመዘገቡ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ያስችላል።

በተለይ ባንኩ አገልግሎቱ ወደ አዘጋጀው የመረጃ ሥርዓት (ሲስተም) በመግባት ከደንበኞቹ የቀረበለትን ሰነድ ትክክለኛ ስለመሆኑ ማረጋገጥ የሚያስችለው መሆኑ ተናግረዋል።

ከዚህ ቀደም ባንኩ ሰነዶችን ለማረጋገጥ ሲፈልግ ባለሙያዎችን በመላክ ያረጋግጥ እንደነበር አስታውሰው፤ ይህም ጊዜን የሚፈጅና ለከፍተኛ ወጪ የሚዳርግ መሆኑን ተናግረዋል። የተደረገው ስምምነትም ይህንን ችግር እንደሚቀርፍ አብራርተዋል።

አቶ ዳንጋቶ የፋይናንስ ተቋማት ለሐሰተኛ ሰነዶች ተጋላጭ በመሆናቸውም በአገልግሎት ሲስተናገዱ በቅድሚያ መረጃ የሚያገኙበት አግባብ መኖሩን ገልጸው፤ በአሁኑ ጊዜም የፌደራል ሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አገልግሎት ከ28 ባንኮች ጋር በጋራ እየሠራ መሆኑ አስታውቀዋል።

ሰነዶች በሐሰተኛ መንገድ በማሠራት ባለ መብት ያልሆነ ሰው ባልተገባ መንገድ ባለ መብት በመምሰል የዜጎች መብት የሚጎዳ ተግባር ይፈጸማል ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ይህንን ለመከላከልም በአገልግሎቱ የተመዘገቡ ሰነዶችን የሚጠቀሙ መሥሪያ ቤቶች በሲስተም በማስተሳሰር በቴክኖሎጂ የተረጋገጠ ሰነድ እንዲቀባበሉ እንደሚደረግ ዳይሬክተሩ ገልጸዋል።

የሲዳማ ባንክ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ታደሰ ሀጢያ በበኩላቸው ስምምነቱ ትልቅ ፋይዳ እንዳለው ገልጸው፤ መረጃዎችን በሲስተም መለዋወጥ የሚያስችል በመሆኑ ጊዜ ቆጣቢና ሕጋዊ የገንዘብ ልውውጥ ለመፈጸም የሚያግዝ ነው ብለዋል።

ባንኩ በሚሰጣቸው የብድር፣ የቁጠባና ሌሎች አገልግሎቶች በብዛት በውክልና የሚሠራ እንደመሆኑ እነዚህ ውክልናዎች እውነተኛ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ይደረግ የነበረውን አድካሚ መንገድም የሚያሳጥር ነው ብለዋል።

አቶ ታደሰ ስምምነቱ ሕጋዊ ያልሆነ ሰነድን ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብንና በትውውቅ የሚሠራ ስርቆትን ለመከላከልና ለመቆጣጠርም ከፍተኛ ሚና እንደሚኖረው ጠቅሰዋል።

ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

# የተለያዩ ተቋማት

## የሥራ ኃላፊዎች ሀብትና የገቢ ምንጫቸውን እንዲያስመዘግቡ እየተደረገ ነው

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- የዘንድሮው የፀረ-ሙስና ቀንን ምክንያት በማድረግ የተለያዩ ተቋማት ሥራ ኃላፊዎች ሀብትና የገቢ ምንጫቸውን እንዲያስመዘግቡ እየተደረገ መሆኑን የፌዴራል የሥነ-ምግባርና የጸረ-ሙስና ኮሚሽን አስታወቀ።

20ኛው የዓለም የፀረ-ሙስና ቀን ከኅዳር 1 እስከ 25 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ "ሙስና የጋራ ጠላታችን ነው፣ በኅብረት እንታገል" በሚል መሪ ሀሳብ በኢትዮጵያ በመከበር ላይ ይገኛል፡፡

የሥነ ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የጥቅም ግጭት መከላከል መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ መስፍን በላይነህ ትናንትና በሰጡት መግለጫ እንዳመለከቱት፤ 20ኛው የዓለም የፀረ-ሙስና ቀን ሲከበር የተለያዩ ተቋማት አመራሮችና የሥራ ኃላፊዎች ሀብትና የገቢ ምንጫቸውን እንዲያስመዘግቡና ግልጽነትና ተጠያቂነትን እንዲረጋገጥ እየተሠራ ነው።

የፀረ-ሙስና ቀን የሚከበርባቸው ኩነቶች በተጨማሪ የተቋማት አመራሮችና የሥራ ኃላፊዎች ሀብትና የገቢ ምንጫቸውን በማሳወቅና በማስመዝገብ ያከብሩታል ያሉት አቶ መስፍን በተለይም ሕገ መንግሥታዊ መርሕ ለሆነው ግልጽነትና ተጠያቂነት አሠራር መስፈን አርዓያነታቸውን የሚያረጋግጡበት ይሆናል ብለዋል፡፡

ሙስና ግለሰብን፣ ቤተሰብን፣ ተቋማትንና የሀገርን ሕልውና አደጋ ላይ የሚጥል ወንጀል በመሆኑ አደገኛ ጠላታችን ነው ያሉት መሪ ሥራ አስፈጻሚው፤ ኢትዮጵያም የሙስና ገፈት ቀማሽ ሀገር በመሆኗ ችግሩን ለመከላከል ሰፊ ጥረት ያስፈልጋል ሲሉ ተናግረዋል።

የሙስናን አስከፊ ገጽታ በመረዳትና በፀረ-ሙስና ትግሉ ቁርጠኛ መሆን እንደሚገባ ጠቁመው፤ ግለሰቦች፣ ተቋማት፣ አመራሮችና የተለያዩ የሕዝብ አደረጃጀቶች ሙስናን በመታገል ቀኑን ሊያከብሩ እንደሚገባ ገልጸዋል፡

ኢትዮጵያ የፀረ-ሙስና ትግሉን ተቋማዊ ቅርጽ እንዲኖረው በማድረግ መምራት ከጀመረች ሁለት አስርት ዓመታት ማስቆጠሯን በመጠቆም፤ መንግሥት ሙስናን ለመከላከል የሕግ ማሻሻያ ሥራዎችን፣ የሥነ ምግባር መከታተያዎች ጨምሮ፣ በሙስና መከላከልና በሕግ ማስከበር ዙሪያ አዎንታዊ ርምጃዎችን በመውሰድ ላይ መሆኑን አመላክተዋል፡፡

ሙስና የሀገሪቱን የሰላም፣ የልማትና የመልካም አስተዳደር እንቅስቃሴ እንቅፋት መሆኑን ይታወቃል ያሉት አቶ መስፍን፤ በተለይም በፕሮጀክቶች፣ የግዢ ሂደቶች፣ የመሬትና የማዕድን ሀብት፣ በውጪ ምንዛሪ ዝውውርና ግብይትና በመሳሰሉት አገልግሎቶች ላይ ከፍተኛ ብልሹ አሠራሮች እንደሚስተዋሉ ተናግረዋል።

በከፍተኛ ደረጃ የሚስተዋለውን የብልሹ አሠራርና የሙስና እንቅስቃሴን በጋራ መግታት ካልተቻለ በሕዝብና በመንግሥት መካከል መተማመንን እንደሚቀንስ የገለጹት አቶ መስፍን፤ የታማኝ ግብር ከፋዮችን ተነሳሽነትና የአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ታማኝነት በመቀነስ ችግሩን እንደሚያባብስ አስረድተዋል።

ሙስናን በአግባቡ መዋጋት ካልተቻለ የዜጎች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች እንዲሸረሸር በማድረግ ድህነትን ለመቅረፍ የሚደረገውን ርብርብ ያጓትታል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

እየረቀቀና እየተስፋፋ የመጣውን ሙስናን የመከላከል ሥራ ዋነኛው አጀንዳና የሀገሪቱ የሕልውና ጉዳይ መሆኑን ጠቁመው፤ ወቅቱ የሚጠይቀውን የፀረ-ሙስና ትግል የጋራ ማካሄድ አስፈላጊ ነው ብለዋል፡፡

ሙስና በዘላቂነት ለመከላከል በቤተሰብ ደረጃ፣ በትምህርት ተቋማት፣ በሚዲያዎች፣ በሃይማኖት ተቋማት፣ በሲቪክ ማኅበራት፣ በፌዴራልና በክልል አስተዳደሮችና ሌሎች ጉዳይ በሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ዘንድ ጠንካራ ሥራ ማከናወን እንደሚያስፈልግ አፅንዖት ሰጥተዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ጊዜው የሚሻው ለሰላም መሥራትንና አብሮ መቆምን ነው!

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሰላም ወዳድ ሕዝብ ነው፡፡ ለዘመናት አብሮ ተከባብሮ በመኖርና የሰላም ተምሳሌት በመሆን በአርአያነት ሲጠቀስ የኖረ ነው፡፡ ከኢትዮጵያውያን ዘመን ተሻጋሪ አኩሪ መገለጫዎች መካከል የብሔር፣ የእምነት፣ የቋንቋ፣ የባሕልና ሌሎች ልዩነቶችን ዕውቅና በመስጠት ተሳስቦና ተከባብሮ የመኖር ትልቅ እሴት ነው፡፡

ሆኖም የዚህን ኩሩና ሰላም ወዳድ ሕዝብ አኩሪ ዕሴቶች ለማምከን የተለያዩ ሴራዎች በውስጥና በውጭ ሲሰሩ ቆይተዋል፡፡ ሕዝቡ የመከባበርና የመቻቻል እሴቱን እንዲያጣ በብሄርና በሃይማኖት በመከፋፈልና በማናቆር ግጭት እንዲነግስና በሂደትም የተዳከመች ኢትዮጵያ እንድትፈጠር በርካታ አካላት ያለመታከት ሰርተዋል፡፡ በዚህም የኢትዮጵያን የሰላም ዕሴት ደብዝዞ ነፍጥ ማንሳት እንደፋሽን ሲቆጠር ታይቷል፡፡

ይህንን አስተሳሰብ ከመሰረቱ ለመንቀልና ኢትዮጵያን ወደ ቀድሞው ዕሴቶቻቸው እንዲመለሱ ለማድረግ ባለፉት አምስት ዓመታት በፍቅር እንደመር፤ በይቅርታ እንሻገር የሚል መርህን በማንገብ በመላ ሀገሪቱ ሰላምን የማስፈን እንቅስቃሴ ሲደረግ ቆይቷል፡፡ በእስር ላይ የነበሩ የፖለቲካ እስረኞችን በመፍታት፤ በፖለቲካ አመለካከታቸው ምክንያት ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገቡ ታግደው የነበሩ የፖለቲካ ፓርቲ አመራሮችን ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ በማድረግ፤ የታጠቁ አካላት ነፍጣቸውን እንዲያስቀምጡና በሀገራቸው ልማት ላይ በነጻነት እንዲሳተፉ ጥሪ በማድረግ ሰላሟ የተረጋገጠ ኢትዮጵያን ዕውን ለማድረግ በርካታ ሥራዎች ተሰርተዋል፡፡

ሆኖም መንግስት ባደረገው የሰላም ጥሪ እና ለሰላም ባለው ምኞት ልክ የተለያዩ አካላት ተገቢ ምላሽ ሲሰጡ አልታዩም፡፡ ይልቁንም አንዳንዶች መንግስት ለሰላም ያለውን ቀናኢነት በማጣጣልና እንደ ደካማነትም በመቁጠር በየጫካው ጦር ሲመዙ ታይተዋል፡፡ ሰላምንም ወደ ጎን በመተው ግጭትና ሁከትን አንግሰዋል፤ ጦርነትም በማወጅ ለበርካታ ዜጎች ዕልቂት ምክንያት ሆነዋል፡፡

በየጫካና በየዱሩም ነፍጥ በሚያነሱ ቡድኖች ምክንያትም አርሶ አደሩ ተረጋግቶ የእርሻ ሥራውን እንዳያከናውን፤ ገበሬው ነግዶ እንዳያተርፍ፤ ተማሪው በዕውቀት ገበታ ላይ እንዳይገኝ፤ ሰዎች ከአንዱ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ተንቀሳቅሰው እንዳይሰሩ ተደርገዋል፡፡ አልፎ ተርፎም ነፍጥ ባነሱ ቡድኖች አማካኝነት በርካታ ዜጎች ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለዋል፤ ተሰደዋል፤ አካል ጉዳተኛ ሆነዋል፤ ሕይወታቸውንም አጥተዋል፡፡

ይህ ፍላጎትን በጠመንጃ ብቻ የማሳካት ምኞት አንድ ቦታ ሊገታ ይገባዋል፡፡ ለውጥ ተፈጥሯዊ ነው፡፡ ከጊዜና ከሁኔታ ጋር ነገሮች መለወጣቸው አንዱ የተፈጥሮ ግዴታ ነው፡፡ አንድ ቦታ የሚቆም ነገር የለም፡፡ ትላንት ትክክል ይመስል የነበረው ነገር ዛሬ ዋጋ ቢስ ይሆናል፡፡ ትላንት ለአሸናፊነት ያበቃው የትግል ስልትም ለዛሬው የሽንፈት ምንጭም ሊሆን ይችላል፡፡

ትላንት ስልጣን መቆናጠጥ የሚቻለው በብረት ነበር፡፡ በሕቡዕ መደራጀት፤ ማድባትና ማሴር ብሎም መግደልና መጠፋፋት የ1960ዎቹ የስልጣን መወጣጫ ብቸኛ መንገድ ነበር፡፡ አንዳንድ ጊዜም ተማሪዎችን አሳምጾ፤ ወጣቶችን አሸፍቶ፤ ዋሽቶና ለፍፎ ወደ ስልጣን ለመቃረብ የሚደረጉ በርካታ ሙከራዎች ነበሩ፡፡ ይሁንና አሁን ላይ ሁኔታዎች ተቀይረዋል፡፡

በኋላ ቀሩ የፖለቲካ ባሕል ውስጥ የሃሳብ ልዩነት ክብር የለውም፣ ዕውቅናም አይሰጠውም። በሐሳብ የተለየን እንደ ደመኛ ጠላት ማሳደድ፣ ማሰር፣ መግደል ወይም ማሰናከል የተለመደ ድርጊት ነበር፡፡ ነፍጥ አንስቶ ጫካ ገብቶ መንግስት መሆንም የሚያዋጣና በቀላሉም ተግባራዊ ማድረግ የሚቻል ነበር፡፡

ዛሬ ስልጣን ለመያዝ ብረት ማንሳት አያስፈልግም፡፡ ብረት አንስቶ ጫካ ቢገባም ትርፉ ሕይወትን መገበር፤ ወጣቶችን ማስጨረስና ሀገርን ማዳከም እንጂ ስልጣን በጠመንጃ የሚያዝበት ምንም አይነት መንገድ የለም፡፡ እሱ ከዘመኑ ጋር አብሮ አልፏል፡፡

ዛሬ ስልጣን ለመጨበጥ የሚስፈልገው የተሻለ ሃሳብ አምጥቶ ዕውቀትን ለገበያ ማቅረብ ብቻ ነው፡፡ በጠረጴዛ ዙርያ ቁጭ ብሎ በመመካከርና በሃሳብ የበላይነት በማሸነፍ ያለሙትን ማሳካት ይቻላል፡፡ በጠመንጃ ከማሸነፍ በሃሳብ የበላይነት ማሸነፍ ዛሬ ግዝፍ ነስቷል፡፡

ኋላቀር አስተሳሰብ ያለውንና አሁንም ስልጣንን በጠመንጃ ብቻ አሳካላሁ የሚለውን ወገን የሚቀበል እና ጦረኛ አስተሳሰብን የሚሸከም ጫንቃ፣ ሕዝብና ሀገር የለም፡፡ ፍላጎትን በሰላም ብቻ ለማሳካት ከመሞከር ውጪ አዋጭ ነገር እንደሌለ ሁሉም ተረድቶ ለሰላም በጋራ መቆም ጊዜው የሚሻው ሃሳብ መሆኑን መረዳት ይገባል!


## አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ብልጥ ከሌሎች ይማራል ሞኝ ከራሱም አይማር

ከጋዜጣው ሪፖርተር

በሰላም ሥራውን እየሰራ የሚገኝ ዶክተር በሚሰራበት ሐኪም ቤት ለሕክምና እርዳታ የመጣችው ሴት ልጁ ከአትንኩኝ ውጭ ብዙም አትጠይቅም፡፡ ሚስቱ የራሷን ጉዳት ረስታ “ልጄ የሱፍን አግኘው” ስትል ወንድ ልጁም የራሱም ሕመም ዋጥ አድርጎ “ወንድሜን አግኝልኝ” የሚል ጥያቄ ያነሳል፡፡ ይሄን ሊመልስ በሆስፒታል ከሚገኙ ሕሙማን መሀል ያለመታከት ልጁን የፈለገው ዶክተር ልጁን ማግኘት አልቻለም፡፡

የማይቀር ግዴታ ሆኖበት ልጁን ከሬሳ ማቆያ ክፍል ቢፈልገው የስድስት ዓመት ሕጻን ልጁ እንደሌሎቹ ልጆቹ አባቱን ላይጠይቅ በዛ ክፍል ተኝቷል፡፡ ይህ ጽሁፍ ልብወለድ ድርሰት ቢመስልም በጋዛ በአንድ ፍልስጤማውያን ቤተሰብ የደረሰ እውነታ ነው፡፡ የእዚህ እውነታ ምክንያትን እስራኤል ብትጠየቅ ሽብርተኛ ብላ የፈረጀችው ሀማስ ያመጣው ጣጣ ነው፡፡ ፍልስጤማውያን ቢጠየቁ እስራኤል ያደረሰችባቸው ጥቃት ነው፡፡

ይህ የእስራኤልና የሀማስ ጦርነት ውጤት ሳይሆን አጠቃላይ የጦርነት ውጤት ነው፡፡ ጦርነት የትም ቢደረግ አንደኛው ወገን ቢያይል ሟቾቹና ተጎጅዎቹ ቁጥራቸው ይለያይ ይሆናል እንጂ ሟች የማይኖርበት ወገን የለም፡፡ በሀገራችንም የሰሜኑ ጦርነት የሆነው ይሄ ነው፡፡ በርካቶች የተጎዳው ወገኔን ላገልግል ብለው ደፋ ቀና በሚሉበት ቦታ የተጎዳ ወገናቸውን አግኝተዋል፡፡

ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም የሀገራችን ጨለማ ቀን ቢባል ማገነን አይደለም፡፡ ሳይታሰብ በሰሜን ዕዝ ላይ በሕወሓት ቡድን በተከፈተ ድንገተኛ ጥቃት በርካታ የመከላከያ አባላት ላይመለሱ አሸልበዋል። ክስተቱን ተከትሎ በቀጠለው ግጭት በርካቶች ውድ ሕይወታቸውን እና አካላቸውን አጥተዋል፡፡

በትግራይ ከሁለት ዓመታት በፊት የተፈጠረው ሁኔታ ወደ ጦርነት ከማምራቱ በፊት መንግሥት የሰላም አማራጮችን ሁሉ ሞክሯል፡፡ የሀገር ሽማግሌዎችና የሃይማኖት አባቶች ሞክረዋል። እናቶች እያለቀሱ ለምነዋል፡፡ መንግሥት ለውይይትና ለፖለቲካዊ ንግግር ቅድሚያ በመስጠት ከልክ በላይ ትችቶችን አስተናግዷል፡፡

ሁለት ዓመት በቆየው ጦርነት “የሞተው ወንድምሽ የገደለው ባልሽ ሐዘንሽ ቅጥ አጣ ከቤትሽ አልወጣ” የሚለው ሀገራዊ እንጉርጉሮ በተግባር ታይቷል፡፡ የአንድ ቤተሰብ አባላት ጎራ ለይተው እርስ በእርስ ተገዳድለዋል፡፡ ገደልኩ ብሎ ለመፎከር የማይመች፤ ጠላት ተብሎ የማይጨከንበት ሁኔታ ውስጥ እንደ ሀገር ለሁለት ዓመት ተዘፍቀን ቆይተናል፡፡

በዚህም በርካቶች ደረሰልኝ ያሉት ልጃቸውን አጥተው በሀዘንም በደጋፊ ማጣትም ተጎድተዋል። በርካቶች የቤተሰባቸው እጣ ፋንታ ባለማወቅ እንዴ ይመጣ/ትመጣ ይሆን? በሚል ተስፋ ሲያደርጉ፤ ሌላ ጊዜ ሞቶ/ሞታ ይሆን በሚል ተስፋ መቁረጥ ሲዋልሉ ሰንብተዋል፡፡

መንግስት ጦርነቱ በሰላም ስምምነት ቢቋጭ ሀገርን አትራፊ የሚያደርግ መሆኑን ስለአመነበት የፕሪቶሪያው የሰላም ስምምነት እንዲፈረም አድርጓል፡፡ ጥቅምት 23 ቀን 2015 ዓ.ም በደቡብ አፍሪካ ጆሀንስበርግ በኢትዮጵያ መንግስትና በሕወሓት መካከል የተፈረመው የሰላም ስምምነት እነሆ አንድ ዓመት አስቆጥሯል፡፡ በዚህ ስምምነት የጠፋውን መመለስ ባይቻልም እንኳ የጦር መሳሪያ ድምጽ የማይሰማበት አካባቢ መፍጠር መቻሉ ትልቅ ስኬት ነው፡፡

ባለፈው አንድ ዓመት የፌዴራል መንግሥት የፕሪቶሪያውን ስምምነት በተመለከተ ከሚጠበቅበት በላይ በሆደ ሰፊነትና ቁስሉ እንዲሽር ካለው ፍላጎት ለሰላም ያለውን ጽኑ አቋም ደጋግሞ አሳይቷል፡፡ በትግራይ ክልል የተለያዩ የመሰረተልማት ዝርጋታዎችን የቴሌኮሙኒኬሽን፣ የባንክና የአውሮፕላን አገልግሎቶች በፍጥነት እንዲጀምሩ፣ ዩኒቨርሲቲዎችንና ትምህርት ቤቶችን ወደ አገልግሎት ለመመለስ የተለያዩ ተግባራትን ፈፅሟል፡፡ ከፌዴራል መንግሥቱም አልፎ ክልሎች ከአነስተኛ በጀታቸውና ገቢያቸው በመቀነስ የትግራይ ክልልን ደግፈዋል፡፡

**መንግሥት ከሁሉም በላይ በሀገሪቱ ሰላም እንዲሰፍንና የዜጎች ደህንነት እንዲጠበቅ ከማድረግ አኳያ ካለበት ኃላፊነት አንጻር ችግሮችን በሆደ ሰፊነት በድርድር ለመፍታት የሚሄድበት መንገድም ሲደነቅ፤ እውቅና ሊሰጠው የሚገባ ነው**

የስምምነቱን አንድ ዓመት ተከትሎ ከሰሞኑ የመንግስት ባወጣው መግለጫም፣ መንግስት ለሰላም ባለው ፅኑ ፍላጎት ብዙ ርቀትን ቢጓዝም በዚያኛው ወገን እግር የመጎተት አዝማሚያ ይታያል፡፡ ይህም ሆኖ ግን የፌደራል መንግስቱ ለክልሉ የሚደረገውን ሁለንተናዊ ድጋፍ አላቋረጠም፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ የሰላም ፍላጎት ፅኑ ነው፡፡ መንግስትም በአፈ ሙዝ የሚደረግ ትግል ያልተገባ ዋጋ ከማስከፈል የዘለለ ፋይዳ እንደሌለው ጠንቅቆ ይረዳል፡፡ የሰላም አማራጭ ማስቀደምና ወደ ጠረጴዛ የማምጣት ፍላቱን በቀጣይም አጠናክሮ እንደሚቀጥል የሚያጠራጥር አይደለም፡፡

መንግሥት ከሁሉም በላይ በሀገሪቱ ሰላም እንዲሰፍንና የዜጎች ደህንነት እንዲጠበቅ ከማድረግ አኳያ ካለበት ኃላፊነት አንጻር ችግሮችን በሆደ ሰፊነት በድርድር ለመፍታት የሚሄድበት መንገድም ሊደነቅ፤ እውቅና ሊሰጠው የሚገባ ነው። የጠረጴዛ ዙሪያ የሰላም ውይይት የሰላምን ዋጋ ለሚረዳ፣ እርስ በእርስ መገዳደል ለሰለቸው፣ የዜጎች ሰቀቀን ለሚሰማው ሁሉ ልብን በደስታ የሚሞላ፣ 'ጮቤ' የሚያስረግጥ ነው።

የሰላም ውይይት ንፁሃን ዜጎች እየከፈሉት ያለውን ያልተገባ ዋጋ ስቃይ፣ ጥፋት በፍጥነት ለማስቆም አቅሙ ግዙፍ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ አሁን ካለበት አለመረጋጋት ወጥቶ እፎይ እንዲል ትልቅ አቅም ነው። ለዚህ ደግሞ ሁሉም ወገን መትጋት አለበት፡፡ ማንኛውም ጥያቄ አለኝ የሚል አካል ምላሽን በጠመንጃ ለማግኘት ከመሽቀዳደም ይልቅ የሰላምን አማራጭ ስለመኖሩ ጠንቅቆ መረዳት ይኖርበታል፡፡

በሌላ በኩል በአንድ ክልል ሰላም አለመስፈን በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የሁሉንም ክልሎች ሰላም ያናጋል። ስለዚህ ኅብረተሰቡ የጦርነቶች ዋነኛ ገፈት ቀማሽ እራሱ መሆኑን ከትናንት የጦርነት ታሪኮች በመማር የጦርነት ነጋሪት ጎሳሚዎችን በቃችሁ ሊል፤ ለሰላም ዘብ መቆምና ጦርነትን ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ ማውገዝ ይጠበቅበታል።

ከሌሎች መማሩ ቢቀርብን ከራሳችን እንማር፤ ግጭቶችን ለመፍታት ትልቅ ጦርነት እስኪሆኑ፤ በርካቶች እስኪሞቱ በርካታ ንጹሃን ቀያቸውን ለቀው እስኪሰደዱ አንጠብቅ፡፡ የአንድ ሰው ሕይወት ዋጋ አላትና በተቻለ አቅም ችግሮችን ከሥር ለመፍታት እንጣር፡፡ በትላንት ትርክቶች ዛሬ ግጭቶች እንደሚፈጠሩት፤ ዛሬ በኛ ትውልድ በሚፈጠር አምባጓሮ ለነገ ትውልድ ግጭት መንስኤ ላለመሆን ግጭቶቻችንን በጊዜው መፍታት እንጀምር፡፡




# ብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር ከ329 ሚሊዮን ብር በላይ ገቢ አገኘ

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- በ2016 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ከሎተሪ ሽያጭና ዕድል ጨዋታዎች 329 ነጥብ 8 ሚሊዮን ብር ገቢ ማግኘቱን የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር አስታወቀ፡፡ በበጀት ዓመቱ ሁለት ቢሊዮን ብር ገቢ ለማግኘት ማቀዱንም ገልጿል፡፡

የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር የሕዝብ ግንኙነት ዳይሬክተር አቶ ቴዎድሮስ ነዋይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ አስተዳደሩ በ2016 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ከሎተሪ ሽያጭና ዕድል ጨዋታዎች 329 ነጥብ 8 ሚሊዮን ብር ገቢ አግኝቷል፡፡ ገቢው የእቅዱን 85 ነጥብ 67 በመቶ የሚሸፍን ሲሆን፣ ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር የ59 በመቶ ብልጫ አሳይቷል ፡፡

ከተገኘው አጠቃላይ ገቢ ውስጥ 247 ነጥብ 3 ሚሊዮኑ የተጣራ ትርፍ መሆኑን ያመላከቱት ዳይሬክተሩ፤ ይህም ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር የ111 ሚሊዮን ብር ወይም የ55 በመቶ ብልጫ አለው ብለዋል፡፡

በ2016 በጀት ዓመት ሁለት ቢሊዮን ብር ገቢ ለመሰብሰብ አቅዶ ወደ ሥራ መግባቱን አስታውሰው፤ በመጀመሪያው ሩብ ዓመት የተገኘው ውጤት ዓመታዊ ዕቅዱን ለማሳካት በሚችልበት ቁመና ላይ መሆኑን የሚያሳይ መሆኑን ጨምረው ገልጸዋል፡፡

አስተዳደሩ የሚያገኘው አጠቃላይ ገቢና ትርፍ ከዓመት ዓመት እየጨመረ መምጣቱን የጠቀሱት አቶ ቴዎድሮስ፤ የከተሞች መስፋፋት፣ ሕዝቡ ተቋሙ ላይ ያለው አመኔታ ከፍተኛ መሆንና የመግዛት ፍላጎት እያደገ መምጣት እንዲሁም አስተዳደሩ የሚያከናውናቸው የቅስቀሳ ሥራዎች ለውጤቱ መገኘት በምክንያትነት አንስተዋል፡፡

ዕጣዎች ከወጡ በኋላ ሐሰተኛ ትኬት አሠርተው ሽልማት ለማግኘት የሚሞክሩና በተለይ ፈጣን ሎተሪዎች ላይ ሐሰተኛ ቁጥሮችን ለጥፈው ዕድለኛ መሆናቸውን በመግለጽ ለማውጣት የተቸገሩ በማስመሰል ኅብረተሰቡን የሚያታልሉ መኖራቸውን አስታውሰው፤ አንድ አሸናፊ ያሸነፈበትን ዕጣ ቁጥር ይዞ ሲቀርብ አስተዳደሩ ክፍያ የሚፈጽመው የትኬቱን ትክክለኛነት ከአታሚው ድርጅት አረጋግጦ ነው ብለዋል፡፡

ኅብረተሰቡም ገንዘቡን በአጭበርባሪዎች እንዳይበላ ተገቢውን የጥንቃቄ እርምጃ መውሰድ እንዳለበት አሳስበዋል፡፡

የዕድል ጨዋታን የማከናወን ሕጋዊ ሥልጣን ያለው ብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር ነው ያሉት ዳይሬክተሩ፤ በገበያዎች አካባቢ ከሚደረጉ የዕድል ጨዋታዎች እስከ ትልልቅ ተቋማት የሚሳተፉባቸው የዕድል ጨዋታዎች ይከናወናሉ፡፡ ይህን ሕገወጥ ተግባር ለመከላከል አስተዳደሩ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር እየሠራ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር አደረጃጀቱን የማስተካከልና አገልግሎቱን በቴክኖሎጂ የመደገፍ ሥራዎች ላይ ትኩረት አድርጎ እየሠራ መሆኑን ያስታወቁት አቶ ቴዎድሮስ፤ በቀጣይነትም ከወረቀት ሎተሪ ባለፈ ዲጂታል ሎተሪዎችን በተጠናከረ መልኩ ለማኅበረሰቡ ለማቅረብ ይሠራል ብለዋል፡፡

# “ቀይ ባሕርን ለጋራ ዕድገት...

ከገጽ 1 የዞረ

ገልጸዋል፡፡

ሕዝቦች ለአያሌ ዘመናት በአብሮነት በመኖራቸው ወደ ጦርነት የሚያስገባ አንዳች ነገር አለመኖሩን በመግለጽ፤ በጋራ መስማማትና መግባባት ከተቻለ የጋራ ተጠቃሚ የሚሆንበት ሁኔታ እንደሚፈጠር ተናግረዋል።

በቀጠናው ተባብሮ መሥራት ከተቻለ አብሮ መለወጥም፣ ማደግም ይቻላል ያሉት አረጋዊ በርሄ (ዶ/ር)፤ የጋራ ተጠቃሚነት ላይ በመሥራት በአካባቢው ያሉ አገሮች ጾማቸውን ያደሩ ሰፋፊ መሬቶችን ማልማት በጋራ መጠቀም እንደሚቻል አመልክተዋል።

ኢትዮጵያ የባሕር በር ጥያቄን ሰላማዊ መሆኑን የገለጹት ፖለቲከኛው፤ አብሮ ለማደግ ለሁሉም የሚመች ሕግንና ሰላምን የተከተለ አጠቃቀም ይኑር ማለቷ ተገቢ ነው ሲሉ አስረድተዋል።

በሰላም፣ በድርድርና በሕግ መብትን ማስከበር ተገቢ መሆኑን ገልጸው፤ በሰጥቶ መቀበል መርሕ፣ በመግባባት፣ ለጋራ ብልጽግና፣ ዕድገትና ልማት እንዲውል ተግባብቶ መሥራት እንዳለበት አመልክተዋል፡፡

የባሕር በር ጥያቄ በሕዝቡ ዘንድ ድሮም ነበረ አሁንም ያለና ወደ ፊትም የሚኖር ነው ያሉት አረጋዊ በርሄ (ዶ/ር) ፤ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በሕዝብ ውስጥ የነበረን ጥያቄ በግልጽ አውጥተው እንዲወያይበት ማድረጋቸው ተገቢ ነው ብለዋል፡፡

በባሕር በር ጉዳይ የዜጎችን የጋራ ተጠቃሚነት አርቆ በማሰብ መግባባት እንደሚያስፈልግ ጠቅሰው፤ ወደ ጦርነት ያመራል የሚለው ፍራቻ አብሮ የመጠቀምና የማደግ ፍላጎትን ካለመረዳት የሚመጣ በመሆኑ ወደ ጦርነት የሚያመራ አይደለም ሲሉ ገልጸዋል፡፡

የኢትዮጵያ የባሕር በር ጥያቄን ማንሳት መብቷ መሆኑን ጠቅሰው፤ ሰላምና ሕግን ተከትሎ መሄድ ገንቢና ለሁሉም የሚጠቅም መንገድ ነው ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ኢትዮጵያ በታሪክ ለብዙ ዘመናት የባሕር በር ባለቤት እንደነበረች አስታውሰው፤ በዓለም የውሃና የባሕር በር ሕጎች፣ ከሕዝብና ከመሬት ስፋት አንጻር የሚገባት መሆኑን ሕጎች እንደሚደነግጉ አመልክተዋል፡፡

የባሕር በርን በሰላማዊ መንገድ ሀገራዊ አጀንዳ ሆኖ በግልጽ መወያየት አስፈላጊ መሆኑን በመግለጽ፤ ጦርነት ፈላጊዎች አይደለንም፤ አብረን እንደግ፤ እንለወጥ በማለት መንቀሳቀስ ተገቢና ፍትሐዊነት ነው ብለዋል፡፡

የባሕር በር ጉዳይ ላይ የተቃዋሚ ፓርቲዎች፣ ማኅበረሰብ አንቂዎች፣ ከሲቪክ ማኅበራት ጋር ውይይት ማድረግ እንደሚያስፈልግ በመግለጽ፤ በተለይም ጥያቄው ሰላማዊና የመብት ጥያቄ መሆኑን ማስገንዘብ ያስፈልጋል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

# 56 ሺህ አርሶ አደሮች ከሁለት ቢሊዮን ብር በላይ ብድር ተጠቃሚ ሆነዋል

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- ባለፉት አራት ዓመታት 56 ሺህ አርሶ አደሮች የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፍኬታቸውን በማስያዝ ከፋይናንስ ተቋማት ከሁለት ቢሊዮን ብር በላይ ብድር ወስደው ተጠቃሚ መሆናቸውን የግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

በግብርና ሚኒስቴር የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ ትግስቱ ገብረ መስቀል ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ሚኒስቴሩ አርሶ አደሮች የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት እንዲያገኙና ሰርተፍኬቱን በማስያዝ ብድር እንዲያገኙ ድጋፍ እያደረገ ይገኛል።

ቀደም ሲል አርሶ አደሩ መሬቱን በማስያዝ ከባንክ ብድር መውሰድ የሚችልበት ዕድል አልነበረም ያሉት አቶ ትግስቱ፤ አርሶ አደሩ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፍኬቱን በማስያዝ ብድር እንዲወስድ የሚፈቅደው አሠራር በሙከራ ደረጃ መጀመሩን ጠቁመዋል።

ከአስር ፋይናንስ ተቋማት ጋር በትብብር በመሥራት ላለፉት አራት ዓመታት የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፍኬቱን በማስያዝ 56 ሺህ አርሶ አደሮች ብድር እንዲወስዱ በትብብር መሠራቱን አስታውቀዋል።

የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፍኬትን በማስያዝ ብድር በመውሰድ ለግብርናም ሆነ ለተለያዩ ሥራዎች ማዋል የሚቻልበት አማራጭ መኖሩን አርሶ አደሩ እንዲገነዘብ በስፋት እየተሠራ መሆኑን አመልክተዋል።

በተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ አርሶ አደሮች የብድር ተጠቃሚ መሆን ሲፈልጉ በግብርናና በፋይናንስ ባለሙያዎች አማካኝነት ታግዘው የብድር ፕሮጀክታቸውን ለፋይናንስ ተቋማት የሚያቀርቡበት ዕድል መኖሩን አስረድተዋል።

ብድሩ ከተገኘ በኋላም አርሶ አደሮቹ በተገቢው መንገድ ጥቅም ላይ እንዲያውሉት አስፈላጊው ድጋፍ እየተደረገላቸው እንደሚገኝ ገልጸዋል።

አርሶ አደሮቹ የብድር አማራጮችን በመጠቀም ዘመናዊ የእርሻ መሣሪያዎችን ለመጠቀም፣ የተፈጥሮ ማዳበሪያ በሰፊው ለማዘጋጀትና የተለያዩ የሥራ ዕድሎችን ለመፍጠር እየሠሩ እንደሚገኝ አስታውቀዋል።

የብድር አገልግሎቱ ከማይክሮ ፋይናንስና ሁለት ባንኮችን ጨምሮ ከ10 የፋይናንስ ተቋማት አርሶ አደሮች ተጠቃሚ መሆናቸውን በመግለጽ በአማራ፣ በኦሮሚያና በቀድሞው ደቡብ ክልሎች የሚገኙ 56 ሺህ አርሶ አደሮች የይዞታ ማረጋገጫቸውን በማስያዝ ተጠቅመው ብድራቸውን መመለስ ችለዋል ብለዋል፡፡

አሠራሩ የአርሶ አደሮችን የብድር ተደራሽነት በማሳደግ የፋይናንስ አቅማቸው እንዲጠናከር አይነተኛ አማራጭ ይሆናል ሲሉ ተናግረዋል።

በገጠር አካባቢ የሚኖሩ ወጣቶች ብድር ወስደው መሥራት በመቻላቸው ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚደረገውን ጥረት ይደግፋል ያሉት አቶ ትግስቱ፤ በተለይም የሥራ ዕድል ፈጠራን ለማበረታታት የሚረዳ አሠራር በመሆኑ በቀጣይም ተጠናክሮ እንዲቀጥል ጥረት ይደረጋል ብለዋል።

የተለያዩ የመሬት ዝውውር ግብይቶች አይነቶች መኖራቸውንና በውርስ፣ ስጦታ እንዲሁም መሬትን የማከራየት ተግባራት ሲከናወኑ መቆየታቸውን ገልጸዋል።

እስከ አሁን የነበረው የመሬት ኪራይ ሥርዓት መደበኛ አሠራር እንዳልነበረው በመጠቆም፤ በአሁኑ ወቅት አርሶአደሩ በመንግሥት በተመዘገበ ውል መሠረት ተጠቃሚ የሚያደርግ ሁኔታ መፈጠሩን አመላክተዋል።

የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት የመልካም አስተዳደር ሥርዓት ጥያቄዎች መመለስ እንደሚያስችል ገልጸው፤ ከመሬት ጋር የተያያዙ ግጭቶችን በመቀነስ፣ የመልካም አስተዳደርን ለማስፈን እንደሚረዳ አስረድተዋል፡፡

ቀበሌዎችን በክላስተር በማደራጀት በተንቀሳቃሽ የመሬት አስተዳደር አገልግሎት ሥርዓት አማካኝነት ለአርሶ አደሮች የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት እየተሰጠ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

# በሠላም ማስከበር...

ከገጽ 1 የዞረ

ሠራዊቱ በሠላም ማስከበር ተልዕኮው በርካታ ሀገራት የዘመተ፤ የትም ዘምቶ ያለውን የሚያካፍል፣ በዲሲፕሊኑ የተከበረ፣ ሕዝብ የሚወደው፣ ከራስ ሕዝብ አልፎ የሌሎች ሕዝቦች ሲራቡና ሲገፉ ማየት የማይፈልግ መሆኑን በተግባር ያረጋገጠ መሆኑን አንስተዋል፡፡

ሚኒስትሩ፤ መከላከያ ከሌለ ፀረ ሠላም ኃይሎች የሚፈልጉትን ለማድረግ ቀላል ስለሚሆንላቸውና የሀገሪቷ ዋናዋ አቅሟ ሠራዊቱ በመሆኑ ስሙን ለማጠልሸት የማይደረግ ነገር የለም ብለዋል፡፡ ይሄንን ለመመከት ሁሉም ኃላፊነቱን መወጣት እንዳለበትም ተናግረዋል፡፡

አሁን ላይ ያለውን የሠራዊቱን ቁመና በሚመለከት በሽፍቶች ይቅርና ከየትኛውም አቅጣጫ የሚመጣ ኃይል ለመመከት የሚያስችል አቅም እንዳለ ገልጸዋል፡፡

እንደ ሀገር ከፀጥታው ጋር ተያይዞ ከሦስት ወራት በፊት የነበረውና አሁን ያለው ሁኔታ የተለያየ ነው ያሉት ሚኒስትሩ፤ መንግሥትን ለማፍረስ ተንስተው የነበሩ ሀሳቦች መጥፋታቸውን፤ ዕድሉን እንደማያገኙም ማረጋገጫ እንደተሰጣቸው ገልጸዋል፡፡

መከላከያ የሀገር ሉዓላዊነትን ከማስጠበቅ ጀምሮ ሰፊ ተልዕኮ ያለው እንጂ ሌባና ሽፍታ ማሳደድ እንዳልሆነ ሊታወቅ ይገባል በማለት፤ ከቀበሌ ጀምሮ ያሉት የአስተዳደር እርከኖች ፀጥታና ደህንነት ላይ መሥራት እንዳለባቸው ተናግረዋል፡፡

አሁንም የፀጥታ መደፍረስ እንቅስቃሴዎች መኖራቸውን ሚኒስትሩ አንስተዋል፡፡ ክፍተቱ የተስተዋለው የአስተዳደር አካላትና የሰፈር የፀጥታ አካላት የሚጠበቅባቸውን ባለመሥራታቸው ነው በማለት፤ ሁሉም ኃላፊነቱን ከተወጣና በመናበብ ከተሠራ ሠላምን የማጽናት ዕድል ሰፊ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

የኢፌዴሪ የሀገር መከላከያ ሚኒስትር ዴኤታ ወይዘሮ ማርታ ሉዊጂ በበኩላቸው፤ መከላከያ ሠራዊቱ የሀገር ምሽግና የሉዓላዊነትና ደህንነት ጥግ ስለሆነ ሀገርን ለማፍረስ የሚፈልግ ሁሉ ከሁሉም ብሔር ብሔረሰብ የተውጣጣውን መከላከያን ማጠልሸት፤ ምቹ አጋጣሚ አድርገው ይጠቀሙበታል ነው ያሉት፡፡ ይህንን ለመመከት እንደ መከላከያ ጠንካራ የሆነ የመረጃ መስጫ መንገዶች እንዳለም አመልክተዋል፡፡

እንደ መከላከያ ሠራዊት በተለያዩ ግንኙነቶች የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች እየተከናወኑ እንዳለ የጠቀሱት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ ሁሉም ሀገሩን የሚወድ ዜጋ የመከላከያ ሠራዊቱን መደገፍ አለበት ብለዋል፡፡

ጽንፈኛ ኃይሎች የመከላከያ ሠራዊቱን ስም ለማጠልሸትና ከሕዝብ ለመነጠል መከላከያን በትነን ሀገር እንበትናለን የሚለውን ዓላማቸውን እንዳያሳኩ መከላከል የሁሉም ዜጋ ሚና መሆን እንዳለበትም አመልክተዋል፡፡

ሠራዊቱ ለሀገር የሚሰዋ፣ ለሕዝብ የሚሞት፣ ከሁሉም ብሔር ብሔረሰቦች ጋር አብሮ የሚሠራ ነው። ነፃ ጊዜ ሲያገኝ ልማቱን የሚሠራና ያለውን የሚያካፍል ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ሠራዊት የማጠልሸት ሥራ እየተሠራ ያለው ሀገርን ለመበተን በሚፈልግ አካል መሆኑ ታውቆ ሁሉም ጠንካራ የሕዝብ ልጅ የሆነውን ሠራዊት ስሙን መገንባት ይኖርበታል ነው ያሉት፡፡

ከሠላም ማስከበር ጋር ተያይዞ ሠራዊቱ ከሀገር ውስጥ ባለፈ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተመርጦ የሠላም ማስከበር ትልቅ ግዳጅ የመወጣት ብቃት፣ ሥነ ምግባርና ሕዝባዊነት ያለው መሆኑን ገልጸዋል፡፡ በዚህም በተለያዩ ሀገራት የሠላም ማስከበር ሥራዎችን እየሠራ እንደሚገኝ ጠቅሰዋል፡፡

ለሠላም ማስከበር ተልዕኮ በሙያና በሥነ ምግባር ብቁ የሆነ፤ በግዳጅ ውስጥ ዘመናዊ መሣሪያና ቴክኖሎጂ መጠቀም የሚችል መሆኑንም ነው የጠቆሙት፡፡

ቋሚ ኮሚቴው የሚኒስቴሩን የሦስት ወራት አፈጻጸም ካዳመጠ በኋላ በሙያዊ ብቃት የተደራጀ ጠንካራ የባሕር ኃይል አደረጃጀት የመፍጠር ሥራው ተጠናክሮ እንዲቀጥልም አቅጣጫ አስቀምጧል፡፡

# ወቅታዊ

# «ኢትዮጵያ በውሃ ዲፕሎማሲ ረገድ በርካታ ተሞክሮዎች ያሳት ሀገር ነች»

*-ዶክተር ያዕቆብ አርሳኖ*

ስምስም መንግሥቱ

**ኢትዮጵያ በኤሌክትሪክ ኃይል እጦት በኋላ ቀር ኑሮ ውስጥ የሚገኙ ዜጎችዋን ለመታደግ የተያያዘችውን የታሳቁን የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ሥራ አጠናቅቃ ከዳር እንዳታደርስ በርካታ እንቅፋቶች ገጥመዋታል። ሆኖም ግን እንቅፋቶች ሳይበግሯት በሰራቻቸው ጠንካራ የዲፕሎማሲ ስራዎች እሾህና አሜካላዎችን እያስፈች ግድቡን ወደ ማጠናቀቅ ደርሳለች፡፡**

**በውሃ ዲፕሎማሲ ላይ ስለተሰሩት ሥራዎችና የተገኙ ውጤቶች እንዲሁም በባሕር በር ዙሪያም ያነጋገርናቸው በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምህርና የዓባይ ጉዳይ ተመራማሪ ዶክተር ያዕቆብ አርሳኖ እንደሚከተለው ማብራሪያ ሰጥተውናል፡፡**



**አዲስ ዘመን፡- የታሳቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ግንባታ እውን መደረግን ተከትሎ ከተለያዩ አቅጣጫ የነበረውን ጫና ለመመከት በኢትዮጵያ በኩል የተሰሩ የዲፕሎማሲ ሥራዎችን ቢያብራሩልን?**

**ዶክተር ያዕቆብ፡-** የታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ግንባታ ከተጀመረ ወዲህ ከፍተኛ የሆነ የዲፕሎማሲ ጫና ተፈጥሮብን ነበር፡፡ የመጀመሪያው ጫና በግብጽና ሱዳን የተፈጠረ ሲሆን፤ ሀገራቱ በዚያን ጊዜ በአንድ ላይ ነበር የሚያስቡት፡፡ እኛን ሳታስፈቅዱ፣ ሳታማክሩ ግድቡን ልትሰሩ አትችሉም ይሉ ነበር፡፡

ለምርምር ሥራና ለጉባኤ ወደ ግብጽና ሱዳን ሀገራት ስንሄድ በፍጹም ሊታመኑ የማይችሉ አሉታዊ ሃሳቦችን ያንጸባርቁ ነበር፡፡ እኛን የሚጨርስ፣ ሕዝባችንን ለችግር የሚዳርግ፣ እርሻችንን የሚያደርቅ ሕዝባችንን ወደ ረሃብ የሚከት ግድብ ኢትዮጵያ ልትሰራ አትችልም፤ ከጀመረችም ማቆም አለባት የሚል ዘመቻ ነበር የሚያካሂዱት የጦርነት ዛቻም አለበት፡፡

የምዕራቡ ዓለም ደግሞ ብዙን ጊዜ ግብጽን ነው የሚሰማው፡፡ ግብጽ በጂኦ ፖለቲካ ረገድ በአውሮፓ፣ በእስያና በአፍሪካ መካከል ስላለች እና ለረጅም ዘመናት አውሮፓና አሜሪካ የሚሉትን ተቀብላ ስለምታራምድ በአፍሪካም በመካከለኛው ምሥራቅም፤ እንዲሁም ግብጽ በአረቦችና በእስራኤል መካከል ያለውን ግጭትና አለመግባባት እኔ ነኝ ድልድይ ሆኜ ግጭቱ እንዳይሰፋ፤ ጥረት እያደረኩና እየሰራሁ ያለሁት ስለምትል አውሮፓም፣ አሜሪካንም ምዕራቡ ዓለም በጠቅላላ ማለት ይቻላል እርስዋ የምትለውን ሁሉ የሚደግፍ ነው፡፡

በዚሁ ምክንያትም ኢትዮጵያ ላይ በርካታ ጫናዎች ይደርሱ ነበር፡፡ ግብጽ በናይል ውሃ ላይ ነው ሕይወቷ የተመሠረተው ኢትዮጵያ እንዴት ግብጽን ለመጉዳት ትነሳለች? በማለት በየሚሳተፉበት ጉባኤ ላይ ሁሉ ኢትዮጵያን ሲወቅሱ ይሰሙ ነበር፡፡

በኢትዮጵያ በኩል ይሄ ትክክለኛ ትርክት ስላልሆነ ግድቡን ለመሥራት ለረጅም ጊዜ ያቀደችበትና ለሕዝቧም የሚጠቅም እንደሆነ፤ በ1950ዎቹ ጊዜ በአፄ ኃይለሥላሴ ዘመን፤ በአባይ ሸለቆ 33 ፕሮጀክቶች አዘጋጅታ ከነዚህ መካከልም በ1970ዎቹ ፊንጫ ፕሮጀክትን፣ ጣና በለስም እንዲሁ በ1990ዎቹ እውን አድርጋለች፡፡ አቅም ማጣትና ምቹ ሁኔታዎች ባለመፈጠራቸው ምክንያት ወደ ሥራ ሳይገባ የዘገየ እንጂ ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ፕሮጀክትም ከነዚህ መካከል አንዱ ፕሮጀክት ነበር፡፡ ቦርደር ዳም (Border Dam) ተብሎ የሚታወቅ፡፡ የጥናት ሥራ ስንሰራም ሆነ ስናቅድ እናንተን አስፈቅደን ሳይሆን ልማታችንን መሠረት አድርገን ነው የሚል ማብራሪያ ለሚቃወሙን ሁሉ በኢትዮጵያ በኩል ማብራሪያ ቢሰጣቸውም ሊቀበሉ አልቻሉም፡፡

ኢትዮጵያ ይሄን ግድብ ለመሥራት ስታቅድ ሕዝቦቿን ከጨለማ ለማውጣት እንጂ ግብጽንም ሆነ ሱዳንን ለመጉዳት አይደለም፡፡ ይህ ግድብ ከጥቅም በስተቀር በማንም ላይ ጉዳት አያመጣም፡፡ ይህ ሁሉ እየታወቀ የኢትዮጵያን ማደግ የማይቀበሉ ሀገራት ስለግድቡ መስማትም ሆነ መግባባት ላይ መድረስ አልዋጥ ሲላቸው ይታያል፡፡

በሶስታችን መካከል የበለጠ መግባባትም ለመፍጠር ዓለም አቀፍ አጥኚ ቡድን ተቋቁሞ የግድቡን አጠቃላይ ሁኔታ እንዲያጠና ተደርጓል፡፡

በዚሁ መሰረት በማሕበራዊ ተጠቃሚነት ላይ በዘርፉ በዓለም አቀፍ ደረጃ ባለሞያ የሆኑ አጥኚ ቡድኖችን አወዳድረን በጋራ ቀጥረን በማስገምገም ደግሞ እነርሱ የሚሉንን እንስማ ተብሎ በኢትዮጵያ በኩል ሀሳብ ቀርቦ ባለሙያዎች ተቀጥረው ከአንድ ዓመት በላይ ለሚሆን ጊዜ ሰርተው ጥናታቸውን አጠናቀቁ፡፡ በዚህ ቡድን ውስጥ በሞያው የታወቁ የሶስቱም ሀገሮች ባለሞያዎች ተሳትፈውበታል፡፡

መጨረሻ ላይ ግብጽና ሱዳን ግድቡ አይረባም ብለው ሲያጣጥሉት የነበረው ሀሳብ ውድቅ ሆኖ ሥራውም ጥብቅና ዓለምአቀፍ ደረጃውን የጠበቀ መሆኑን፣ የዓለምአቀፍ መሥፈርቶች ሁሉ ተጠቅሰው ግዱቡ በዚህ ረገድ ጥያቄ ሊነሳበት እንደማይችል ሪፖርት ጻፉ፡፡ ሪፖርቱ ለግብጽም፣ ለሱዳንም፣ ለኢትዮጵያም ግልጽ እንዲሆን ነው የተደረገው። ለሶስተኛ ወገን ሁሉ እንዲታወቅ የተደረገ ሪፖርት ነበር፡፡

ለወደፊት ግድቡ በግብጽና ሱዳን ላይ ተጽዕኖ ያስከትላል የሚል ነገር ካለ እየቆየ፤ሶስታችሁም ተመካክራችሁ ባለሞያ በመቅጠር ምክረሃሳብ መውሰድ ትችላላችሁ፤ነገር ግን የግድቡ ሥራ እንዲቆም የሚያስገድድ ችግር የሚያስከትልና በአደጋ ደረጃ የሚገለጽና የሚታይ ነገር የለም ብለው ነው የዳኙት፡፡ ሪፖርቱ፤ ለዓለም የቀረበ ነው፡፡ የዓለም አቀፉ ጫና በዚህ ተነፈሰ ማለት ይቻላል፡፡

ግድቡ ይጎዳናል የሚለውን ሀሳብ ደጋግመው ስለሚያነሱ፤ ምን እናድርግ ተብሎ ምክክር ሲጀመር የሶስቱ ሀገራት የውሃ ሚኒስትሮች የተሳተፉበት ሶስትዮሽ የተባለ የጋራ ኮሚቴ ተቋቋመ፡፡ ኮሚቴውም ከአንድ ዓመት በላይ ነበር ሥራውን የሰራው፡፡ አሁንም ለግብጽ ስሞታ ምላሽ ለመስጠት ሲባል በአካባቢና ማሕበራዊ ረገድ የግድቡን ተጽዕኖ ለማጣራት ሲባል አንድ ገለልተኛ የሆነ በውሃ ጥናትና ምርምር የተካነ ድርጅት ምክር ይስጠን ተብሎ ዋናውን ሥራ የሚሰራ አንድ የፈረንሳይ ድርጅት እና አንድ የደች ድርጅት ደግሞ ረዳት ሆኖ እንዲሰሩ፣ የ70/30 የሥራ ድርሻ እንዲኖራቸው ተደርጎ በውድድር እንዲቀጠሩ ተደረገ፡፡ ይሁን እንጂ ግብጾች ከአሁን በፊት እኛ የነበረንን የውሃ ድርሻ አክብራችሁ እርሱ ላይ ተመሥርታችሁ ነው የምትሰሩት የሚል የማሰናከያ ሃሳብ አቀረቡ፡፡

በኢትዮጵያ በኩል ደግሞ ቀድሞ የነበረው የውሃ ክፍፍል ጊዜ ያለፈበትና የማያሰራ ነው፡፡ የቆየ ትርክት ነው። እኛ ደግሞ የምንፈልገው፤ ከመሠረቱ ጀምሮ የግድብ ሥራ ግብጽን፣ ሱዳንን፣ እንዴት ይጎዳል፣ እንዴትስ ተጠቃሚ ያደርጋል የሚለውን ሚዛን ነው እንጂ እናንተ የምትሉትን አንቀበልም የሚል ሃሳብ ተነሳ፡፡ በዚሁ ምክንያት ጥናቱ ኢንሴፕሽን የሚባል ደረጃ ደርሶ በግብጾች ጫናና ማስተጓጎል ቆመ፡፡

በኢትዮጵያ በኩል ለአካሄድ እንዲረዳ፤ ናሽናል ፓናል ኦፍ ኤክስፐርትስ ወይንም ብሄራዊ የኤክስፐርቶች ፓናል ቀደም ሲል ተቋቁሞ የማማከር ተግባሩን ቀጥሏል፡፡ በዚህ ውስጥም በውሃ ሀብት፣ በአካባቢ ጥበቃ፤ በጂኦፖለቲክስ፣ በሕግ፤ በዲፕሎማሲ፣ በግድብ ግንባታ ሞያ፣ ወዘተ የምርምር እውቀትና ልምድ ያላቸው ወደ 29 የሚሆኑ ባለሞያዎች እንስዲሳተፉ ተደርጓል፡፡

ይህ የባለሙያዎች ቡድን በውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር አማካኝነት ነው የተቋቋመው፡፡ የባለሙያዎች ቡድኑ ኢትዮጵያ ሥራዋን እንዴት ብታካሂድ፣ ከግብጽና ከሱዳን የሚመጣባትን ጥያቄ በምን መልኩ ምላሽ ብትሰጥ ይሻላል፣ በነርሱ ጀርባም ሆኖ ጥያቄ ለሚያቀርብ፣ እንዲሁ በተመሳሳይ ጥያቄ ላላቸው ለተለያዩ አካላት ምላሽ መስጠት የሚችል ኤክስፐርቶችን አካቶ የተቋቋመው ነው፡፡ ፓናሉ ጠንካራና የሞያ ስብጥር ያለው ነው፡፡ አሁንም ዝግጁ ሆኖ በሥራ ላይ ያለ ፓናል ነው፡፡

እንደሚታወሰው እኤአ በጃንዋሪ 2020 በዋሽግተን ዲሲ ድርድር መሳይ ውይይት ተካሂዶ ነበር፡፡ እነዚህ በውሃ ሀብት፣ በሕግ፣ በጆኦፖለቲካ፣ በዲፕሎማሲና በተዛማጅ ሞያዎች እውቀቱና ልምድ ያላቸው በድርድሩ ጠረጴዛ ላይ ተቀምጠው እውቀታቸውን መሠረት በማድረግ ኢትዮጵያን ወክለው ብሔራዊ ጥቅም ለማስከበር መሳተፋቸው ይታወሳል፡፡ በኢትዮጵያ በኩል በዚህ መልኩ ሲሰራ ቆይቷል፡፡ የዋሽግተን ዲሲ ውይይት ወይንም ድርድር ለኢትዮጵያ ረብ ያለው ነገር ያላመጣ መሆኑን በመገንዘብ የኢትዮጵያ ወገን አቋርጦ ተመልሷል፡፡

ይሄ የኢትዮጵያ አካሄድ የዲፕሎማሲ ጫናን መቀነስ ብቻ ሳይሆን፣ ዲፕሎማሲው በሙሉ እውቀት ላይ ተመሥርቶ፤ ግድቡ ለኢትዮጵያ የሚጠቅመውን ያህል ሌሎች ሀገሮችን በከፋ ደረጃ የማይጎዳ መሆኑን በማሳየት ሥራ ተሰርቷል፡፡ ጉዳዩን በአብዛኛው የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር የሚመራው ቢሆንም፣ ጫን ያለ ነገር ሲኖር የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ አልፎ አልፎ ደግሞ ጉዳዩ በጠቅላይ ሚኒስትር ደረጃ የሚከናወንበት ሁኔታ ነው የነበረው፡፡

እንግዲህ በኢትዮጵያ ደረጃ የግብጽን፣ የሱዳንን፣ የነርሱን ወዳጆችና ደጋፊዎች ከግራም ከቀኝም ለመከላከልና ለመመከት ዲፕሎማሲያችን አንደኛ በኤክስፐርት ደረጃ የተዋቀረ፣ ሁለተኛም ተጠሪው መሥሪያቤት የውሃ ሚኒስቴር ስለሆነ በዚህ ደረጃም የተዋቀረ፤ ነገሩ ከፍ ሲል በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፤ አመራር ሲፈለግም ጠቅላይ ሚኒስቴር ድረስ የሚሄድ መዋቅር ያለው፤ የዲፕሎማሲ አካሄድ ነው፡፡ ይሄ በጣም ወሳኝና ውጤታማ አካሄድ ነበር፡፡

በተጨማሪ ሥራውን ለመደገፍ መላ ሕብረተሰብን በማስተባበር፤ በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር የሚመራ፤ ዩኒቨርሲቲዎችን፣ የንግዱን ማሕበረሰብ፣ አርቲስቶችን፣ ታዋቂ ግለሰቦች ወዘተ የተካተቱበት ወደ 90 የሚሆኑ አባላትን የያዘ በብሔራዊ ደረጃ የተቋቋመ ካውንስል አለ፡ ፡ ካውንስሉ ለግድቡ ግንባታ የሚያግዝና ለግንባታ የሚውል ገቢ በማሰባሰብና በተለያየ መንገድ ለመከታተልም የተቋቋመ ሲሆን፣በተጓዳኝም የሕዳሴ ግድብ ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት ተቋቁሞ የተጠናከረ ሥራ እየተሰራ ይገኛል፡፡

ዲፕሎማሲውን ከፍ ለማድረግ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈጉባኤ የሚመራው በተለያየ የሙያ ዘርፍ ውስጥ የሚገኙ አካላት የተሳተፉበት ፐብሊክ ዲፕሎማሲ እንዲሁ ተዋቅሯል፡፡ ይህም ግድቡ ለኢትዮጵያም ሆነ ለግብጽ፣ ለሱዳንና ለሌሎች ሀገሮች፣ በአጠቃላይ ለሁሉም የሚጠቅም መሆኑን ለማሳየት እንዲቻል፤ ይህንኑ ለግብጽ፣ ለሱዳንና ለሌሎች የጎረቤት ሀገራት ፖለቲከኞችና ባለሞያዎች ለማብራራት የተቋቋመ ነው፡፡

የፐብሊክ ዲፕሎማሲ ቡድን ወደ ግብጽ፣ ሱዳን፣ ጅቡቲና ዩጋንዳ ሄዷል፡፡ ከሱዳንና ከብጽም እንዲሁ ተመሳሳይ ቡድኖች ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ተስተናግደዋል። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲም አንዱ የጉብኝት መዳረሻ ሆኖ ነበር። ፐብሊክ ዲፕሎማሲ በአባልነት ብቻ ሳይሆን በሚሄዱበት ሥፍራ ምን ያጋጥማቸዋል፣ ምንስ ይጠቀማሉ፣በምን አይነት እራሳቸውን ማዘጋጀት አለባቸው፤ በአጠቃላይ ውይይቶች ላይ ለመሳተፍ ምን አይነት ዝግጅት ያስፈልጋል በሚሉ ጉዳዮች ዙርያ ቅድመ ዝግጅት ተደርጎ ተከናውኗል፡፡

ዲፕሎማሲ ሁለት አይነት ነው፡፡ አንዱ በቀጥታ መንግሥት የሾማቸውና ያደራጃቸው፤ የመንግሥት ተጠሪ መሥሪያ ቤቶች የሚመሩትና የሚሳተፉበት ነው፡፡ ሌላው ዲፕሎማሲ መንግሥታዊ ያልሆነው ነው፡፡ በዜግነት፣ በእውቀትና በሥራ አጋጣሚዎች የሚካሄድ ዲፕሎማሲ ነው። ኢትዮጵያን የሚጠቅም ብቻ ሳይሆን ሌሎችንም የማይጎዳ መሆኑን በማስረዳት የሚያግዝ ሲሆን፤ በዚህ መንግሥታዊ ባልሆነ ዲፕሎማሲ በውሃና በተያያዥ ዘርፎች የዲፕሎማሲ ተግባራት ተከናውነዋል ለማለት ይቻላል፡፡

በምርምር ዘርፉም ቢሆን፤ ውሃና ማሕበረሰብ በሚል ምሁራዊ የሆነ የጥናትና ምርምር ሥራዎችና የምክክር መድረኮች እንዲሁም ኢትዮጵያ የታላቁ የሕዳሴ ግድብን

ወደ ገጽ 8 ዞሯል

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ

# «ኢትዮጵያ በውሃ ዲፕሎማሲ...

ከገጽ 7 የዞረ

ጨምሮ በውሃ ዘርፍ የምትሰራቻቸውን ለሀገር ጠቃሚ ሥራዎችን በተመለከተ መንግሥታዊ ባልሆነው የዲፕሎማሲ በርካታ ሥራ ተሰርቷል፡፡ በዚህ ሁሉ መንገድ ሥራዎችን በመሥራት ነው የውጭውን ጫና ለመቋቋም ጥረት የተደረገው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- እነዚህ ሁሉ ስራዎች ሲሰሩ ያጋጠሙ ችግሮች ነበሩ?**

**ዶክተር ያዕቆብ አርሳኖ፡-** ሥራዎች ሲሰሩ የተለያዩ ፈተናዎች አጋጥመዋል፡፡ በቃላት ሁሉ የሚገለጹ ጫናዎችና ፈተናዎችን በማሳለፍ ጭምር ነው ዲፕሎማሲው ሲካሄድ የቆየው፡፡ ግብጾች እጃቸው ረዘም እንደሚል ይታወቃል። ኢትዮጵያ የምታከናውነው የግድብ ሥራ ከፍተኛ ጉዳት ያስከትልብናል በማለት ጩኸቷን ለአሜሪካና ለአውሮፓ በማሰማት ያለማቋረጥ ጥረት አድርጋለች፡፡

እኤአ በጃንዋሪ 2020 የዋሽግተን ዲሲ የአሜሪካው ፕሬዚደንት ትራንፕ ለግብጽ ወገናዊነታቸውን ማሳየታቸው ግልጽ ነበር፡፡ የውይይቱ ሂደት የኢትዮጵያን የግድብ ግንባታ ሥራ የሚያደናቅፍ ነበር፡፡ አሜሪካ ሶስቱን ወገኖች ጠርታ ለማወያየት ያደረገችው ጥረት ውጤቱ በፕሬዚደንቱ እይታ ጥሩ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በአሜሪካን በኩል ለሁላችሁም ይበጃል ተብሎ ሰነድ ተዘጋጀ፤ ሰነዱ ግን ለኢትዮጵያ እራስን የሚገል አይነት ነው የነበረው፡፡ የኢትዮጵያ ወገን ሰነዱ ላይ ሳይፈርም ተመለሰ፡፡

ቀደም ሲል ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ከሁለት ሚኒስትሮችና በድርድር ውስጥ ከሚገኙ አማካሪዎች ጋር ውይይት ባደረጉበት ወቅት ‹‹ልምዱ፣ እውቀቱና የሀገር ፍቅርም አላችሁ፤ ይሄ የተረጋገጠ ነገር ነው፤ በዲፕሎማሲውና በድርድሩ በሙሉ ልባችሁ ሥሩ፤ ለኢትዮጵያ በሚሆን መንገድ እንደምትሰሩም አልጠራጠርም፤ ከልካይ የላችሁም።

አስፈላጊ ሀብት አሰባስቤ ግድቡን መገንባት የኔ ሥራ ነው፡፡ ግድቡን እኔ ገነባለሁ ዲፕሎማሲውን እናንተ አካሂዱ›› ነበር ያሉን፡፡ እንግዲህ የዋሽግተን ዲሲው ድርድር የተካሄደው በልበ ሙሉነትና በአርበኝነት መንፈስ ነበር፡፡

የአሜሪካኑ ፕሬዚደንት ተበሳጭተው ግብጽ ግድቡን መምታት ነበረባት፣ እዚህ ደረጃም መድረስ አልነበረባትም ማለታቸው ይታወሳል፡፡ ይሄ ሁሉ የዲፕሎማሲው ጫና ምን ያህል እንደሆነ ማሳያ ነው፡፡ በኢትዮጵያ በኩል ጫናውን ለመቋቋም የተሰሩት ሥራዎች፤ በተለይም በአመራርም፣ በቴክኒክም የተደራጀ ኮሚቴ በማዋቀር እንዲሁም ከተለያየ የሞያ ዘርፍ የተውጣጡ ዜጎችና ባለሞያዎች ተሳታፊዎች የተካተቱበት ብሔራዊ ጥቅምን የሚያስቀድሙ በመሆናቸው ጭምር ነው ውጤታማ ሥራ መሥራት የተቻለው፡፡ የግድብ ግንባታ ሥራውም ቢሆን የተለያዩ ፈተናዎችን በመቋቋም ነው እስከ አራተኛ ዙር የውሃ ሙሌት ሥራ ማከናወን የተቻለው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ግድቡ የአፍሪካ ጉዳይ በመሆኑ የአፍሪካን ችግር በአፍሪካዊ መፍትሄ እንዲፈታ ከማድረግ አንጻር የኢትዮጵያ ሚና እና የተገኙ ውጤቶች ምንድን ናቸው?**

**ዶክተር ያዕቆብ፡-** ግብጾች ጉዳዩን በጣም ስላጦዙትና የአሜሪካንም ተጽዕኖ ስላልተሳካ ጉዳዩ በዓለም መንግሥታት ሴኪዩሪቲ ካውንስል እንዲደርስ ተደረገ፡፡ ግብጾች አደጋ ላይ ነን ካውንስሉ ይዳኘን ብለው ነበር ያቀረቡት፡፡

ግብጽ እንዲህ ያለውን ነገር እንደምታደርግ በኢትዮጵያ በኩል ቀድሞም ግምት ስለነበር ጥብቅ በሆነ ምክክርና ውይይት ዝግጅት ተደርጎ ስለነበር በኤክስፐርቶች በኩል ጎን ለጎን ሥራዎች ሲሰሩ ቆይቷል፡፡ በኢትዮጵያ በኩል ለተመድ ሴኩሪቲ ካውንስል በቀድሞ በውሃ ሚኒስትሩ ክቡር ዶክተር ስለሺ በቀለ የተሰጠው መግለጫ፤ ግድቡ የልማት ፕሮጀክ እንጂ ሌላውን የሚጎዳና የሚያጠፋ የንኩሌየር ማብለያ እንዳልሆነ፤ ለጎረቤት ሀገሮች ጭምር የሚጠቅም የኤሌክትሪክ ኃይል የሚያመነጭ የውሃ ፕሮጀክት መሆኑን የሚገልጽ ነበር።

ሴኪዩሪቲ ካውንስሉ የደህንነት ጉዳይ እንጂ የውሃ ግንባታና የልማት ሥራ ላይ አይመለከተውም ተብሎ ስለተተቸ የግብጾች አቤቱታ ከሸፈባቸው፡፡ በወቅቱም የኢትዮጵያ ሀሳብ የአፍሪካ ጉዳይ በአፍሪካ እንዲታይ የሚል ስለነበር፤ ጉዳዩ ለአፍሪካ አመራር ተላከ፡፡ በወቅቱ የአፍሪካ ሕብረት ሊቀመንበር ደቡብ አፍሪካ ነበረች፡፡ ደቡብ አፍሪካ ሀገሮች በማይጋጩበትና ለሁሉም በሚጠቅም ሁኔታ ሥራው መካሄዱን ለማረጋገጥና ለመምከር ለአንድ ዓመት ሰርታለች።

አፍሪካ ሕብረት አወያይ ወይንም አመቻች እንጂ፤ ወሳኝም ዳኛም አይደለም፡፡ ሀገሮች ብሔራዊ ጥቅሞቻቸውን ለማስከበር ሲወያዩና ሲደራደሩ፣ ሀሳቡ በደንብ



እንዲንሸራሸር የማመቻቸት ሥራ ያከናውናል፡፡ በዚህ መልኩ በአፍሪካ ሕብረት በኩል እኤአ በ2020 በዚህ ሁኔታ ነበር የተጠናቀቀው፡፡ ግን ውጤት አልተገኘበትም፡፡

እኤአ በ2021 አዲስ የአፍሪካ ሕብረት ሊቀመንበር ተመረጠ፡፡ በወቅቱም ኮንጎ ዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ ነበር የተመረጠችው፡፡ ኮንጎም የሶስትዮሽ ውይይቱን ለማመቻቸት ሞክራ ነበር፡፡ ሆኖም ግን ግብጾች የሚመቹ ሆነው ስላልተገኙ፤ አልገፋችበትም፡፡ ኢትዮጵያ የአፍሪካ ሕብረት መሪዎች ቢለዋወጡም ጉዳያችን እስከታየለን ድረስ በሚል በጥንቃቄና በትጋት ጉዳይዋን በማቅረብ ስትሳተፍ ቆይታለች፡፡ የኮንጎ የመሪነት ጊዜም አልፎ ሴኔጋል ተተካች፤ እርስዋም ብትሆን ምንም ሳትሰራ 2022 አለቀ፡፡

ኢትዮጵያ ግድቧን እየሰራች ያለችው ሌሎችን በማይጎዳ መልኩ ተጠንቅቃ በመሆኑ ይህን ሥራዋን የሚያበረታቱና ጥቅሟንም የሚያስጠብቁላት እንዲሁም ግብጽንም ሱዳንንም የሚያሸማግሏት ወዳጆች፣ ሀገሮችም ሆኑ ሌሎች ከጎኗ እስከ ሆኑ ድረስ የምትቀበል መሆኗን ግልጽ በማድረግ ነበር በዲፕሎማሲው እስካሁን ሥትሰራ የቆየችው፡፡ የኢትዮጵያ አካሄድ በሙሉ ዝግጅትና ዲፕሎማሲ ላይ የተመሰረተ ስለሆነ ተቀባይነትንም አግኝታለች ማለት ይቻላል፡፡

የኢትዮጵያን አካሄድ ትክክል ነው ብለው የተቀበሉ ብዙ የአፍሪካ ሀገሮች አሉ፡፡ በነዚህ ሀገራት ተቀባይነት ያገኘችውም ጉዳይዋን በጥንቃቄ ይዛ በመራመዷና ማስረዳትም ስለቻለች ነው፡፡ ሲካሄዱ ለነበሩ ውይይቶችና ድርድሮች በኢትዮጵያ በኩል 153 ሰነዶች ቀርበዋል፡፡ ኢትዮጵያ በእንዲህ ያለው መልኩ በመንቀሳቀሷ የሚያሳፍራትና የጎደላትም ነገር አልነበረም፡፡ ለግድቡ ግንባታ በገንዘብ በኢትዮጵያውያን በኩል ይደረግ የነበረው ተሳትፎም ለዲፕሎማሲው ትልቅ አቅም የፈጠረ ነው፡፡ ዲፕሎማሲው ከሌሎች የሚመጣውን ጫናን ለመቋቋም ብቻ ሳይሆን፤ ስለግድቡ ሌሎች እንዲረዱት ለማድረግ በሰነድ የታገዘ፣ በተግባር የተደገፈ ሥራ በመሥራት ጭምር ነው፡፡ በዚህም በእስካሁኑ ሂደት ውጤታማ ስራ ተሰርቷል ማለት ይቻላል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የቀጣይ ዘመን የውሃ ዲፕሎማሲ ምን ገጽታ ይኖረዋል ተብሎ ይታሰባል?**

**ዶክተር ያዕቆብ፡-** እስካሁን የመጣንበት መንገድ በራሱ አመላካች ነው፡፡ ኢትዮጵያ የበርካታ ወንዞች ባለቤት ናት፡፡ ተከዜ አንድ ግድብ ብቻ ነው የተሰራለት፤ ባሮ አኮቦ ላይ ተጨማሪ ግድቦች ሊሰሩ ይገባል፡፡ ገናሌ ላይም ትልቅ ግድብ አለ፤ ዋቢሸበሌ ላይም ኃይል የሚያመነጭ መልካዋከና አለ፤ በኦሞ ጊቤ ላይም እንዲሁም አንደኛ ሁለተኛ ሶስተኛ ጊቤ እየተባለ የሚሰሩ ስራዎች አሉ፡፡ አሁን ደግሞ የኮይሻ ፕሮጀክት በግንባታ ላይ ነው፡፡ በአጠቃላይ ኢትዮጵያ በውሃ ሃብት የታደለች በመሆኗ በርካታ የልማት ሥራዎችን እየሰራች ነው፤ ወደፊትም ትሰራለች፡፡

ያለንን የውሃ ሀብት ከመሬት ጋር በሚገባ ብናስተገብራቸው ተጠቃሚነታችን ያድጋል፡፡ ተተኪው ትውልድ በተሻለ እውቀት ለአካባቢው የሚጠቅም ሥራ መሥራት ይኖርበታል፡፡ የኢትዮጵያ ልማትና የዕድገት ተስፋ በውሃ ሀብቶቿን በማልማት ላይ የሚመሠረት ነው ማለት ይቻላል፡፡

ዲፕሎማሲ ማለት፤ ትክክለኛውን ሥራ ሌሎች እንዲቀበሉ ማድረግ፤ እንዲሁም ሌሎች የሚሰሩትን ትክክለኛ ሥራ ለመቀበል ዝግጁ መሆን ነው፡፡ እዚህም እዛም ያልተስተካከለ ነገር ካለ እንዲስተካከል ማድረግ ነው፡፡ ቅቡልነቱና የጋራ ጥቅምም ከፍ እንዲል ማድረግ ነው፡፡

ስለዚህ በኢትዮጵያ በኩል ያለው የውሃ ሀብት ልማት ጉዳይ ዲፕሎማሲያችን ለአካባቢያችንም ለዓለምም ጠቃሚ መድረክና የእውቀት መስክ ስለሆነ ለወደፊት ጥሩ መሠረት ይጥላል ብዬ ነው የማስበው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በኢትዮጵያ የባሕር በር ጉዳይ የግጭት መንስኤ ሆኖ ዘመናት ተቆጥሯል፡፡ መንስኤው ምንድነው?**

**ዶክተር ያዕቆብ፡-** በታሪክ ብዙ የተጎዳንባቸው ነገሮች አሉ፡፡ ጣሊያን በኃይል ወርሮ ኢትዮጵያ ውስጥ በቆየባቸው ጊዚያቶች የባሕር በሩን ይዞ ቆይቶ ነበር፡፡ ኤርትራ የኢትዮጵያ አካል ሆና በፌዴሬሽን ከተቀላቀለች በኋላ ደግሞ፤ የባሕር በሩ የኢትዮጵያ አካል ሆነ፤ ፌዴሬሽኑ ፈርሶ ኤርትራ አንድ ጠቅላይ ግዛት ስትሆን የባሕር በሩ የኢትዮጵያ ሙሉ አካል ሆነ፡፡ ስለዚህ ኢትዮጵያ ከቀይ ባሕር ጋር ቀጥታ ግንኙነት ያላት ሀገር ነች፡፡

የኤርትራ አማጽያን፤ ጣሊያን የኤርትራን ግዛት በቅኝ በገዛበት አኳያ ነፃ ሀገር እንፈልጋለን አሉ፡፡ በዚህም የተነሳ ለ30 ዓመታት በአማጽያኑና በኢትዮጵያ መካከል ጦርነት ተካሄደ፡፡ አማጽያኑ አሸንፈው ኤርትራ ነጻ ስትሆን በወቅቱ የነበረው የኢትዮጵያ አገዛዝ ወይንም ኢትዮጵያን ያስተዳድራት የነበረው ሕዘባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ (ሕወሓት) ድርድር ሳያደርግ፣ ለኢትዮጵያ ጥቅም መቆም ሲገባው ይህን ባለማድረጉ ኢትዮጵያ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የባሕር በር ሳይኖራት ቀርቷል፡፡

ችግሩ እስካሁን ቀጥሏል፡፡ እንዴት ነው የባሕር በር የምናገኘው የሚለው ጉዳይ ብዙ ሥራ ይጠይቃል፡፡ የጥናት ሥራም ይፈልጋል፡፡ ብዙ አዋቂዎች፣ የፖሊሲ ሰዎች ተሳትፎ ያስፈልጋል፡፡ ይህም ከኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ከዚያኛውም ወገን ተሳትፎ መኖር አለበት፡፡ ከፍተኛ የዲፕሎማሲ ሥራ ይጠይቃል፡፡

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ሰጥቶ መቀበል ብለዋል፡፡ ሰጥቶ መቀበል ተቀባይነት እንዲኖረውና ሂደቱም ሰላማዊ ሆኖ እንዲጠናቀቅ በደንብ መግባባትን የሚጠይቅ ጉዳይ ነው፡፡ እንደዋዛ የሚታይ ጉዳይ ነው ብዬ በግሌ አላምንም፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በዚህ ወቅት ኢትዮጵያ የባሕር በር ጉዳይን አጥብቃ ይዛለች፡፡ በዚህ ላይም ሀሳብ ቢሰጡን፤**

**ዶክተር ያዕቆብ፡-** ኢትዮጵያ ከጥንት ጀምሮ ወደ ባሕር በር ነው ግንባሯ ያለው፡፡ ባሕር በር በነበራት ጊዜ ከልካይ አልነበራትም፡፡ በአሰብም በምጽዋም እቃዋንም፣ድርጅቷንም ሚስጥሯንም፣ ወደ ውጭ ለመላክም ሆነ ከውጭ ለመቀበል መንገዱም ሉዓላዊነቱም ነበራት፡፡ ነገር ግን በመካከል ላይ በተነሳ የአማጺ ነፃነት ንቅናቄ ለረጅም ጊዜ ጦርነት ተካሂዶ ኤርትራ ነፃ ወጣች ሲባል ድርድር ሳይደረግ እንደማናቸውም ተራ ነገር ኤርትራ የባሕር በሩን ይዛ እንድትሄድ መንገድ ተከፈተላት፡፡

አሁን እንግዲህ አቀበቱን እያረፍንም፣ እየተነፈስንም ቢሆን መወጣት ያለብን ይመስለኛል፡፡ እኔ እንደ አንድ ሙህርና መምህር አሁንም ደግሜ የምለው ከፍተኛ የሆነ የዲፕሎማሲ ሥራ ይጠይቃል፡፡

የታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ግንባታ ሥራ ሲጀምር ለባላንጦቻችንም ሆነ ለሶስተኛ ወገኖች ለማስረዳት ብዙ ዝግጅት ተደርጓል፡፡ ብዙ ሀሳብና እውቀት አንድ ላይ በማድረግ የተለያዩ ሂደቶችን በማለፍ ነው አሁን ግድቡ የደረሰበት ደረጃ ላይ ማድረስ የተቻለው፡፡ ይሄ ጥሩ ተሞክሮ መሆኑ እየታየና ምስክርነትም እያስገኘ ነው፡፡

ኢትዮጵያ የባሕር በሯን እንድታጣ ተደርጓል፡፡ ይህም ትልቅ ስህተት ነው፡፡ አንድ ሀገርን የሚያስተዳድር መንግሥት ትልቁ የመጀመሪያ ሥራው መሆን ያለበት ለሀገር የሚጠቅም ነገር በዲፕሎማሲም ሆነ በሌላ ዘዴ ተጠቅሞ የሀገርን ጥቅም ማስጠበቅ ነበር፡፡ ነገር ግን በስንፍናም፣ በእውቀት ማነስም፣ በሸፍጥም ይሁን በሌላ ጥፋት ተሰርቷል፡፡ ሳንወድ የዚያ እዳ ተሸካሚ ሆነናል፤ ይሄንን መቀበል ያስቸግር ይሆናል። የተበላሸውን ነገር ለማስተካከል ትዕግሥትና ጥበብ ያስፈልጋል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- እርስዎ እንዳሉት ኢትዮጵያ የባሕር በሯን ለማስመለስ ጥንቃቄ፣ትዕግሥት የተሞላበት በሳል የዲፕሎማሲ ሥራ ያስፈልጋታል፡፡ በዚህ ረገድ ከማን ምን ይጠበቃል?**

**ዶክተር ያዕቆብ፡-** መንግሥት ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛል፡፡ ምክንያቱም ሀገርን ተጠቃሚ በሚያደርግ መንገድ ነገሩ በደንብ እንዲሳለጥ መንግሥት ዕውቀትን ገንዘብንና ሕዝብን በማደራጀቱና በማስተባበሩ በኩል ጠንክሮ መሥራት ይኖርበታል፡፡ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከባሕር በር ጋር የተገናኘ ሥራ የሚሰሩ መንግሥታዊ ተቋማት አሉ።ለዚህ እውቀትም ዝግጅትም አለኝ የሚሉ አካላት በጉዳዩ ላይ በንቃት እንዲሳተፉ ማድረግ ይገባል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ በአባይ እና በቀይ ባሕር መካከል መገኘቷ እንደጥቅምና እንደተግዳሮት የሚነሳ ነገር ካለ ቢያብራሩልን?**

**ዶክተር ያዕቆብ፡-** አባይና የአባይ ገባሮች 86 በመቶ የሚሆነው ውሃ ጥቅም ላይ የሚውለው ለሱዳንና ለግብጽ ነው፡፡ በዚህም እነርሱ ውሃችንን አትንኩ ይላሉ፡፡ እኛ ደግሞ የጋራ ነው እንላለን፡፡ ሆኖም ለልማት ከማዋል ወደኋላ አንልም፣ ሉዓላዊ ግዛታችን ውስጥ የሚገኝ ውሃ ከመጠቀም የሚከለክል አንዳች ኃይል የለብንም ስንል ኖረናል፡፡

ይሄ በዲፕሎማሲ ትልቅ ተግዳሮት ሆኖ ቆይቷል። አሁን እውቀታች፣ አቅማችን፣ፍላጎታችንና ለልማት ያለን ቁርጠኝነትም ከፍ እያለ ሲሄድ ከ60 ዓመት በፊት የተጀመረውን እቅዳችችን ለመተግበር ትንሽ በትንሽ በመንቀሳቀስ ላይ እንገኛለን፡፡

ከነበሩት 33 ፕሮጀክቶች መካከል 10ሩ እንኳን ገና ሥራ ላይ አልዋሉም፡፡ ግን ሰርተን በማሳየት ተግዳሮቶችን እየተቋቋምናቸው እንገኛለን፡፡ እንደአያያዛችን ብዙ እንሰራለን ብዬ አስባለሁ፡፡ አቅማችንና አሰራራችን እያደገ ሲሄድ የታቀዱትን ብቻ ሳይሆን አዳዲስ እቅዶችንም ጨምረን እንሰራለን ብዬ አምናለሁ፡፡ ተግዳሮቶችን እየቀነስን ጥቅማችንን እያሳደግን ከሄድን ኢትዮጵያ በቀይ ባሕርና በአባይ ተፋሰስ መሃል መገኘቷ የራሱ የሆነ ጥቅም ያለው ነው፡፡ የእድገትም ምንጭ ነው፡፡

የባሕር በር ጉዳይን በተመለከተ የታሪክ ተመራማሪዎች ብዙ ነገር ሊነግሩን ይችላሉ፡፡ በቅርቡም ያየነው የቅኝ ግዛት ሥርዓት በመላ አፍሪካ ላይ የተጫነ ነበር፡፡ ኢትዮጵያ ቅኝ ተገዥ ባትሆንም የቅኝ ግዛት ጠባሳው አላረፈባትም ማለት አይቻልም፡፡ የኤርትራ ጉዳይም የሚያያዘውም ከዚሁ ጋር ነው፡፡ ከብዙ ድካም በኋላ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን እንድትተዳደር ተደረገ፡፡

በፌዴሬሽን መሆኑ ለኢትዮጵያም የሚጠቅም ነበር። ለኤርትራም ወገኖች የሚጠቅም ነበር፡፡ በኋላ ደግሞ የጂኦፖለቲካ ተጽዕኖን በመሥጋት የኢትዮጵያ መንግሥት ኤርትራን ከፌዴሬሽን የበለጠ የተዋሀደች ሀገር ትሁን በማለት ተንቀሳቀሰ፡፡ እናት ሀገር ወይንም ሞት የሚሉ ኤርትራውያን ከዚህ ጋር አብረው ከኢትዮጵያ መንግሥትና ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር ተባብረው ኤርትራ 14ኛ ጠቅላይ ግዛት ልትሆን ቻለች፡፡ ያንን በመቃወም ደግሞ አማጽያን ተነስተው ለ30 ዓመታት ጦርነት ተካሄደ፡፡ ከዚያ በኋላ ኢትዮጵያ በተዳከመች ጊዜ ኤርትራ ነፃ ሀገር መሆኗን አወጀች፡፡ በዚህ ሁኔታ ነው እንግዲህ እንደዋዛ ኢትዮጵያ የባሕርበር ያጣችው፡፡ ይሄ በታሪክ እንደ ስህተት ይወሰዳል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ስለሰጡን ማብራሪያ አመሰግናለሁ።**

**ዶክተር ያዕቆብ፡** እኔም አመሰግናለሁ፡፡

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

## የአግሮ ኢንዱስትሪ ፓርኩና የኩባንያዎቹ የዝግጅት ሥራዎች

አንተነህ ቸሬ

የኢትዮጵያን መዋቅራዊ የምጣኔ ሀብት ሽግግር እውን ለማድረግ አስተዋፅኦ ይኖራቸዋል ተብለው ትኩረት ከተሰጣቸው ተግባራት መካከል የኢንዱስትሪ ፓርኮች (Industrial Parks) ልማት አንዱ ነው፡፡ የኢንዱስትሪ ፓርኮቹ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት የመሳብ፣ የሥራ ዕድል ፈጠራን የማስፋት እና የቴክኖሎጂ ሽግግርን እውን የማድረግ ዋና ዋና መሠረታዊ ተልዕኮዎችም አሏቸው፡፡ ፓርኮቹ በሚገነቡባቸው አካባቢዎች ለሚኖረው የኅብረተሰብ ክፍል ሥራ በመፍጠርና ከአካባቢ ጋር ተስማሚ የሆነ የሥራ ከባቢ እውን በማድረግ ለሀገራዊ የምጣኔ ሀብት እድገት ትልቅ አስተዋፅዖ ይኖራቸዋል፡፡

የኢንዱስትሪ ፓርኮችን ተመራጭ ከሚያደርጓቸው መካከል በርካታ አገልግሎቶችን አንድ ሥፍራ ላይ ሰብሰብ አድርገው የሚያቀርቡ መሆናቸው፣ ተገቢ መሠረተ ልማት የሚገነባላቸው እንዲሁም ከሌሎች አምራቾች ጋርም የሚያገናኙ መሆናቸው ይጠቀሳሉ፡፡ ከዚህ አኳያ በኢትዮጵያም ብዙ የኢንዱስትሪ ፓርኮችን በማቋቋም እንዲሁም በአንፃራዊነት ዝቅተኛ ዋጋ የሚከፍልበትን የኤሌክትሪክ አገልግሎት አቅርቦት፣ ማሽኖችን ከቀረጥ ነፃ ማስገባትን፣ የብድር አቅርቦትን፣ የአንድ ማዕከል አገልግሎትን እና የመሠረተ ልማት ግንባታዎችን እንደማበረታቻ በማቅረብ ትልልቅ ዓለም አቀፍ ኩባንያዎች ፋብሪካዎቻቸውን ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲከፍቱ ጥረቶች ተደርገዋል፡፡

በእርግጥም ኢትዮጵያ የአፍሪካ የማምረቻ መናኸሪያ (Manufacturing Hub) እንድትሆን የሚደረገውን ጥረት ለማቀላጠፍ እንዲሁም የሥራ አጥነት ችግርን ለመቅረፍ ላቅ ያለ ሚና ይጫወታል ተብሎ ተስፋ የተጣለበት የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ውጤቶች ተገኝተውበታል፡፡ በተለይም ኢንዱስትሪ ፓርኮቹ ለበርካታ ዜጎች የሥራ ዕድሎችን በመፍጠር ቀላል የማይባል አስተዋፅዖ አበርክተዋል፡፡ በአሁኑ ወቅት በመላ ሀገሪቱ 13 የኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚገኙ ሲሆን፣ በሥራ ዕድል ፈጠራ፣ በውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትና በቴክኖሎጂ ሽግግር ለሀገራዊ ምጣኔ ሀብት እድገት ቀላል የማይባል አስተዋፅዖ እያበረከቱ ይገኛሉ፡፡

በተለይም የግብርና ውጤቶችን እሴት በመጨመር በብዛትና በጥራት ተወዳዳሪ የማድረግ አቅም እንዳላቸው የታመነባቸው የተቀናጁ የግብርና ምርቶች ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ ፓርኮች (Integrated Agro-Industry Parks)፣ የግብርናውን ዘርፍ በማዘመን መዋቅራዊ የምጣኔ ሀብት ሽግግርን ያሳካሉ ከተባሉ የኢንዱስትሪ ፓርክ ዘርፎች መካከል በቀዳሚነት ይጠቀሳሉ፡፡

እነዚህ የአግሮ-ኢንዱስትሪ ፓርኮች ለአርሶ አደሮች የግብይት ሰንሰለቱን ቀላል በማድረግ አርሶ አደሮችን ተጠቃሚ የሚያደርግ የገበያ ትስስር ይፈጥራሉ፡፡ ባለሀብቶች የግብርና ግብዓቶችን ከአርሶ አደሮች እንዲቀበሉ በማድረግ አርሶ አደሮች የልፋታቸውን ያህል እንዲጠቀሙ አወንታዊ አስተዋፅዖ ያበረክታሉ፡፡ መንግሥት አግሮ-ኢንዱስትሪ ፓርኮችን ለመገንባት እስካሁን ድረስ ከ30 ቢሊዮን ብር በላይ ወጪ ማድረጉንና ይህ ወጪ ባለሀብቶች በፓርኮቹ ውስጥ ገብተው በምርት ሥራዎች ላይ እንዲሰማሩ ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር እንደሆነ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

በኦሮሚያ ክልል፣ ምሥራቅ ሸዋ ዞን፣ አዳሚ ቱሉ ጂዶ ኮምቦልቻ ወረዳ፣ ከባቱ ከተማ በ16 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኘው የ‹‹ቡልቡላ የተቀናጀ አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርክ›› በሀገሪቱ ከተገነቡ የተቀናጁ የግብርና ምርቶች ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ ፓርኮች መካከል አንዱ ነው፡፡ ፓርኩ በሚያዝያ ወር 2013 ዓ.ም በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ የተመረቀ ሲሆን የአትክልትና ፍራፍሬ፣ የወተት፣ የማር፣ የስጋና የእንቁላል ምርቶችን የሚያቀነባብሩ አምራቾች የሚሰማሩበት የኢንዱስትሪ ፓርክ ነው፡፡

የፓርኩ የመጀመሪያ ዙር ግንባታ በ271 ሄክታር መሬት ላይ ያረፈ ሲሆን፣ እስከ አንድ ሺ ሄክታር መሬት መሸፈን የሚችል ቀጣይ ዙር ግንባታ ሊከናወንለት እንደሚችል የፓርኩ የአዋጭነት ጥናት ያሳያል፡፡ በመጀመሪያ ምዕራፍ ግንባታው 148 ባለሀብቶችን ማስተናገድ ይችላል፤ በሙሉ አቅሙ ወደ ሥራ ሲገባ ከ70 ሺ እስከ 100 ሺ ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ ዕድል ይፈጥራል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ ባለሀብቶች ወደ ፓርኩ ገብተው እንዲሠሩ የፓርኩን ገፅታና አቅም ለባለሀብቶች የማስተዋወቅ መርሃ ግብር በወርሃ ነሐሴ 2014 ዓ.ም በአዲስ አበባ መካሄዱና በወቅቱም ከ40 በላይ ባለሀብቶች በፓርኩ ለመሰማራት ቃል መግባታቸው ይታወሳል፡፡

በኦሮሚያ ክልል ኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን የሕዝብ ግንኙነት ባለሙያ አቶ ጌታሁን አዱኛ እንደሚናገሩት፣ የቡልቡላ የተቀናጀ አግሮ-ኢንዱስትሪ ፓርክ ባለሀብቶችን ተቀብሎ ለማስተናገድ ባከናወናቸው ተግባራት ፈቃድ የወሰዱ 29 ኩባንያዎች ወደ ፓርኩ ገብተው በግብርና ምርቶች ማቀነባበር ሥራ ላይ ለመሰማራት የሚያስችሏቸውን የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች እያከናወኑ ይገኛሉ፡፡ ባለሀብቶቹ የሚሰማሩባቸው የአግሮ-ፕሮሰሲንግ (ግብርና ማቀነባበር) ዘርፎች የማርና ሰም፣ የምግብ ዘይት፣ የአትክልትና ፍራፍሬ (ቲማቲም፣ ድንች፣ ጭማቂ… )፣ የቡና፣ የአቮካዶ ዘይት፣ የስጋ፣ የወተት፣ የእንስሳት መኖ፣ የፓስታና ማካሮኒ፣ የሕፃናት ምግቦች ማምረትና ማቀነባበር ሥራዎች ናቸው፡፡

እንደ አቶ ጌታሁን ማብራሪያ፤ በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ ሩብ ዓመት አራት ባለሀብቶችን ወደ ፓርኩ ለማስገባት ታቅዶ ለሰባት ባለሀብቶች ፈቃድ መስጠት ተችሏል፡፡ ባለሀብቶቹ በምግብ ዘይት ምርት እንዲሁም በስጋ እና አትክልትና ፍራፍሬ ማቀነባበር ዘርፎች የሚሰማሩ ናቸው፡፡ ፈቃድ ከተሰጣቸው ኩባንያዎች መካከል ‹‹ቲኬ ግሩፕ›› (TK Group) የተባለ ኩባንያ ሼድ ገንብቶ የማሽን ተከላ ሥራ እያከናወነ ይገኛል፡፡ ኩባንያው በምግብ ዘይት እና በእንስሳት መኖ ምርትና ማቀነባበር ሥራ ላይ የሚሰማራ ሲሆን፣ ለሥራውም ሁለት ነጥብ ስምንት ሄክታር መሬት ተረክቧል፡፡ ከሁለት ወራት ባልበለጠ ጊዜ ምርት ማምረት ይጀምራል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

ሌሎቹ ድርጅቶች ደግሞ መሬት ተረክበው የባንክ ብድር ለማግኘት እየተንቀሳቀሱ ይገኛሉ። አንዳንዶቹም የባንክ ብድር ተፈቅዶላቸው ማሽን ማስገባት ጀምረዋል፡፡ ለአብነት ያህል መንግሥት ለናሙና ወደገነባቸው ስድስት ሼዶች ውስጥ ከገቡት አምራቾች መካከል ሁለቱ የብድር ፈቃድ ሂደቶችን አጠናቅቀው ማሽኖችን እያስገቡ ይገኛሉ። ወደ ፓርኩ ገብተው ሥራ ለመጀመር ፈቃድ ከወሰዱት ባለሀብቶች መካከል አብዛኞቹ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች መሆናቸውንም አቶ ጌታሁን ይናገራሉ፡፡

የመሠረተ ልማት አቅርቦትን በተመለከተ ‹‹ፓርኩ የመሠረተ ልማት አገልግሎቶች የተሟሉለት ነው፡፡ የመንገድ፣ የመብራት፣ የቴሌኮም፣ የአንድ ማዕከል አገልግሎቶች አሉት፡፡ ለሁሉም ፓርኮች የመብራት ሰብስቴሽኖችን የሚገነባው የፌዴራል መንግሥት ነው፡፡ የሰብስቴሽን ግንባታ ስለዘገየብን ከ35 ሜጋዋት በላይ ኃይል ከአካባቢው በመሳብ ፈቃድ የወሰዱት ባለሀብቶች የዝግጅት ሥራዎቻቸውን እንዲቀጥሉ አድርገናል፡፡ በውሃ አቅርቦት ረገድ ደግሞ፣ በአካባቢው ያለው ውሃ ጨዋማ ነው፡፡ ውሃውን ለማጣራት ከፍተኛ ገንዘብ ይጠይቃል፡፡ ስለሆነም ከፓርኩ ከ50 ኪሎ ሜትር ርቀት በላይ በመጓዝ በጢዮ ወረዳ (አርሲ) አምስት የውሃ ጉድጓዶችን ለመቆፈር ታቅዶ ሦስቱ እንዲቆፈሩ ተደርጓል፤ መስመር የመዘርጋት ሥራም ተጀምሮ ነበር፡፡ በአንዳንድ ችግሮች ምክንያት ሥራው እንዳይስተጓጎል ለተወሰነ ጊዜ ከባቱ ከተማ ወደ ፓርኩ ውሃ ለማስገባት ታቅዷል›› በማለት ይገልፃሉ፡፡

> **ከፓርኩ ጋር ትስስር ያላቸውና ግንባታቸው የተጠናቀቀ ስድስት የገጠር ሽግግር ማዕከላት ያሉ ሲሆን፣ የማዕከላቱ ዋና ተግባር የአርሶ አደሩን ምርት በጥራትና በብዛት ሰብስቦ ለፓርኩ አምራቾች ማቅረብ ነው፡፡ ወደ ፓርኩ የሚገቡት ባለሀብቶች ከሽግግር ማዕከላቱ ጋር በሚፈጥሩት ትስስር አርሶ አደሩን ጨምሮ የአካባቢው ኅብረተሰብ ተጠቃሚ ይሆናል**

እንደ አቶ ጌታሁን ገለፃ፣ ከፓርኩ ጋር ትስስር ያላቸውና ግንባታቸው የተጠናቀቀ ስድስት የገጠር ሽግግር ማዕከላት ያሉ ሲሆን፤ የማዕከላቱ ዋና ተግባር የአርሶ አደሩን ምርት በጥራትና በብዛት ሰብስቦ ለፓርኩ አምራቾች ማቅረብ ነው፡፡ ወደ ፓርኩ የሚገቡት ባለሀብቶች ከሽግግር ማዕከላቱ ጋር በሚፈጥሩት ትስስር አርሶ አደሩን ጨምሮ የአካባቢው ኅብረተሰብ ተጠቃሚ ይሆናል። በሻሸመኔ፣ መቂ፣ ዶዶላ፣ ባሌ ሮቤ፣ ኢተያ እና ኦለንጪቲ ከሚገኙት ማዕከላት መካከል የሻሸመኔና የመቂ ማዕከላት የመሠረተ ልማት ግንባታዎቻቸው ጭምር ተጠናቀዋል፡፡ አራቱ ማዕከላት ደግሞ የሕንፃ ግንባታቸውን አጠናቀው መሠረተ ልማቶችን (ውሃ፣ መብራት፣ መንገድ…) የማሟላት ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ፡፡ በበጀት ዓመቱ ሁለተኛ ሩብ ዓመት ማጠናቀቂያ የሁሉንም ማዕከላት ግንባታና የመሠረተ ልማት አቅርቦት ሥራዎች ለማጠናቀቅ ታቅዶ እየተሠራ ይገኛል፡፡

የፓርኩ ግንባታ ብዙ የሰው ኃይልና ግብዓት ይፈልግ እንደነበር አቶ ጌታሁን ጠቅሰው፣ በፓርኩ ግንባታ ወቅት በርካታ የአካባቢው ኅብረተሰብ ተጠቃሚ እንደነበርም ጠቅሰዋል፡፡ አምራቾች ሥራ ሲጀምሩ ደግሞ የአካባቢው አርሶ አደሮች ለፓርኩ የግብርና ግብዓቶችን በማቅረብ ተጠቃሚ እንደሚሆኑም ያስረዳሉ፡፡

‹‹ፓርኩ በጥናት ላይ ተመስርቶ ሲገነባ ያስገኛል ተብሎ የታሰበው ዋና ጥቅም የአርሶ አደሩን ምርት በጥራትና በመጠን በመጨመር እንዲሁም የገበያ ዕድል በመፍጠር አርሶ አደሩን ተጠቃሚ ማድረግ ነው፡፡›› ያሉት አቶ ጌታሁን፤ አሁን ባለሀብቶች ገና ወደ ፓርኩ ለመግባት በዝግጅት ላይ በመሆናቸው ስለአርሶ አደሩ ሰፊ ተጠቃሚነት ለመናገር ጊዜው ገና ነው ብለዋል፡፡ በቅርቡ ወደ ሥራ እንደሚገባ የሚጠበቀው ‹‹ቲኬ ግሩፕ›› ዘይት የሚያመርተው ከአኩሪ አተር መሆኑን ጠቅሰው፣ ለምርቱ የሚያስፈልገውን ግብዓት (አኩሪ አተር) እየሰበሰበ እንደሚገኝና በዚህም አኩሪ አተር አምራች አርሶ አደሮች ተጠቃሚ እየሆኑ እንደሚገኙ አስታውቀዋል፡፡

በተጨማሪም ‹‹የቡልቡላ የተቀናጀ አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርክ የግብርውን ዘርፍ ለማሳደግ ታልሞ የተገነባ በመሆኑ የሚጠቀመው ግብዓት የሀገር ውስጥ የግብርና ምርቶችን ነው፡፡ በፓርኩ አካባቢ ያለው ማኅበረሰብ አርሶ አደር ነው። የፓርኩ አምራቾች የሚጠቀሙት ጥሬ ዕቃ የአካባቢውን የግብርና ምርት ነው፡፡ አርሶ አደሩ ግብርናውን በማዘመንና አምራችነቱን በመጨመር ለምግብና ለገበያ ከሚያውለው ምርት በተጨማሪ ለኢንዱስትሪ ግብዓት የሚሆን ትርፍ ምርት እንዲያመርት እየተሠራ ነው፡፡ በቀጣይ አምራቾች በማር፣ በስጋ፣ በዶሮ፣ በወተት፣ በጥራጥሬ፣ በዘይትና በሌሎች ዘርፎች ወደ ሥራ ሲገቡ አርሶ አደሩ ይበልጥ ተጠቃሚ ይሆናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርት በመተካት የአካባቢው ኅብረተሰብ የገበያ ዕድል እንዲያገኝም ያደርጋል›› በማለት ፓርኩ ለአካባቢው ኅብረተሰብ ተጠቃሚነት ያለውን ፋይዳ ያስረዳሉ፡፡

የሀገሪቱን የምጣኔ ሀብት መዋቅር ከእርሻ መር ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ ለማሸጋገር የሚያግዙ በርካታ መልካም አጋጣሚዎችና ዕድሎች አሉ፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህን መልካም አጋጣሚዎች በመጠቀም የኢኮኖሚውን መዋቅራዊ ሽግግር ለማሳካት የተከናወኑ ተግባራት ሀገሪቱ ካላት አቅምና ፍላጎት ጋር ተመጣጣኝ አይደሉም፡፡ ኢትዮጵያ በኢንዱስትሪ ያላትን አቅም በመጠቀምና ከዚሁ ዘርፍ የሚገኘውን ገቢ በማሳደግ ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ የምታደርገውን መዋቅራዊ የምጣኔ ሀብት ሽግግር ለማሳካት አምራች ዘርፉ አሁን ካለው አፈፃፀም በብዙ እጥፍ እንዲጨምርና እንዲሻሻል ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

የአምራች ዘርፉ እድገት ሊሻሻል የሚችለው ከኢንቨስትመንት መስፋፋት ጋር ተያይዞ ነው። የኢንዱስትሪ ፓርኮች ደግሞ የአንድ ማዕከል አገልግሎትን ተግባራዊ በማድረግ ለኢንቨስትመንት መስፋፋት ምቹ ሁኔታዎችን የሚፈጥሩ ናቸው። ስለሆነም መዋቅራዊ የምጣኔ ሀብት ሽግግሩን ለማሳካት የኢንዱስትሪ ፓርኮችን አፈፃፀም ማሻሻል ይገባል፡፡ ይህም ባለሀብቶች ወደ ፓርኮቹ ገብተው ለማምረት የሚያስችሏቸውን የመሠረተ ልማት ግብዓቶች፣ የሰለጠነ የሰው ኃይልና የፋይናንስ አቅርቦት ማሟላትን እንደሚያካትት ሊታወቅ ይገባል፡፡

# ጎሜ

# ከመገዳደል መገዳደር

**የፈኔት እናት**

የኅዳር ወር ንፋስ በርትቷል፡፡ ልክ እንደድሮ ጥቅምት፤ ውርጩ ፊት ይለበልባል፡፡ ቀኑን ሙሉ ቢሮ ውስጥ ተቀምጠው የሚውሉት ዘውዴ መታፈሪያ፣ ገብረየስ ገብረማርያም እና ተሰማ መንግስቴ የቀትር ፀሐይ ሳያሞቃቸው ውለዋል። እንደለመዱት አመሻሽ ላይ በቢራ ለመሟሟቅ ማምሻ ግሮሰሪ ተገናኙ፡፡ ሦስቱም በአንድ ጠረጴዛ ዙሪያ ሰፍረው የሚጠጡትን አዘው ጨዋታ ጀመሩ። የዛሬው ትልቁ አጀንዳቸው ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ባደረጉት ንግግር ላይ የተመሠረተ ነበር፡፡

ተሰማ ፊቱ ላይ የተለየ ደስታ ይነበባል። የጠቅላይ ሚኒስትሩ ንግግር ያረካው ይመስላል። ገብረየስ እና ዘውዴ ግን ብዙም ለውጥ አይታይባቸውም። እንደለመደባቸው ዘወትር የሚታይባቸው የተለመደ ዓይነት ስሜት ነበር፡፡ አልሞቃቸውም፤ አልበረዳቸውም፡፡ አልከፋቸውም፤ አልተደሰቱም፡፡ ዕለቱ ከሌላው ቀን የተለየ አልሆነላቸውም፡፡

ተሰማ ውስጡ ያለው ደስታ እየተናነቀው፤ « ዛሬ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ንግግር በተለይ ‹እኛ እይታችን ሀገራዊ ነው› ብለው አስረግጠው መናገራቸው በጣም አስደስቶኛል። በትክክልም ‹ኢትዮጵያ ከሁሉም ጫፍ ያሉ ዜጎቿ፤ በእኩል በነፃነት የሚኖሩባት፤ ሁሉ እምነት የሚከበርባት፤ ሁሉም ቋንቋ ሁሉ ባህል የሚከበርባት፤ የጎላች ያማረች የበለፀገች ሀገር የምትፈጥርበትን መንገድ እንሻለን።› ማለታቸው ማንኛውም ጤነኛ አስተሳሰብ ያለው ሰው ይደግፈዋል፤ ይህም ያስደስተዋል ብዬ አምናለሁ፡፡» አለ፡፡ ተሰማ ይህንን ሲናገር ገብረየስ እና ዘውዴ እንዴት እየተመለከቱት እንደነበር አላስተዋለም፡፡ ሁለቱም ዝም አሉ፡፡

ተሰማ ምላሽ ሳይሰጡት ቢቀሩም፤ ምንም አልመሰለውም፡፡ ያስደሰተውን የጠቅላይ ሚኒስትሩን ንግግር እየመዘዘ ለማስረዳት መሞከሩን ቀጠለ፡፡ «ሁላችንም ወንድማማቾች መሆናችንን የገለፁበት መንገድ ‹ የኢትዮጵያ መሠረት እያንዳንዱ ዜጋ ነው። ያ ዜጋ በጊዜ ሂደት ውስጥ ቋንቋና ባህል ቢያዳብርም፤ የራሱ እምነት ቢኖረውም፤ ሲጀመር ግን ያው ሰው ነበር። ኦሮሞ የሚባል አንድ ሰው ነበር፤ ሲዋለድ ኦሮሞን የሚያክል ብሔር ፈጠረ፡፡ አማራ የሚባል ወይም ከአማራ አካባቢ የተነሳ አንድ ሰው ነበር፤ ሲዋለድ አማራን ፈጠራ፤ እንጂ ሲጀመር ጀምሮ ኦሮሞ የሚባል ብሔር ወይም አማራ የሚባል ብሔር የለም፡፡

አንድ ሰው በጊዜ ብዛት አንድ ቤተሰብ መሠረተ፤ የቤተሰብ ብዜት ውጤት ወደ ብሔር አደገ። ይሄ የሚያሳየው መሠረታችን ሰው መሆኑን ነው።› የሚለው ገለፃቸው እጅግ አስደስቶኛል። ‹ስለዚህ ሁላችንም ሰው ነን፡፡ ያዳበርነው ቋንቋ ማንነትና በጊዜ ብዛት የገነባነው ቤተሰብ ቢኖረንም ሁላችንም መሠረታችን አንድ ነው፡፡› ማለታቸው እኔ እና እናንተ ምንም ሊያጋጨን የሚገባ ነገር የለም ማለት ነው፡፡» አለ፡፡

ገብረየስ ቀበል አድርጎ ለተሰማ « እምንባላውና የምንጋጨውማ ብልህ ያሙቱን ሞኝ የዕለቱን የሚለውን ብሂል ረስተነው ነው፡፡ የምናየው የፊት የፊታችንን የዕለቱን ብቻ ነው፡፡ ሁላችንም እኩል ሰው መሆናችንን ዘንግተን፤ ሌሎች ሰዎች እንዳልሆኑ ለመነጠል፤ ለመለየት እና ለማጥፋት እንሞክራለን፡፡ በትክክል ማንም ላስተውል ብሎ ዓይኑን ገልፆ ልቡን ከፍቶ የተመለከተ ሰው በደንብ ካሰላሰለ የሚያጋጭና የሚያባላው ምንም ነገር የለም፡፡ በእርግጥም አንድ ሰው ቤተሰቡን የመጠበቅ ኃላፊነት አለበት፡፡ ነገር ግን ያ ኃላፊነት

> ሁሉም አንድ ቤተሰብ ነው፡፡ አንዱ በሌላው ላይ ተነስቶ፤ ሌላውን ለመግደልም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለማጥፋት ቢሞክር ድሉ ጊዜያዊ ነው፡፡ ድሉ ዘላቂ መሆን አይችልም። ዘላቂ ውጤት የሚገኘው በጦርነት ሳይሆን በሰላማዊ መንገድ ነው

ሰዎችን እስከ ማጥፋት የዘለቀ ሊሆን አይገባም፡፡ ይህን ማድረግ ማለት ዛሬ ቤተሰቤን እጠብቃለሁ ብሎ የሌላውን ቤተሰብ ያጠፋ ሰው ነገ የእርሱም ቤተሰብ የሚጠፋ መሆኑን መገንዘብ አለበት። የዕለት የዕለቱን እያሰበ ሲንገበገብ ዛሬውን እያበላሸ፤ ነገውን ያደበዝዛል» አለ፡፡

ዘውዴ ምንም አልተነፈሰም፤ ሁለቱም ተራ በተራ ሲናገሩ ያዳምጣል፡፡ በዛው በደስታ ስሜት ውስጥ እየዋኘ ያለው ተሰማ ገብረየስን በመደገፍ ቀጠል አድርጎ «ትክክል ብለሃል፤ ሁሉም አንድ ቤተሰብ ነው፡፡ አንዱ በሌላው ላይ ተነስቶ፤ ሌላውን ለመግደልም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለማጥፋት ቢሞክር ድሉ ጊዜያዊ ነው፡፡ ድሉ ዘላቂ መሆን አይችልም፡፡ ዘላቂ ውጤት የሚገኘው በጦርነት ሳይሆን በሰላም ነው። በእርግጥም ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዳሉት ሁሉ፤ ‹ ለእኛ የቸገረን ነገር ሰላም ነው።› ሰላም ጠምቶናል። ሰላም ሆነን ብንሠራ በእዚህ ጊዜ ከእዚህ የተሻለ ደረጃ ላይ እንደርስ ነበር፡፡» አለ፡፡

ዘውዴ እንደተቀመጠ ትንሽ ተነቃንቆ ጉሮሮውን ከጠራረገ በኋላ በጎርናና ድምፅ፤ «በደመና ጊዜ ስለመብረቅ አይወራም፡፡ ለሚወራውም ቀን ያስፈልገዋል፡፡ ያለበለዚያ መአት መጥራት ነው፡፡ የጠሩት መዓት ቢዘገይም አይቀርም፡፡ ከአፍ የወጣ ከጥርስ የነጣ እንደሚባለው ሁሉ፤ ሰላም ከፈለግን ሰላማዊ መንገድን እንደዋነኛ አማራጭ መውሰድ አለብን። በእርግጥ የሁሉም ሕዝብ ምኞት ሰላም ነው። ሕዝቡ ሰላም እና ልማት ይፈልጋል፤ ድህነት እንዲቀንስ ይፈልጋል፡፡ ኢትዮጵያ ከችግር እንድትገላገል ይፈልጋል፡፡ ዴሞክራሲ እንዲገነባ ይፈልጋል፡፡ ተቋማት እንዲገነቡ ይፈልጋል፡፡ ጦርነት የሚፈልገው ማን ነው? ይህንን በደንብ አጥርቶ መለየት ይገባል፡፡ በእርግጥም በፍፁም ሕዝብ ጦርነት አይፈልግም፡፡ » አለ፡፡

ተሰማ እንደተለመደው ዘውዴን መቃወም ጀመረ፤ «ትክክል ነህ! ሕዝብ ተጠቅሎ መሰደብ የለበትም፡፡ ሕዝብ ጦርነት ይፈልጋል ማለት አይቻልም፡፡ ነገር ግን ጥያቄ አለኝ፡፡ በእርግጥ ሕዝብ ጦርነት አይፈልግም? ነገር ግን መካድ የማይቻል አንድ ነገር አለ፡፡ ኢትዮጵያውያን በጇ ብለው መንግሥት ነው ብለው ተቀብለው አብረው የኖሩለት ደግፈው ያበረቱት መንግሥት አለ ብሎ ለመከራከር ብዙ ምርምርን ይጠይቃል፡፡ ሁሌም ግጭት የሚመስል ነገር አለ፡፡ መጠኑ ምን ያህል ነበር? የሚለው ላይ መነጋገር ይቻላል፡፡ ነገር ግን ይብዛም ይነስም፤ ከመንግሥት ጋር መታገልን እኛ ኢትዮጵያውያን በተደጋጋሚ የምንፈፅመው ጉዳይ ነው፡፡ አባት ያቆየው ለልጅ ይበጀው። የሚባለው በጎ ነገር ሲቀመጥ ነው፡፡ እኛ ጋር ደግሞ መጥፎ ልማድ በመቀመጡ አባት ያቆየው ለልጅ አይበጀው በሚል አባባሉ በተቃራኒው እየተተገበረብን ነው።» አለ፡፡

ገብረየስ እዚህ ላይ ተቃውሞ አለኝ በሚል ስሜት እልህ እየተናነቀው መናገር ጀመረ። «መጀመሪያ ሕዝብ ማለት ምን ማለት ነው? የሚለውን በደንብ ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ ‹ሕዝብ የለመደው መደገፍ ሳይሆን መቃወም ነው።› የሚለውን ሃሳብ አልስማማበትም፡፡ የተወሰኑ ሰዎች የሕዝብ መገለጫ እንደሆኑ ተደርጎ መጠቀስ የለበትም፡፡ በእርግጥ ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዳሉት ‹ከመገዳደል እና ከመገዳደር፤ ሁልጊዜም እየተገፋፉ ኃይል ከማባከን ይልቅ ንግግርን እና ሰላምን ማስቀደም ይበጃል፡፡

በጦርነት ገንዘብ፣ ጊዜ እና ጉልበት ብቻ ሳይሆን ትውልድን ከመጨረስ እና ከማስጨረስ ይልቅ በትጋት ለሁሉም እንሥራ፡፡ ሥራን እናስቀድምና የድህነት ታሪካችንን እጥፋት እናበጅለት፡፡» ሲል እርሱም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ያስተላለፏቸው ሃሳቦችን እንደሚደግፍ ተናገረ፡፡

ተሰማ በበኩሉ፤ «ለነገሩ የእዚህች ሀገር ዋነኛ ችግር ብለን ልንጠቅሳቸው የምንችላቸው ብዙ ጉዳዮች አሉ፡፡ ዋናው ነገር አስቸጋሪዎች ነን። አስቸጋሪ እንግዳ ትራሱን ዘቅዝቆ ይተኛል። እንደሚባለው ማስቸገር ልማዳችን ነው፡፡ እናንተ የፈለጋችሁትን ብትሉም እኔ በበኩሌ እንደማንመች አምናለሁ፡፡» አለ፡፡

ገብረየስ በበኩሉ ተሰማን እየተቃወመ መሆኑን ለመግለፅ ፈለገ፡፡ «ዋናው ችግር የሕዝብ አለመመቸት ጉዳይ ሳይሆን፤ ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዳሉት ‹የሃሳብ አለመኖር ነው፡፡ ሰዎች ሃሳብ ቢኖራቸው ከግለሰብ ጋር ሳይሆን ከሃሳብ ጋር ይጨቃጨቁ ነበር፡፡ አሁን ብዙ ሰው የተሻለ አመራጭ ሲያመጣ አይታይም፡፡ የመጣን አማራጭ በግራና በቀኝ በስሜትና በተሳሳተ ስሌት መተንተን ልማድ ሆኗል፡፡ ይሄ ደግሞ ኢትዮጵያን ወደ ፊት አይወስዳትም።› ብለዋል፡፡ የእኔም እምነት ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጋር ተመሳሳይ ነው። ኢትዮጵያን እየበደላት ያለው የሃሳብ ድርቀት ነው፡፡ በሃሳብ ድርቀት ሳቢያ ከመገዳደር ይልቅ መገዳደልን እንደሞያ ተያይዘነዋል፡፡

አንዳንዶች ደግሞ ሃሳብ ያስባሉ፤ ምኞት ይመኛሉ፤ ልክ ፈጣሪውን ባዶ እጁን ባርክልኝ እያለ እንደሚለምነው ሰው፡፡ ፈጣሪው ሊባርክለት ሲል ባዶ እጁን እንደተገኘው እና እንዳልተባረከለት ሰው ይሆናሉ፡፡ በእርግጥም ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዳሉት፤ ‹ ሃሳብ ብቻውን በቂ አይደለም፤ ሃሳብ መተግበር አለበት፤ ለመተግበር ትጋት ይፈልጋል። ቀን ከሌሊት መልፋት ያስፈልጋል፡፡ ካልተሠራ እና ካልተለፋ በስተቀር ለውጥ አይመጣም። ለዚያውም ልፋቱም ቀጣይነት ያለው መሆን አለበት፤ የአንድ ሰሞን ሥራ ብቻ ሳይሆን ሁሌ የሚደረግ ጥረት መኖር አለበት፡፡

ሃሳብ መንጭቶ ተግባር ሲታከልበት ግጭት ይቆማል፡፡ አሁን ግን እንኳን ተግባር አዲስ ሃሳብ የለም፡፡ ሰዎች አዲስ ሃሳብ ቢኖራቸው ይህና ባደርግ፤ ያንን ብተው፤ ይህን ብጨምር እያሉ አዕምሯቸውን በራሳቸው አዲስ ሃሳብ እና ሃሳባቸውን ተግባራዊ በማድረግ ዙሪያ ስለሚወጠሩ ለመገዳደል አይነሱም ነበር፡፡ የተሻለ ሃሳብ ሲኖራቸው በሃሳብ ለመገዳደር ጥረት ያደርጋሉ፡፡ ነገር ግን አለመታደል ሆነና ዘመናችንን በመገዳደል ፈጀነው፡፡» ብሎ ገብረየስ በረዥሙ ተነፈሰ፡፡

ተሰማ በገብረየስ ገለፃ ተደሰተ፡፡ ገብረየስን እየደገፈ፤ «አዲስ ሃሳብ አመንጪ በዝቶ፤ የሚተጋ ተበራክቶ ሁሉም በየራሱ የሕይወት ለውጥ ላይ ቢረባረብ ብዙዎቻችን እንደምንመኘው ሰላም ብቻ ሳይሆን የኢኮኖሚ እድገት እና ዴሞክራሲም ብርቅ አይሆንብንም ነበር፡፡ የፓርቲ አመራሮችም ሆነ እያንዳንዳቸው ፓርቲዎች በበቂ መጠን ሀገር የሚጠቅም ሃሳብ ቢኖራቸው ኖሮ፤ በእነሱም ላይ የወደፊት ተስፋችን ይለመልም ነበር፡፡ ትልቁ ጉዳይ ግለሰብም ሆነ ቡድን እንዲሁም ድርጅት ብቃት ያለው የነጠረ ሃሳብ ሊኖረው ይገባል፡፡

እኛ ግን ‹ነገር ወዳጅ ሰው ከመንገድ ዳር ቅበሩኝ› ይላል፡፡ እንደሚባለው ነገረኞች ነን፡፡ ለመጣላት፣ ለመጋጨት እና ጦር ለመማዘዝ ነገር እንፈለፍላለን። የሌለ ታሪክ ፈጥረን ካልተጋደልን ብለን ለያዥ ለገናዥ እናስቸግራለን፡፡ የእኛ ነገር ይኸው ነው። በሃሳብ ከመገዳደር ይልቅ ምርጫችን ምንጊዜም መገዳደል ነው፡፡» ብሎ ሃሳቡን ደመደመ፡፡

ዘውዱ ለተሰማ ምንም ምላሽ አልሰጠም። ለዛሬ ዝምታን መርጧል፡፡ ገብረየስ ግን «ማለዳ የምትለቅም ዶሮ ጭልፊት አትጠልፋትም፤ እንደሚባለው ማንም ቢሆን ባገኘው ዕድል ሌሊቱ ሲነጋለት ማልዶ መሥራት አለበት። አለመሥራቱም ያው ነው፡፡ ዕድሉን አግኝቶ ካልሠራ ‹ገበያ ሂዳ ማንቀላፋት ሁለተኛ ጥፋት፤› እንደሚባለው ይሆናል። መሽቷን ትታ ስታንቀላፋ እንደተዘረፈችዋ ነጋዴ ከማይወጡበት ችግር ውስጥ መግባት ያጋጥማል። በሕይወታችን እያንዳንዳችን የምናደርገው እንቅስቃሴ በጥንቃቄ ካልታጀበ፤ አልሞትም ብሎ ሔዶ የማይቀበርበት ሀገር ደረሰ፡፡ እንደተባለው ሰውዬ የምንገባበት ችግር የማንወጣው ዓይነት ከባድ ይሆናል፡፡ ማንም ገድሎ ማትረፍ አይችልም፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዳሉት አማራና ኦሮሞ ቢፈልጉም ባይፈልጉም በሰላም ለመኖር ያላቸው ምርጫ የአንድ ሀገር ዜጎች ወንድማማች መሆናቸውን አውቀው፤ ተከባብረው አብረው መኖር ነው፡፡ ከዚያ ውጪ ያለው አማራጭ ምንም አይጠቅምም። ወደ መልካም ውጤትም አይወስድም። ሌሎቹም ብሔሮችም ቢሆኑ፤ ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋር በሰላም በፍቅር በትብብር ከመኖር ውጪ ምንም አዋጭ አማራጭ የላቸውም። የሚበጀው ሰላም፣ ፍቅር እና አብሮነት ብቻ ነው። ያለበለዚያ ግን ሞኝን ሁለት ጊዜ እባብ ነደፈው እንደሚባለው፤ ሁለት እና ሦስተኛ መገዳደል እና እልቂት ሀገርን ቁልቁል ወደ ኋላ ከመጎተት ውጪ ምንም ትርፍ የለውም፡፡

ፈተና ቢመጣ ፈተናውን በፅናት ለማለፍ አዲስ ሃሳብ ማመንጨት ተገቢ ነው፡፡ አዲስ ሃሳብ አመንጭቶ ተግቶ መሥራት ያስፈልጋል። መገዳደል በዝቶ ወንዙ በውሃ ተሞልቶ ክረምት ላይ ለመሻገር ቢያዳግትም፤ አዲስ ሃሳብ መንጭቶ፤ አዲስ ሃሳብ በትጋት እውን ሆኖ በጋ ሲመጣ ውሃው ደርቆ መሻገር ተራ የሚሆንበት ዕድል ስለሚፈጠር አዲስ ሃሳብ ማመንጨት ላይ እናተኩር፡፡ ከመገዳደል ይልቅ ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዳሉት በሃሳብ እንገዳደር፡፡» ብሎ እርሱም ሃሳቡን ቋጭቶ ወደ ቤቱ ለመሔድ ብድግ አለ፡፡

ስፖርትና መዝናኛ

# የዘመን ጥበብ


## የጠልሰም ጥበብ - በመጥፋት ጎዳና

ሙሉጌታ ብርሃኑ

ኅዳር ሲታጠን...ጠልሰም ሲጠለሰም፤ ሁለቱም ውሃ ጥም ሲቆርጡ አንጀትን ያረሰርሳሉ ነብስንም ያለመልማሉ። ከጥበብ ጋራ ከሚፈስሱ የሸንተረር ምንጮች መካከል እንደ ጠልሰም ያለ ኩልል ያለ ውሃስ ከወዴት ይገኛል...ጠልሰም ጥበብ...ጠልሰም ባህረ ምስጢር...ጠልሰም ጸጋ...ጠልሰም የፈጣሪ እጆች... ጠልሰም የእውቀት ሰማይ...ጠልሰም ስዕል...ጠልሰም ቀለማት...ጠልሰም...ሞት ያደፈጠበት የሕይወት መንገድ ነው። በተፈጥሮ ውስጥ የተገለጡ ምድርና ሰማይ፤ በቀለማት ጠብታ ከሰው ልጆች እውቀትና ጥበብ ጋር ተዋህደው የሚፈጥሩት ይሄ ለአዕምሮ የሚከብድ ምስለ አምሳል...የጠልሰም ጥበብ ወይንም ጥበበ ጠልሰም ይባላል። የአባቶቻችንን የአዕምሮና የመንፈስ ምጥቀትን የሚያሳይ የጥበብ ሥራ ነው። ጠልሰምን ስዕል ብቻ ነው እንዳንል...በስዕል ጥበብ ላይ ያረፈ፤ ምድርንና መላውን ተፈጥሮ የምናንቀሳቅስበት እንዲሁም በቀመራዊ ስሌት የተቀረጸ ቁልፍ ነው። ይሄ ጥበብ አባቶቻችን ዘንድ ነበር። ዛሬ ግን...በነበር ልናልፈው ጥቂት ርዝራዥ ቀርቶታል። 'ጠልሰም አስማትና ምትሀታዊ የሰይጣን ሥራ ነው' የሚል አስተሳሰብን በወለደ ትውልድ ተረግጦ፤ ከአፈር እንዲደባለቅ ተፈርዶበታል።

ጠልሰም አስማት ወይንስ ጥበብ? የጠልሰምን እውነተኛ ማንነት አግኝቶ መጨበጥ ለተማረውም ለተመራመረውም አልገባህ ያለ ቅኔ አዘል ምስጢር ሆኖበታል። በቀለማት ጠብታ እየተሰባጠረ፤ በቃላት ምሰሶ እየቆመ የሰውን ልጅ የሕይወት መስመር የሚያቀና ምን ዓይነቱ ተዓምራዊ ጥበብ ነው ብለን ሳንጨርስ፤ ደግሞ ከወዲህ ማዶ አስማታዊ ክንፉን ዘርግቶ የሰውን ልጅ ነብስ እስከመንጠቅ ያደርሳል። ለወትሮ ከአባቶቻችን ዘንድ ሳለ የምንመለከተው ጥበባዊ የእውቀት ዳርቻው ሰፍቶ ለታመመው ፈውስ መድኃኒት፤ ለከፋው የነብስ ምግብ ተስፋው ነበር። ዘግየት ብሎ ደግሞ ጠልሰምን በመጠቀም የጠሉትን የሚያደቁ፤ ያልተገባቸውን የሚነጥቁ ግለሰቦች ብቅ ማለት ጀመሩ። ጠልሰም አስማት ነው ወይ? ጠልሰም አስማት አይደለም። ለሰው ልጆች የጦር መሣሪያ ያስፈልጋል፤ ወይንስ አያስፈልግም? ብሎ እንደመጠየቅ ነው። አዎን ያስፈልጋል በማለት ጠቀሜታውን የሚያስረዱ እንዳሉ ሁሉ ኧረ በጭራሽ... በማለት ጎጂነቱን ለማሳየት የሚሞክሩም አሉ። በሁለቱም ወገን የማይካድ ሀቅ መኖሩ ግልጽ ነው። የመሣሪያ አጠቃቀማችን እነዚህን ሁለት ጽንፍ የያዙ አስተሳሰቦችን ፈጥሯል። በጠልሰም ባሕረ ሃሳብ ውስጥ ያለው ጉዳይም መልኩ ይህንኑ ይመስላል። የጠልሰም ጥበባዊነትም ሆነ አስማታዊነት በእኛ አጠቃቀም ላይ የተመሠረተ ነው። መድኃኒት ያድናል ደግሞም ይገድላል። በእውቀትና በጥበብ ብርሃን እየተመራን ያለውን ኃይል ከተጠቀምንበት የገነትን ምድራዊ በር እንደርስበታለን። በተቃራኒው በስውር የጨለማ ጉድጓድ ውስጥ ደብቀን ካደፈጥንበት ወደ ጥልቁ የሲኦል ወለል ተሽቀንጥረን እንወድቅበታለን። በጠልሰም ጥበብ የነበረው የአባቶቻችን ራዕይ እጅግ በጣም ግዙፍ ነበር። ዛሬ ግን ይህን የሀገር ሀብት ወድቆ አገኙትና አንዳንዶች ለጥንቆላቸው ውቃቢ መቀስቀሻ አደረጉት።

ጠልሰም የሚለው ቃል በጥሬው ውክል፣ አምሳል እንዲሁም በልዩ ሁኔታ ማስዋብ ማለት ነው። በጠልሰም ውክልና ማለት እንደ አስፈላጊነቱ ከእጽዋት፣ ከእንስሳት፣ ከአፈርም ሆነ ከየትኛው ተፈጥሮ የምንወስደው የተፈጥሮ ናሙና በትክክልም ለጉዳዩ የሚሆን ኃይል አለው ተብሎ ስለሚታሰብ ነው። ለምሳሌ እጽዋት ከበሽታ የማዳን ኃይል አላቸው። ከሰው ልጆች አንደበት የሚወጣው ቃልም የራሱ የሆነ ኃይል አለው፤ ተፈጥሮን ማዘዝ ይችላል። አንድ ሰው ታሞ ወደ ጠልሳሚ አባቶች ዘንድ ሲመጣ፤ የበሽታውን ዓይነት በመመርመር ከእጽዋቱም ሆነ ከሌላ አስፈላጊውን ሁሉ በመሰብሰብ ወካይ ቀለማትን አዘጋጅተው ከበሽታው እስከ መድኃኒቱ በስዕል ይጠለስሙታል። ከዚህ የበሽታ ዓይነት ሊያድኑት የሚችሉና ኃይል የተሞሉ ቃላትን ከዚሁ ስዕል ላይ በመከተብ ጠልሰምን በጥበብ እፍታ ያዘጋጁታል። በሕክምናው ብቻም ሳይሆን በተለያዩ ዘርፎች ለእያንዳንዱ ጉዳይ ተዓምራዊ መፍትሄን ሲሰጡበት ኖረዋል። በጠልሰም ጥበብ የተነደፉ አባቶቻችን ጂኦግራፊ አልተማሩም፤ ጂኦግራፊ ከእነርሱ ተማረ እንጂ... እራስዋ ተፈጥሮ እንጂ ባዮሎጂንም ጠመኔ ይዞ በጥቁር ሰሌዳ ያስተማራቸው የለም። የዚህን ጥበብ ምስጢራዊ እውቀቶችን በብዙ የብራና መጽሐፍቶቻቸው ላይ ያስቀመጡት ቢሆንም፤



የተሰረቁት ተሰርቀው የጠፉትም ጠፍተው ዛሬ በጥቂት ገዳማትና አድባራት ላይ ብቻ ይገኛሉ። የዚህ ጥበብ የምስጢር ተካፋይ የሆኑት ጠልሳሚዎቹም ቢሆኑ በትውልድ ቅብብሎሽ መሃል ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተመናመኑ ወደመጥፋቱ ተቃርበዋል። የጥበቡ ምንጮች በጉልህ ከወዴት እንዳሉ ባይታወቅም፤ የመፈወስ ኃይል እንዳለው የሚያምኑ አንዳንድ ሰዎች፤ ዛሬም ጠልሰምን በክታብ መልክ አስረውት እንመለከታለን። ጠልሰም ሃይማኖታዊ ቢመስልም፤ ነገር ግን ምንም ዓይነት ሃይማኖታዊ ይዘት የሌለው ግዙፍ የሆነ ሳይንሳዊ ጥበብ ስለመሆኑ በምርምር ጠልሰምን ፍለጋ የወጡ ሁሉ ይመሰክራሉ።

ጠልሰም መቼና እንዴትስ ተጀመረ?..የጠልሰም የስዕል ጥበብ በሀገራችን በረዥም የታሪክ መስመር ላይ ተጉዟል። የመነሻ ታሪኩ ወደ ሁለተኛው ክፍለ ዘመን ይወስደናል። ያኔ የጀመረው የአባቶች ጥበብ በስዕል አቡጊዳ አሊያም በሳይንሳዊ ምርምር የመጣ አልነበረም። ዛሬ ሳይንስ የቱንም ያህል ቢመጥቅ ያለ መርፌና ኪኒን ሊያድን አይችልም። የእኛ አባቶች ግን ከሳይንስ ቀድመው ተወልደው በእኛ ጉራማይሌ ሳይንስ ሞተዋል። ተፈጥራዊ ሰውነታቸውን በተፈጥሮ ብቻ በማከም በሕክምናው ዘርፍ ያገኟቸውን ግኝቶች ዛሬ ላይ ሳይንሱ ከላይ እያጣጣለ ከስር ቢያነፈንፈውም ሊደርስበት ግን አልቻለም። ጠልሰም የራሱ የሆኑ የተለዩ አላባውያን አሉት፡፡ ከእነዚህም ዕጽዋት፣ ኃይልን የታመቁ ቃላትና ልዩ ልዩ ምልክቶች ተጠቃሾች ናቸው። የጥንት አባቶቻችን ጥበብን ከእውቀትና እረቂቅ ከሆነው መንፈሳቸው ጋር አዋህደው የሚፈጥሩት ምልክታዊ እምቅ ኃይል ነው። በዚህም ምክንያት የአስማት ስዕል በማለት ብዙዎች ይፈሩታል። በጠልሰም አዋቂዎች ዘንድ ሁሉም የሚስማሙበት አንድ ፍልስፍና አለ። ይህም የሰው ልጅ የፈጣሪ ጠልሰም ነው። ጠልሰም ማለት የአንድ ነገር መልክ በመሆኑ፤ ፈጣሪም የሰውን ልጅ በአምሳሉ ፈጥሯልና የእርሱ መልክ ነው። ፈጣሪ በሰማይና በምድር ሁሉ ሙሉ ሥልጣንና ኃይል አለው። የሰው ልጅ ደግሞ የእርሱ አምሳል በመሆኑ ለሰው ልጅ በምድር ላይ የተሰጠው ኃይልና ሥልጣን አለ። ምድርን እንዲገዛ በምድር ያለውን ሁሉ ሰጥቶታል። ስለዚህ ጠልሰም ማለት ፈጣሪ የሰጠንን ነገር በጥበብ የምንጠቀምበት መክፈቻ ነው። በጠልሰምም የምናገኘው ይህንኑ ምድራዊ ኃይል ነው። የምድርን ቁልፍ ፍለጋ በተደረገ ጥበባዊ አሰሳ ጠልሰም ተወለደ፡፡

የጠልሰም ጥበብ ከምን ይወለዳል? ከስዕል ጥበብ ወይንስ ከመንፈስ ሃሳብ?... አንድ ጎበዝ ጠልሳሚ ለመሆን ጥሩ የስዕል ተሰጥኦ ሊኖር የግድ ነው። እንደማንኛውም ሰዓሊ ይህ ብቻ ጠልሳሚ አያስብለንም። ከሀገር ከርሰ ምድር እስከ ሕዝቦቿ ያለውን ውስጣዊ ማንነት ማወቅ ያስፈልጋል። ከእጽዋቱ እስከ አራዊቱ መመርመርን ይጠይቃል። ከአፈርና ድንጋዩ ጋር ማውጋት፤ እየዳሰሱ በመጫወት እያሸተቱ በመለየት ተፈጥሮን ጥንቅቅ አድርጎ ማወቅ ወሳኙ ነገር ነው። ጠልሰም የሚከወነው በስዕል ጥበብ ውስጥ ቢሆንም ከመደበኛ የስዕል ጥበብ የሚለይባቸው በርካታ ነገሮች አሉ። ሁለቱን አንድ የሚያደርጋቸው ደግሞ ስዕል የምናብ ፈጠራ እንዳለበት ሆኖ እውነተኛና ያለን፤ የሚኖር ነገርን መወከሉ ነው። ሁለቱም የተለየ ችሎታን የሚጠይቁና የአንድ ነገር ውክልና ያላቸው መሆናቸውም ጭምር። ከዚህ በተለየ ጠልሰም መሠረታዊና ሁሉም የጠልሰም ሊህቃን የሚግባቡት የራሱ የሆነ ቋንቋ አለው። እንደ ስዕል በራሳችን ፍልስፍና እንደገባን ብቻ የምናስቀምጠው አይደለም። አሐዛዊ ስሌቶችም የተካተቱበት ነው። አንድ ጠልሰም፤ ጠልሰም ለመሆን መልክ፣ ቁጥር፣ አሥራ ሦስቱ ወራት፣ ምልክት እና ሐረጎች ወይም ቃላት በአንድ ሊሰደሩ የግድ ነው።

ይህ ጥበብ በዓለማችን በተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች ውስጥ የሚገኝ ቢሆንም ረቂቅነቱም ሆነ የግዝፈት ደረጃው በእኛ ሀገር የነበረውን ግን አይስተካከልም። ለዚያም ነው የእኛን ብራና መጽሐፍት አጥብቀው የሚሹት። ኢትዮጵያዊ የሆኑ ልዩ ልዩ ምልክቶችን የራሳቸው እንደሆነ ነገር አድርገው በኩራት ሲጠቀሙባቸው እናያለን። ለምሳሌ ያህል በላሊበላ ውቅር አቢያተ ክርስቲያን አናት ላይ የሚገኘውን ዞዲያክ፤ የጀርመን ናዚዎች ወስደው አቀማመጡን ብቻ በተቃራኒው በመገልበጥ የወታደሮቻቸው አርማ አድርገውታል። ይህም በደንብ ልብሶቻቸው ላይ ሳይቀር ይጠቀሙበታል። በአሜሪካን የኮንግረስ ምክር ቤቱ መግቢያ ላይ ከሚገኘው የንስር አሞራን ጨምሮ በርካታ ምልክቶቻችንን ተነጥቀን እኛም እንደዋዛ ረስተናቸዋል። በጠልሰም ጥበብ ውስጥ አባቶቻችን ሲጠቀሙባቸው የነበሩትን ልዩ ልዩ ዞዲያኮችንም ሆነ የጠልሰም እውቀት፤ በሀገር ደረጃ ወጥቶ እንዳያገለግል ብዙ ጉዳዮች የተጋረጡበት መሆኑ ነው። ከዘመናት በኋላ እኚያ ሁሉ ጥበብ እኚያ ሁሉ እውቀት፤ አስማትና የመናፍስት ሥራ ናቸው ተብለው አወቅን በሚሉ አላዋቂዎች ተወገዙ። ሳይንስ የራሱን ኪስ ለማደለብ ሲል የእኛን ጥበብ ጨምድዶ ወደ ገደል ጣለው። በውስጡ ምስጢራትን ያዘለ በመሆኑ እውቀቱ በጥቂት ማኅበረሰብ ውስጥ ባሉ ጥቂት ቤተሰቦች ሲተላለፍ ኖሯል። ጠልሰምን ጨምሮ ሀገራችንን ሊለውጡ የሚችሉ ብዙ ቁልፎችን የያዙ ምስጢራዊ ቤተሰቦች ዛሬም ድረስ በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች አሉ።

የጠልሰም ጥበብ ዛሬ ላይ በመጥፋት ጎዳና ላይ እያዘገመ ይገኛል። ታምቆ ከነበረበት በባለቤትነት ወደ አደባባይ የሚያወጣው ባለማግኘቱ ወደ መክሰምና መኮሰስ ገብቷል። ብዙ ሊህቃንና የስዕል ጠቢባን በጠልሰም ዙሪያ ምርምር በማድረግ የእውቀቱን ጅራት ለመያዝ ቢታገሉም፤ በዋዛ እጅ የማይሰጥ እረቂቅና ድብቅ ሆኖባቸዋል። አሁን አሁን ሰዓሊያኑ በጥቂቱም ቢሆን በሥራዎቻቸው መሃል እንደ ማጣፈጫ ጠብ ሲያደርጉት እንመለከታለን። ከሀገራችን እውቅ ሰዓሊያን መካከል እስክንድር በጎሲያን፣ ወርቁ ጎሹ እና ዘሪሁን የትምጌታ ጠልሰምን ከዘመናዊው ስዕል ጋር አዋህዶ በመጠቀም ግንባር ቀደሞቹ ናቸው። ጠልሰም ከወደቀበት እንዲነሳ አድርገን በተቋም ደረጃ ሀገርና ሕዝብን የምንለውጥበት ቁልፍ ቢሆንም፤ አሁን ግን የመኖርና የመሞት ዕጣ ፈንታው ከሰዓሊያኑ እጅ ላይ ነው። የዚህን ጥበብ ግዙፍ ጠቀሜታ በመረዳት ከማንም ፈጥኖ ለመድረሱ ከእነርሱ የሚቀርብ አይኖርም። ይህን የተረዱም ዛሬን ስለጠልሰም በመሯሯጥ ላይ ናቸው።

የእኛ አባቶች የዓለምን ምስጢራዊ የእውቀት ቁልፍ የያዙ እውነተኛ የምድር ጌቶች ነበሩ። ከእነርሱ የተሰወረች ምስጢር፤ በልባቸው ያላደረች ጥበብና በአዕምሮዎቻቸው ያልፈሰሰ እውቀት ያለ አይመስልም። ለዚህም ነው ዛሬ ዓለም ሁሉ የረገጡበትን የእግር ኮቴ፤ የእጆቻቸው ዐሻራ ያረፈባቸውን የብራና መጽሐፍቶቻችንን እያነፈነፈ የሚያድነው። የእኛ የሆነውን ነገር ለማግኘት እንዲያ ሲያስሱ፤ የጥበብና እውቀቱ ባለቤት የሆንነው እኛ ግን 'አይሞቀኝ አይበርደኝ...' ብለን፤ ፍዝዝ ድንዝዝ ማለታችን ምኑን ቢያስነኩን ይሆን? የእኛ ጥበብ...የእኛ እውቀት አይነጥላ እየሆነብን ምትሀት...አስማት...የሰይጣን... እያልን አሽቀንጥረን የጣልናቸው የጥበብ አቁማዳዎች ቁጥር ስፍር የላቸውም። መርዶም ሳንቀመጥ ገድለን የቀበርናቸው የአባቶቻችን ጥበቦች፤ የሙት መንፈስ ቢኖራቸው ኖሮ በህልም፤ በቁም ቅዠት እየመጡ መውጫ መግቢያ ባሳጡን ነበር። ከእነዚህም መካከል አንደኛው 'ርስተ ጌታ' የተባለውና ከጠልሰም በፊት የነበረው ግዙፍ ጥበብ አንደኛው ነው። ምን ቀረሽ የማትባል የጥበብ ጸጋ በ'ርስተ ጌታ' ተገልጣ ነበር። ጥበብ አካለ እውቀትን ለብሳ፤ ባልተበረዘውና ጸአዳ በሆነው የአባቶቻችን የልብ ዙፋን ላይ ተቀምጣም ነበር። ዛሬ ታዲያ ይሄ ሁሉ የት አለን? ከእኛ አባቶች የወረስነው የመጠሪያ ስምና የዘር ግንድ ብቻ ነውን?

እንደ 'ርስተ ጌታ' ሁሉ የቀረችውንም የጠልሰምን ጥበብ ጥለን እፎይ!... ተገላገልን እንበል? ወይንስ ሳንቀደም ቀድመን፤ ጠልሰምን ከጻዕረ ሞት አድነን እኛም እንዳንበት? በጥቂት ብራናዎች ላይ በጠልሰም ጥበብ ዛሬም ድረስ ሰፍረው የሚገኙትን ምስጢራት መፍታት ከቻልን፤ አሁንም አረፈደም...ሀገርና ሕዝባችንን እንቀይርበታለን። ጠልሰም ዘ ጥበብ...

## ነህ

በ19 መቶ በዜሮ ዜሮ ጥቅምት 15ት፤

የዓድዋ ባለ ድል ዳግማዊ ምኒልክ ያቋቋሙት፤

የኢትዮጵያ ክብር የአፍሪካ ኩራት፤

አደባባይ ወጣን መቶ አስራ ስድስተኛውን

ልናከብርለት።

መከላከያችን የድንበር አጥራችን፤

የሀገራችን ክብር ዘብ የህልውናችን፤

የአብራካችን ክፋይ የበኩር ልጃችን፤

የጀግኖቹ አንበሳ አንተ ከፊት እንጂ አትሁን

ከኋላችን፤

የኢትዮጵያ ሠራዊት መከላከያችን ከዚህም

በላይነህ እናከብርሃለን።

ቀን በደህና ውሎ ሰላም ውሎ መግባት፤

እፎይ ብሎ ተኝቶ መነሳት፤

ከፈጣሪ በታች አንተ ስላለኸን የልባችን ኩራት።

ሰላም ሰላም ብዬ ሰላም ልበልህ፤

ቢያንስብህ ነው እንጂ ለአንተ አይበዛብህ፤

መከላከያችን ኩራታችን እና መመኪያችን ነህ።

**መዝገበ ከበደ ባይሞትናር**
**ሐሙስ ጥቅምት 15 ቀን 2016ዓ.ም**
**ኮተቤ ካራ(አዲስ አበባ)**

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## ወጣቶችና የበጎ ፍቃድ አገልግሎት

**እየሩስ ተስፋዬ**



ቃልኪዳን ሽመልስ ውልደቷና እድገቷ አዲስ አበባ ነው፡፡ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካ ሳይንስ እና ዓለም አቀፍ ግንኙነት የትምህርት ዘርፍ ተመርቃለች፡፡ ትምህርቱን ፈልጋው እና መርጣው ነው የተማረችው፡፡ ቃልኪዳን በከፊል የማየት ችግር አለባት፡፡ ከርቀት ማየት አትችልም፡፡ የጨለማ ፍርሃት እንዳለባትም ትናገራለች፡፡ ይሁን እንጂ ማንበብም ይሁን መጻፍ በሚገባ ትችላለች፡፡

የፖለቲካ ሳይንስ ምሩቋ ቃልኪዳን ከልጅነቷ ጀምሮ ከርቀት ማየት ስለምትቸገር በክፍል ውስጥ ሰሌዳ ላይ የሚጻፍን ነገር ወደ ደብተሯ መገልበጥ ለእሷ አዳጋች ነበር፡፡ በዚህም ከክፍል ተማሪዎቿ ደብተር በመዋስ ክፍል የተማረችውን እቤቷ ወስዳ ለመገልበጥ ትገደድ ነበር፡፡ ይህ በየቀኑ የክፍል ተማሪዎቿን ፊት እንድታይ አድርጓታል፣ «ደስ አይልም፡፡ ይህ ነገር እኔን በሚገባ ፈትኖኛል፡፡ አንዳንዴም ከርቀት ያለማየቱ ነገር ወደ ኋላ ያስቀራል፡፡» ስትል የገጠማትን ነገር ታስታውሳለች፡፡

ይህ ዓይነቱ ችግር በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ጭምር መኖሩን የምትናገረው ቃልኪዳን ምንም እንኳን መጻፍ እና ማንበብ ብትችልም ፈታኝ ተዘጋጅቶላት ፈተናዎችን ትወስድ ነበር። እርሷ የፈተና ወረቀቶችን ለማንበብ ወደ ፊቷ አቅርባ (አስጠግታ) ስትመለከት ብዙ ሰዎች ይጨነቃሉ፡፡ ለምን አርቀሽ አታይም? እና መሰል ጥያቄዎች ይቀጥላሉ፡፡ «እንደዚህ ዓይነቱ ነገር ስለሚገጥመኝ በፈታኝ እንድፈተን ይደረጋል፡፡» የምትለው ቃልኪዳን በዚህ ሂደት አልፋ በጥረተ ለምርቃት በቅታለች፡፡

ቃልኪዳን ፖለቲካል ሳይንስ እና ኢንተርናሽናል ሪሌሽንን ፈልጋ ያጠናችበት ምክንያት የምለውጠው ነገር እዚህ ዘርፍ ላይ ነው የሚል ዕምነት ስላላት ነው፡፡ እምነት ብቻ ሳይሆን ከልጅነቷ ጀምሮ ታሪክ እና ፖለቲካ ሲወራ በተለየ መልኩ እንደሚገባት እንዲሁም ልዩ ፍቅር እንዳላት ትናገራለች፡፡ «ታሪክ በጣም እወዳለሁ፡፡ እናም ብዙ መፍትሔ ያጡ ነገሮችን የመፍታት ብቃት ውስጤ ያለ ይመስለኛል፡፡ ለዚያ ነው ፖለቲካን የመረጥኩት። ያልተፈቱ ነገሮችን የመፍታት አቅም አለኝ ብዬ ነው የማምነውም፡፡» ትላለች፡፡

ቃልኪዳን ከምርቃት በኋላ ተቀጥራ ሥራ ለመሥራት አንዳንድ ቢሮዎችን ታንኳኳ እንጂ በቀላሉ ሊሳካላት ግን አልቻለም፡፡ «በፖለቲካል ሳይንስ የሥራ ማስታወቂያ ማውጣት አስቸጋሪ ነው፡፡» የምትለው ቃልኪዳን ከተቻለ ለምን መምህር አልሆንም? በማለት በአንዳንድ ትምህርት ቤቶች የሥነ ዜጋ ወይም የታሪክ መምህር ለመሆን ተወዳድራለች፡፡ ይሁን እንጂ በታሪክ እና በሥነ ዜጋ (ሲቪክስ) የተመረቁ መምህራን በመኖራቸው በተመረቀችበት የትምህርት ዘርፍ ሥራ እንድትፈልግ አስተያየት እየሰጡ ይመልሷታል፡፡

ቃልኪዳን አሁን ላይ ሥራ የመቀጠሩ ነገር ተስፋ ያስቆረጣት ትመስላለች፡፡ ስለዚህም ለምን ቁጭ ብዬ እጠብቃለሁ? በማለት ሥልጠናዎችን ለመከታተል ወሰነች፡፡ በዚህም መሠረት ስለ ሊደርሺፕ (አመራር)፣ ስለ ማኔጅመንት እና የሥራ ፈጠራ ሂደትን ያካተቱ ጉዳዮች ላይ ሥልጠናዎችን እየተከታተለች ትገኛለች፡፡ አሁን ሥልጠና በምትወስድበት ቦታም በበጎ ፈቃደኝነት ለማገልገል ይሁንታን አግኝታለች፡፡ በተጨማሪም ብራይት ሳይድ የተባለ ማኅበራዊ ሚዲያ ላይ በበጎ ፈቃድ እንድታገለግል አጋጣሚውን አግኝታለች፡፡

ቃልኪዳን ለወደፊት መገናኛ ብዙኃን ላይ ኀበዝ ጋዜጠኛ ሆና የመሥራት ፍላጎቱ አላት፡፡ እንደ እርሷ ብዙ ነገሮች ይቀየራሉ ብለው ከሚያምኑ ሰዎች ጋር በጋራ ለመሥራት ያላት ፍላጎትም ከፍተኛ ነው፡፡

ከምርቃት በኋላ ሥራ አለማግኘት የበርካታ ኢትዮጵያውያን ችግር ነው፡፡ አካል ጉዳተኛዋ ሞዴል እና ዲዛይነር ሳቤላ ከድርን በአርአያነት የምታነሳት ቃልኪዳን፤ በሁለት ቦታ ላይ በበጎፈቃደኝነት እየሠራች ትገኛለች፡፡ ዛሬ ላይ መቀጠር ብቻ አማራጭ ነው የሚል አመለካከቷም ተቀይሯል፡፡ «የሰው ልጅ አዕምሮውን መጠቀም መቻል አለበት፡፡ አቅሙ የፈቀደውን ነገር በበጎፈቃደኝነትም ሆነ በሌሎች አማራጮች ራሱን የሚቀይርበት መንገድ ማመቻቸት አለበት፡፡» በማለት ቁጭ ከማለት የተለያዩ አማራጮችን መሞከሩ ከጭንቀት ለመገላገል አንዱ አማራጭ መሆኑን ታመላክታለች፡፡

ያምሆኖ በመንግሥት በኩል ብዙ ሥራዎች መሠራት እንዳለበት ታስረዳለች፡፡ «በመንግሥት በኩል አስፈላጊ የሆኑ እና አካታች የሆነ ሥራዎችን መሥራት ይጠበቅበታል። አካል ጉዳተኛውንም ጉዳት አልባውንም በእኩል ማስተናገድ ቢቻል መልካም ነው፡፡» በማለት መፍትሄ የምትጠቁመው ቃልኪዳን፤ አንዳንድ ሰው በገንዘብ እጥረት ምክንያት በጎ ፈቃደኛ ሆኖ እንኳን ማገልገል እንዳልቻለ ትናገራለች፡፡ ስለዚህም እነዚህ ነገሮች በጣም ታስበው መሠራት ይኖርባቸዋል ባይ ናት፡፡ አካል ጉዳተኛው በቀላሉ ሥራዎችን መከወን እንዲቻለውም የተለያዩ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት እንዲቻልም ጥረቶች መደረግ እንዳለባቸው ጠቁማለች፡፡

እንደ ቃልኪዳን ማብራሪያ ሁሉም ሰው ተስፋ መቁረጥ የለበትም፡፡ «ከምንም ነገር በላይ ፈጣሪ ሰውን ፈጥሮ ብቻውን አይተወውም፡፡ ሰው ከጣረ የእጁን ፍሬ ያገኛል። ከሠራም ብር ያገኛል፡፡ እና ማንም ሰው እከሌ እንዲህ አለኝ፣ እከሌ እኮ ፊት ነሳኝ ብሎ ቤቱ ከመቀመጥ እንደነ ሳቤላ ጠንካራ ሆኖ መውጣቱ የተሻለ አማራጭ ነው፡፡» በማለትም ትመክራለች፡፡

«ይህች ዓለም ለጠንካሮች ነው የምትሆነው፡፡ ደካማ ከሆንን ችግሮች እየጨመሩ እንጂ እየቀነሱ አይመጡም፡፡ አንዳንድ ጊዜም ስሜትን ዋጥ አድርጎ ወደፊት መራመዱ ያዋጣል» ባይ ናት፡፡ በቀጣይ ምን ልስራ በሚለው ጉዳይ ላይ በብዙ እያሰበች የምትገኘው ቃልኪዳን፤ ለወደፊቱ ለብዙዎች መፍትሄ የሚሆን ሥራ ለመሥራት እና ለራሷ የምትለው ነገር እንዲኖራት ጥረት ማድረጓን ቀጥላለች፡፡

ቃልኪዳን እንደ እርሷ ብዙ ወጣቶች ከምርቃት በኋላ በሥራ ማጣት ራሳቸውን ለጭንቀት መዳረግ እንደማይገባቸው ትልቅ ምሳሌ ናት፡፡ እርሷ ይህንን በማድረጓ ከጭንቀት ተገላግላለች፡፡ ነፃ አገልግሎት እየሰጠች በበጎ ተግባራት የመንፈስ እርካታን ታገኝበታለች። የትናንት ጭንቀቷ ሥራ ተቀጥሬ ብሠራ የሚል ነበር፣ ዛሬ ግን ምን ሥራ ልፍጠር? የሚል ሆኗል፡፡ ሕይወት ብዙ መንገዶች እና ብዙ መልኮች አሏት፡፡ እርሱን መፈለግ፣ መጣር እና ለስኬት ለመብቃት ተግቶ መሥራት ከወጣቶች የሚጠበቅ ኃላፊነት መሆኑን መዘንጋት አይገባም፡፡

# ዓለም አቀፍ

## አሜሪካ ሐማስ በአል-ሺፋ ሆስፒታል ስር ማዘዣ ጣቢያ እንዳለው ይፋ አደረገች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



አሜሪካ ሐማስ በጋዛ ከተማ በሚገኘው እና ትልቅ በሆነው አል-ሺፋ ሆስፒታል ስር የማዘዣ ማዕከል እንዳለው የሚያሳይ መረጃ እንዳላት ገለፀች።

የአሜሪካ ብሔራዊ ደህንነት ቃል አቀባይ የሆኑት ጆን ኪርቢ እንዳሉት ቡድኑ በዚያ መጣሪያ እንደሚያከማች እና ለእሥራኤል ጥቃት ምላሽ ለመስጠት እየተዘጋጀ መሆኑን ተናግረዋል።

ይህ መረጃ እሥራኤል ሐማስ ሆስፒታሎችን የማዘዣ ጣቢያዎቹን ለመሸሽግ ይጠቀምባቸዋል የሚለውን ውንጀላዋን የሚደግፍ ሲሆን ከአጋሮቿ የተሰማ የመጀመሪያው መረጃም ነው።

መግለጫው የወጣው እሥራኤል ንጹሃን ዜጎችን ከጥቃት የመጠበቅ ኃላፊነት አለባት የሚል ጫና ከተለያዩ ዓለም አቀፍ አካላት እየተሰነዘረባት ባለበት ወቅት ነው።

የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን እንዳሉት አል-ሺፋ ሆስፒታል በዙሪያው ከሚደረጉ ከባድ ውጊያዎች «መጠበቅ አለበት» ያሉ ሲሆን፤ የዩኬ ጠቅላይ ሚኒስትር በበኩላቸው እሥራኤል በዓለም አቀፍ ሕጎች መሠረት መንቀሳቀስ አለባት ብለዋል።

ከቅርብ ቀናት ወዲህ በጋዛ ትልቁ ሆስፒታል በሆነው አል-ሺፋ ዙሪያ ያለው አካባቢ ከባድ ውጊያ የሚካሄድበት የጦር ቀጣና ሆኗል።

በሆስፒታሉ በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ተጠልለው እንደሚገኙ ይታመናል። ሚስተር ኪርቢ አሜሪካ ከተለያዩ ወገኖች ያሰባሰበቻቸው የራሷ የደህንነት መረጃዎች ነበሯት ብለዋል።

ሐማስ እና እስላማዊ ጂሃድ በጋዛ ሰርጥ የሚገኙ ሆስፒታሎችን እንዲሁም መሬት ለመሬት የተቆፈሩ ዋሻዎችን የወታደራዊ እንቅስቃሴዎቻቸውን ለመሸፈንና ያገቷቸውን ሰዎች ለማቆየት ይጠቀሙባቸዋል ሲሉ ተናግረዋል።

ከዚህ ቀደም የአሜሪካ አስተዳደር ሐማስ ሆስፒታሎችን ወታደራዊ እንቅስቃሴዎቹን ለመሰወር ይጠቀምበታል የሚለውን መረጃ ከሌሎች አካላት ስትጠቅስ እንጂ መረጃው እንዳላት ስትናገር ተሰምታ አትታወቅም።

እሥራኤል ምንም እንኳ በሆስፒታሉ ሐማስ ይገኛል ብላ ብታምንም እስካሁን ወደ ሕክምና ተቋሙ አለመተኮሷን ትናገራለች።

የእሥራኤል መከላከያ በአሜሪካ፣ ዩኬ እና የአውሮጳ ኅብረት በአሸባሪነት የተፈረጀውን እና በጋዛ ሰርጥ የሚንቀሳቀሰውን ሐማስን ለማጥፋት ያለመ ዘመቻ ከጀመረች አንድ ወር አልፏታል።

## ናይጄሪያዊቷ በዓለም ረጅሙን በእጅ የተዘጋጀ ዊግ አዘጋጅታ ክብረ ወሰን ያዘች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ሄለን ዊሊያምስ የተባለችው ናይጄሪያዊት በዓለም ረጅሙን በእጅ የተዘጋጀ የፀጉር ዊግ በመሥራት አዲስ የጊነስ የዓለም ክብረ ወሰንን ያዘች።

በተለያዩ ዘርፎች በዓለም ዙሪያ የሚያዙ ክብረ ወሰኖችን የሚመዘግበው ጊነስ ዎርልድ ሪከርድስ ባወጣው መግለጫ እንዳስታወቀው፤ የሌጎስ ከተማ ነዋሪ የሆነችው ሄለን ከ350 ሜትር በላይ የሚረዝም ዊግ ሠርታለች።

ለስምንት ዓመታት ዊግ በመሥራት ሙያ ላይ ተሰማርታ የቆየችው ሄለን ዊሊያምስ፣ ረጅሙን ሰው ሠራሽ ዊግ ለመሥራት 11 ቀናት የፈጀባት ሲሆን፣ 2,493 ዶላርም አስወጥቷታል።

ሄለን በዓለም ረጅሙን ዊግ በሠራችበት ጊዜ ጥሩ ልምድ ብታገኝበትም የመሥሪያ ዕቃዎቹን ማግኘትን ጨምሮ ሌሎች ፈታኝ ነገሮች እንደገጠሟት ተናግራለች።

ሄለን ለጊነስ ዎርልድ ሪከርድ እንደተናገረችው እየሠራች ሳለ «በጣም ደክሟት» ሥራውን ለማቆም ደርሳ ነበር።

«ነገር ግን ጓደኞቼ እና ቤተሰቦቼ ስላበረታቱኝ፣ የእነሱን ድጋፍ ችላ ላለማለት ትኩረት አድርጌ መሥራቴን ቀጠልኩ። በውጤቱም በዓለም ረጅሙን በእጅ የተዘጋጀ ዊግ ለመሥራት ቻልኩኝ» ብላለች ሄለን።

ዊጉን ከሠራች በኋላ ዋነኛ ችግር ሆኖባት የነበረው የዊጉን ርዝመት ለማወቅ በቀጥታ መስመር ተዘርግቶ በትክክል የሚለካበት ቦታ ማግኘት ነበር።

በመጨረሻ ግን ረጅሙን ዊግ ዘርግቶ ለመመተር ሌጎስን እና አቢዮኩታ ከተሞችን በሚያገናኘው የፍጥነት መንገድ ላይ ሥራዋ ተለክቶ ከ350 በላይ ሜትር እንደሆነ ተረጋግጧል።

ናይጄሪያውያን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተለያዩ መስኮች በጊነስ ዎርልድ ሪከርድ ላይ ያልተመዘገቡ ክብረ ወሰኖችን በመያዝ ለመታወቅ ጥረቶችን እያደረጉ ነው።

ከወራት በፊት ናይጄሪያዊቷ ምግብ አብሳይ ሂልዳ ባቺ ለበርካታ ተከታታይ ሰዓታት ምግብ በማብሰል የዓለም ክብረ ወሰንን ለመያዝ በመቻሏ በናይጄሪያ መነጋገሪያ መሆኗ ይታወሳል።



ነገር ግን ባለፈው ሳምንት የሂልዳ ክብረ ወሰን በሌላ አገር ዜጋ ተሰብሮ ቦታዋን ለቃለች።

አሁን ደግሞ ሄለን ዊሊያምስ ረጅሙን በእጅ የተዘጋጀ ዊግ በመሥራት ክብረ ወሰን በመያዝ በዓለም ቀዳሚ ሆናለች።

ፖስቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ

## የቆዳው ዘርፍ ስትራቴጂ አስቀድሞ መጥቶ ቢሆን መልካም፣ አሁን መምጣቱም መልካም!

**ዘካርያስ**

ኢትዮጵያ በዓለም በከብት ሀብቶቻቸው ከሚታወቁ አስር ሀገሮች ተርታ እንዲሁም ከአፍሪካ ቀዳሚዋ ብትሆንም፣ ከዘርፉ ተጠቃሚ በመሆን በኩል ግን ተጠቃሽ መሆን አልቻለችም። ሀገሪቱ በተለይ በቆዳና ስጋ ሀብቷ የሚገባትን ያህል ተጠቃሚ አለመሆኗን በዘርፎቹ የተሰማሩ አካላትም፣ መንግስትም በተደጋጋሚ ያረጋገጡት ሀቅ ነው። ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ሊያስገኝ የሚችለው ቆዳ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ እንደ ዋዛ እየተጣለ ያለበት ሁኔታ ብቻውን ሌላው ትኩስ ማረጋገጫ ነው።

በቅርቡ የተካሄደ መድረክም ይህንኑ ቆዳ በሚገባ ጥቅም ላይ አለመዋሉን አረጋግጧል። የቆዳው ዘርፍ ባለድርሻ አካላት በዘርፉ ችግሮችና መፍትሄዎች ላይ በመከሩበት በዚህ መድረክ ላይ በሀገሪቱ በዓመት ከሚመረተው የቆዳና ሌጦ ምርት ግማሽ ያህሉ አገልግሎት ላይ እንደማይውል የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር አስታውቋል።

በመድረኩ ላይ ከ2016 እስከ 2025 ዓ.ም የሚተገበርና የቆዳውን ዘርፍ ችግሮች በመፍታት ልማቱን ለማጠናከር የሚረዳ የስትራቴጂ ሰነድ ለውይይት በቀረበበት ወቅት እንደተጠቆመው፤ የቆዳ ዘርፉ ባሉበት ውስብስብ ችግሮች ምክንያት በሀገር አቀፍ ደረጃ በየዓመቱ ከሚመረተው ከ41 ሚሊየን በላይ የቆዳና ሌጦ ምርት ግማሽ ያህሉ ብቻ ነው አገልግሎት ላይ የሚውለው። በዚህ የተነሳም ሀገሪቱ ከዘርፉ ማግኘት የሚገባትም ጥቅም አጥታለች።

ሀገሪቱ ከ165 ሚሊየን በላይ የቀንድ ከብት ሀብት እንዳላት ሚኒስቴሩ ጠቅሶ፣ ከዚህ የሚገኘው የቆዳና ሌጦ ምርት ግን ዝቅተኛ ነው ብሏል፤ ችግሩን ለመፍታት ይህ የአስር ዓመት ስትራቴጂ መነደፉን አመልክቷል። የቴክኖሎጂ አጠቃቀም አናሳ መሆን፣ የዓለም የቆዳ ምርቶች ገበያ መቀዛቀዝ፣ የመኳኳዣ እጥረት፣ የጥሬ ቆዳ አሰባሰብ ችግር፣ ምርቶች የሚቀርቡበት ሰፊ ገበያ አለመኖርና የግብአት አቅርቦት እጥረት ዋነኛ የዘርፉ ማነቆዎች መሆናቸውን አመልክቷል።

በመድረኩ የስትራቴጂው ፋይዳዎችም ተጠቁመዋል። ስትራቴጂው ምክንያት ሆኖ ባለድርሻ አካላት በጉዳዩ ላይ በጋራ መምከራቸው በራሱ ብቻ ዘርፉን ለመታደግ ይጠቅማል። በቆዳና ሌጦ ምርት ላይ እየደረሰ ያለው ጉዳት በእጅጉ የሚያም መሆኑን እዚህ ላይ መግለጽ ይገባል። የዘርፉ ችግሮች አያሌና ውስብስብ ናቸው። ይህን ችግር ለመፍታት ርብርብ ማድረግ መጀመር የነበረበት ዛሬ አልነበረም። አስቀድሞ ይህን ማድረግ ባለመቻሉ የሀገር ሀብት የሆነው ቆዳ መጣል ላይ ከተደረሰ ዓመታት ተቆጥረዋል።

የቆዳውን ዘርፍ ችግሮች ለመፍታት መጮህ ሲገባ ዓመት በአላት በመጡ ቁጥር ዘርፉ የሚመለከታቸውን አካላት ዋቢ ያደረጉ ዘገባዎች ይዘዋቸው የሚወጡ መረጃዎች ግራ የሚያጋቡ የሚባሉ ናቸው። ቆዳ እየተጣለ ባለበት ሀገር «በዓሉን በማስመልከት እርድ በሚፈጸምበት ወቅት ለቆዳ ጥንቃቄ ይደረግ» የሚሉ አይነት ዘገባዎች ናቸው ሲቀርቡ የቆዩት። ከአንዴም ሁለቴ፣ ሶስቴ፣ ቆዳ ለጣለ ማሕበረሰብ ይህ ዜና ምን ይረባዋል? ለሚጣል ቆዳ ጥንቃቄ አድርጉ የሚል መልዕክት ማስተላለፍስ ራስን ለመሳለቂያ አይዳርግም ወይ? ቆዳ ጠያቂ አጥቶ እየተጣለ ባለበት ወቅት ይህን አይነት ዜና መስማት በእርግጥም ይገርማል።

በአንድ ወቅት ከቡና ቀጥሎ ሁለተኛው የውጭ ምንዛሬ ምንጭ የነበረው ቆዳ እንደ ዋዛ እየተጣለ ነው፤ መፍትሄ ይፈለግለት የሚል መረጃ ነጋ ጠባ መስራት ሲገባ በእርድ ወቅት ቆዳ እንዳይቀደድ ጥንቃቄ ይደረግ ብሎ መረጃ መስጠት ወቅታዊም

> **የሀገሪቱ የቆዳና ሌጦ ምርት ሲጣል ማየት/ ለዚያውም ለዓመታት/ በእጅጉ ያማል። በዘርፉ ላይ ለዓመታት የሰሩና አሁን በሌሎች ዘርፎች ላይ ያሉ አካላት ጭምር ዘርፉ በዚህ ደረጃ መሰበሩ በእጅጉ እያሳዘናቸው ይገኛል**

ምጣኔ ሀብታዊ ፋይደም የለውም።

ሁሉም ማሕበረሰብ ባለፉት ዓመታት የታዘበው ቆዳ የሚሰበሰበው በመጥፋቱ የተነሳ እንደ ሌሎች የእርድ ተረፈ ምርቶች በየቆሻሻ መጠያው፣ በየስርቻውና በየወንዙ እየተጣለ መሆኑን ነው። የአራጆች ድምጽ እንጂ የቆዳ ገዥዎች ድምጽ ከተሰማ ቆይቷል። የአራጅ ሂሳብን ይችል የነበረው ወይም የአራጅ ወጪን በከፊልም ቢሆን ይችል የነበረው ቆዳ ሲጣል ምን ያህል ከፍተኛ መጠን ያለው ሀብት እየተጣለ መሆኑን መገንዘብ አያዳግትም።

በአንድ ወቅት በዘርፉ ላይ ዘገባ ለመስራት ከጥቂት ዓመታት በፊት ከሚመለከታቸው ክፍሎች አንዱን አነጋግሬ ነበር። መረጃውን የሰጡኝ አካላት የቆዳና ሌጦን ጉዳይ በቁጭት ነው ያነሱልኝ። ከቡና ቀጥሎ ሁለተኛው የውጭ ምንዛሬ ምንጭ የነበረበትን ዘመን የጠቀሱት እነዚህ ምንጮች፣ የቆዳ ጉዳይ በእጅጉ አሳሳቢ ደረጃ ላይ መድረሱን ነገሩኝ።

የዘርፉ ችግሮች በርካታ መሆናቸውን ጠቅሰው፣ በተለይ ቆዳ ሰብሳቢዎች ለከፍተኛ ኪሳራ መዳረጋቸውን፣ ቆዳ ተረካቢዎች /ኢንዱስትሪዎች/ በሚሰጧቸው ዝቅተኛ ዋጋ የተነሳ ቆዳ ከፋኝ መጎዳታቸውን፣ በርካታ ቆዳ ሰብሳቢዎች ከስራ ውጪም መሆናቸውንም ገልጸውልኝ ነበር።

እውነታው ፍንትው ብሎ የሚታይ ቢሆንም፣ ምክንያቱ ይህ ይሁን ሌላ ቆዳ ለመሰብሰቢያ በየአደባባዩ የተገነቡ ማዕካላት በአሁኑ ወቅት በቦታቸው የሉም። ይህም ቆዳ መሰብሰብ ላይ እየተሰራ ስላለመሆኑ እንደ አንድ አመላካች ሊወሰድ ይችላል።

ኢንዱስትሪዎቹ የሚያነሷቸው ችግሮች ስለመኖራቸውም ይገለጻል። ከጥንት ጀምሮ በእርድ ወቅት በሚከሰት የጥንቃቄ ጉድለት ሳቢያ በቆዳ ላይ ጉዳት እንደሚደርስ ይገለጻል፤ አዎን ሊደርስ ይችላል፤ ጥንቃቄም መደረግ አለበት። ባለኢንዱስትሪዎቹ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተደጋጋሚ የሚያነሱት ችግር ለዘርፉ የሚያስፈልጉ ግብአቶችን ከውጭ ለማስመጣት የሚያጋጥመው የውጭ ምንዛሬ እጥረት ነው።

ልብ በሉ እንግዲህ፤ ዘርፉ የውጭ ምንዛሬ አመንጪ ሆኖ እያለ ነው የውጭ ምንዛሬ እጦት ፈተና የሆነበት። በእዚህ ጉዳይ ላይ ከመንግስት አካላት ጋር ብዙ ቢመከርም፣ የመጣ ለውጥ ግን ሳይመጣ ብዙ ጊዜ ቆይቷል። ኢንዱስትሪዎቹ ቆዳና የቆዳ ውጤቶችን ለውጭ ገበያ ልከው ከሚያገኙት የውጭ ምንዛሬ እጅግ የተወሰነውን ነበር እንዲጠቀሙ የሚፈቀድላቸው። ቢያንስ 50 በመቶው እንዲፈቀድላቸው ሲጠይቁም ነበር። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ምን ያህል የኢንዱስትሪዎቹን ጥያቄ የመለሰ እንደሆነ ባላውቅም መንግስት ለእዚህ ችግር መፍትሄ ያስቀመጠ መሰለኝ።

ሌሎች አካላት ደግሞ የኢንዱስትሪዎች አለመዘመንና እርጅና የዘርፉ ሌላው ችግር መሆኑን ይጠቁማሉ። በእርድ ወቅት በቆዳ ላይ ጉዳት መድረስ እንደሌለበት የሚጠቁሙት እነዚህ አካላት፣ በኢንዱስትሪዎች ማሽነሪዎች እርጅና የተነሳ እዚያው ፋብሪካ ውስጥም ቆዳ የሚቀደድበት ሁኔታ እንዳለም ያመለክታሉ። ኢንዱስትሪዎች ዘመኑን የዋጁ አይደሉም፤ በሌላ ሀገር አገልግሎታቸውን ጨርሰው እንደገና ኢትዮጵያ ውስጥ የተተከሉ ናቸው፤ በዚህ ምክንያት በቆዳ ላይ ጉዳት ያደርሳሉ የሚሉ አስተያየቶችም ይሰነዘራሉ።

መንግስት በዘርፉ ላይ ያለውን ችግር በመመልከት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ጥሬ ቆዳ ለውጭ ገበያ እንዲቀርብ ያደረገበት ሁኔታ መኖሩን መረጃዎች ይጠቁማሉ። ደረቅ ቆዳ ወደ ናይጄሪያ እንደሚላክ ነው የሚገለጸው። ቆዳ የትም ከሚጣል ጥሬ ቆዳ ወደ ውጪ መላኩ አንድ መፍትሄ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። ቀደም ሲል ያነሳሁት ለአጠቃላይ ላኪዎች የወጣው አዲስ አሰራር የቆዳና ቆዳ ውጤቶች ላኪዎችም ከሚያገኙት የውጭ ምንዛሬ እስከ አሁን ከሚጠቀሙት በላይ ሊጠቀሙ የሚችሉበት እድል መመቻቸቱም አንድ ለውጥ ሊሆን ይችላል። ችግሩ ግን ከዚህም በላይ መስራትን የግድ ይላል።

መንግስት የዘርፉን ማነቆዎች በመፍታት ልማቱን ለማሳለጥ ይጠቀማል የተባለ ከ2016 ጀምሮ ለአስር ዓመት የሚተገበር ስትራቴጂ ይዞ መምጣቱን ደግሞ እንደ አንድ ለውጥ መመልከት ይገባል። ስትራቴጂው ቀደም ብሎ መጥቶ ቢሆን ኖሮ መልካም ነበር፤ አሁን መምጣቱም መልካም ነው። ስትራቴጂው መያዝ ያለበትን ሁሉ እንዲይዝ ማድረግ ላይ ግን በሚገባ መስራት ያስፈልጋል። በስትራቴጂው ላይ ባለድርሻ አካላት እንዲመከሩበት መደረጉ አንድ ጥሩ ነገር ነው። ምክክሩ ግን ሰፊ መሆን አለበት ፤ ብልጭ ብሎ ወደ መጽደቅ የሚሄድ መሆን የለበትም። በየደረጃው ውይይት ሊደረግበት ይገባል።

በዓለም ገበያ የቆዳ ግብይት መቀዛቀዙን የሚገልጹ አካላት ቢኖሩም፣ ሌሎች በዘርፉ ላይ የሚሰሩ አካላት ገበያው አሁንም እንዳለ ነው የሚጠቁሙት። ዛሬም ቢሆን የሀገሪቱ የቆዳና ቆዳ ውጤቶች በዓለም ገበያ ተፈላጊ መሆናቸውን በዘርፉ የተሰማሩ አምራቾችና ላኪዎች ይገልጻሉ።

የኢትዮጵያ ቆዳ በተለይ የደጋ በጎች /የሀይላንድ ሺፕ/ ቆዳ በውጭው ዓለም በከፍተኛ ሁኔታ ተፈላጊ መሆኑን እነዚሁ አካላት አሁንም ይጠቁማሉ። በፋሽን ኢንዱስትሪውም በኩል ቢሆን የቆዳ ምርቶች ተላጊነት እየጨመረ መጥቷል። በሀገር ውስጥም ቢሆን ዋጋቸው እየተወደደ እንጂ የቆዳ ውጤቶቹ በእጅጉ ተፈላጊ ናቸው።

ይህ በሆነበት ሁኔታ የሀገሪቱ የቆዳና ሌጦ ምርት ሲጣል ማየት/ ለዚያውም ለዓመታት/ በእጅጉ ያማል። በዘርፉ ላይ ለዓመታት የሰሩና አሁን በሌሎች ዘርፎች ላይ ያሉ አካላት ጭምር ዘርፉ በዚህ ደረጃ መሰበሩ በእጅጉ እያሳዘናቸው ይገኛል።

የቀደሞው መንግስት ከቆዳና ቆዳ ውጤቶች የበለጠ ተጠቃሚ ለመሆን ጥሬ ቆዳ ለውጭ ገበያ እንዳይቀርብ ክልከላ ጥሎ ነበር፤ በምትኩ እሴት የተጨመረበት ቆዳ ብቻ ለውጭ ገበያ ለማቅረብ አቅጣጫ አስቀምጦ መስራት ውስጥ ገብቶ እንደነበር ይታወሳል።

በተለይ በእድገትና ትራንስፎርሜሽን የእቅድ ዘመናት በዚህ ላይ ለመስራት እንቅስቃሴዎች ተደርገዋል፤ ይሁንና ከቆዳ የሚገኘው ተጠቃሚነት ማደግ ሲገባው ቁልቁል እየወረደ ሄዶ ቆዳ የሚጣልበት ዘመን ላይ ከተደረሰ ዓመታት ተቆጥረዋል።

የሀገሪቱን የቆዳ ዘርፍ ተዋንያን ከገጠሟቸው ተግዳሮቶች በማውጣት እንደ ዋዛ እየተጣለ ያለው የሀገሪቱ ቆዳ ለኢንዱስትሪዎች የሚቀርብበትን መንገድ መፈለግ ወቅቱ የሚጠይቀው ተግባር ነው። ለእዚህ ስኬት ደግሞ የስትራቴጂውን መምጣት እንደ መልካም አጋጣሚ በመጠቀም አሁንም በዘርፉ ላይ በሚገባ መምከርና መካተት ያለባቸው ካሉ ማካተት ያስፈልጋል።

በስትራቴጂው መሰረት በዘርፉ ቀጣይነት ያለው ኢንቨስትመንት ለመሳብ፣ የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን ለማሻሻል፣ የጥሬ ቆዳ አቅርቦትንና ጥራትን ለማሳደግና ሌሎች ሀገሮች በቆዳ ውጤቶች ያደጉባቸውን መንገዶች ለመቅሰም ጥረት ይደረጋል ተብሏል። የቆዳና ቆዳ ውጤቶች መዳረሻ ሀገሮችን ማሳደግ፣ የሀገር ውስጥ ገበያን መጠቀም፣ ከውጭ የሚገቡ ኬሚካሎችን በሀገር ውስጥ ማምረት የሚሉትና ሌሎች መፍትሄዎች እንደሚተገበሩም ተመልክቷል።

ሁሉም መልካም ናቸው። ምክከሩ በሌሎች መድረኮችም የሚቀጥል ከሆነ እንዲሁም ሰነዱ እስከሚፀድቅና ስራ ላይ አስከሚውል ድረስ ችግሮቹን ስኬቶቹንም በዝርዝር በመዳሰስ መካተት ያለባቸውን ማካተት ይገባል።

ከዘርፉ የበለጠ ተጠቃሚ ለመሆን በእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዘመኑ ጥሬ ቆዳ ለውጭ ገበያ ከማቅረብ በመውጣት እሴት ጨምሮ ብቻ መላክ ላይ ለመስራት የተሄደበት ርቀት ለምን ውጤታማ ላይሆን እንደቻለም መመልከት ያስፈልጋል።

ቆዳ በዚህ ልክ እየተጣለ ባለበት ሁኔታ ኢንዱስትሪዎች ቆዳና ሌጦ ከየት እያገኙ ነው በመስራት ላይ የሚገኙት? የሚለው ጥያቄም በአግባቡ መመለስ ይኖርበታል። እያንዳንዱ የዘርፉ አካል እየተዳሰሰ ችግሩ የት ላይ እንደሆነ ታይቶ መፍትሄውም ምን መሆን እንዳለበት መመላከት አለበት።

ስትራቴጂው ሊተገብራቸው ይዟቸው የመጣ ተግባሮች አንድ ነገር ሆነው በሀገሪቱ ታሪክ ቆዳ እስከመጣል ያደረሰ ኪሳራ ላይ ለምን እንደተደረሰ በሚገባ አጥንቶ በአስቸኳይ ለችግሩ መፍትሄ በመስጠት ዘርፉ የሚያገግምበት መንገድ መቀየስ ይኖርበታል።

# ስፖርት





## ትዕግስት አሰፋ የዓመቱን ምርጥ አትሌቶች ሽልማት ለማሸነፍ ተቃርባለች

ብርሃን ፈይሳ

የዓለም አትሌቲክስ በመጠናቀቅ ላይ በሚገኘው የውድድር ዘመን የላቀ ብቃት ያሳዩ አትሌቶችን አወዳድሮ ከሳምንታት በኋላ ይሸልማል፡፡ ይህ ክብር በአትሌቲክስ ቤተሰቡ እንዲሁም ስፖርቱን በሚመራው የበላይ አካል ምርጫ ላይ ተመስርቶ የሚሰጥ እንደመሆኑ ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ነው፡፡ በመሆኑም በምርጫው መካተት እንዲሁም ከመጨረሻዎቹ እጩዎች መካከል ለመካተት የተሻለ ብቃት ማሳየት ወሳኝ ነው፡፡

ላለፉት ሳምንታት በማሕበራዊ ድረገጾች ድምጽ ሲሰጣቸው ከቆዩ አትሌቶች መካከል ብልጫ ያገኙትን አምስት አትሌቶች የዓለም አትሌቲክስ አሳውቋል። አምስቱ አትሌቶች ከተለያዩ ሃገራት የተወጣጡ እና በተለያዩ ርቀቶችና የሜዳ ተግባራት ውድድሮች ተሳታፊ ሲሆኑ፤ ሁለቱ ግን አፍሪካን በመወከል ከኢትዮጵያ እና ኬንያ የተገኙ ናቸው፡፡ ሁለት እጩዎች የነበሯት ኢትዮጵያ በበኩሏ በአንድ አትሌት እስከመጨረሻው የምትፎካከር መሆናን አረጋግጣለች፡፡ በመጪው የፈረንጆቹ ወር አጋማሽ ሞናኮ ላይ በሚካሄደው ስነስርዓት በሚደረገው የዓመቱ ምርጥ አትሌት ሽልማት ይፋ እስኪሆንም አጓጊነቱ ቀጥሏል፡፡

በመጨረሻው የእጩዎች ዝርዝር ውስጥ ከተካተቱ አምስት አትሌቶች መካከል ኢትዮጵያዊቷ የማራቶን ጀግና አትሌት ትዕግስት አሰፋ የዓመቱ ምርጥ አትሌት የመሆን ዕድሏ እየሰፋና ሚዛን እየደፋ መጥቷል፡፡ ምክንያቱ ደግሞ አትሌቶች በቀላሉ በማይዳፈሩትና ሮጠው ለመጨረስም ከፍተኛ ጽናትና ብቃትን በሚጠይቀው ማራቶን የድርብ ክብር ባለቤት በመሆኗ ነው፡፡




አትሌት ትዕግስት አሰፋ የዓመቱ ምርጥ አትሌቶች ሽልማትን የማሸነፍ እድል አላት፤

ባለፈው መስከረም ወር በተካሄደው የበርሊን ማራቶን በሴቶች የዓለም ክብረወሰን የሆነ ሰዓት ያስመዘገበችው ትዕግስት አሰፋ ከመጨረሻዎቹ አምስት እጩዎች አንዷ መሆኗን የዓለም አትሌቲክስ ከትናንት በስቲያ ይፋ አድርጓል፡፡ ትዕግስት ከሰበረችው የማይደፈር የማራቶን ክብረወሰን ባለፈ አስደናቂው ያለፈ ታሪኳ ትኩረት በመሳብ በመላው ዓለም እጅግ አነጋጋሪ አድርጓታል፡፡ በመላው ዓለም ያሉ አትሌቶችን በተለይም ሴቶችን ልታበረታና ልታነቃቃ የምትችል እንደመሆኗ በስፖርት ቤተሰቡ በተሰጣት ድምጽ ላይ የዓለም አትሌቲክስ ባለሙያዎች ይሁንታም ተጨምሮበት ለዓመታት ከኢትዮጵያ የራቀውን ክብር እንደምታስመልስም ይጠበቃል፡፡

በ400 እና 800 ሜትር አትሌቲክስን የጀመረችው ትዕግስት ሃገሯን በመወከል ሜዳሊያ ማስመዝገብ የቻለች አትሌት ናት፡፡ ፊቷን ወደማራቶን ካዞረች በኋላ ግን እአአ ከ2014 አንስቶ ከተረከዝ ጅማት ሕመም ጋር ጠንካራ ትግል ስታደርግ ነው የቆየችው፡፡ ይኸው ጉዳቷ እየጠነከረ ከመምጣቱ ጋር ተያይዞም የሕክምና ባለሙያዎች ሩጫን እንድታቆም ቢነግሯትም ከአንድ ዓመት በኋላ በድጋሚ ወደ ውድድር ተመልሳ ነበር። ከሕመሙ ሙሉ ለሙሉ ማገገም አለመቻሏም እአአ በ2019 የቫሌንሺያ ግማሽ ማራቶንን እንዳጠናቀቀች በድጋፍ ወደ ሕክምና ስፍራ እስከመሄድም አድርሷታል። በወቅቱ በክራንች እየታገዘች በሄደችባቸው የአውሮፓ የሕክምና ማዕከላትም በተመሳሳይ ሩጫን እንድታቆም ቢነገራትም የጽናት ተምሳሌት የሆነችው አትሌት ግን ከሕመሟ አገግማ ወደ ቀድሞ አቋሟ ለመመለስ ሳትሰለች በመስራት በጎዳና ላይ ሩጫዎች ወደ አትሌቲክስ ሕይወቷ ለመመለስ ችላለች፡፡

ከረጅም ጊዜ የሕክምና ክትትል በኋላ የመጀመሪያ ማራቶኗን በሳውዲ አረቢያ ያደረገችው አትሌቷ በወቅቱ ያስመዘገበችው 2:34:01 የሆነ ሰዓት ነበር። ባለፈው ዓመት ደግሞ በዚሁ የበርሊን ማራቶን 2:15:37 በሆነ ሰዓት በመሮጥ የውድድሩን ክብረወሰን እንዲሁም የዓለም ሶስተኛውን ፈጣን ሰዓት ማስመዝገብ ችላ ነበር፡፡ አትሌቷ የገባችበት ሰዓት ቀድሞ ከነበራት 19 ደቂቃዎችን ያሻሻለችበት መሆኑ በርቀቱ ያላትን የወደፊት ተስፋ በግልጽ ያመላከተ ነበር፡፡ ከዓመት በኋላ ዳግም በሮጠችበት የበርሊን ማራቶንም ከነበራት ሰዓት ወደ 4 ደቂቃ በማሻሻል 2:11:53 በሆነ ሰዓት ነበር የዓለም ክብረወሰኑን ከእጇ ያስገባችው፡፡

የአትሌቷን ጥንካሬ የሚያጎላውም በርቀቱ አስቀድሞ ከተያዘው ክብረወሰን በ3 ደቂቃዎች ቀድማ መግባቷ ሲሆን፤ እንደወንዶች ፈጣን ሰዓት በቶሎ በማይመዘገብበት የሴቶች ማራቶን ከ2 ሰዓት ከ10 ደቂቃ በታች መግባት ይቻላል የሚለውንም ያስመሰከረ ሆኗል፡፡ በመሆኑም የአትሌቷ ታሪክ ቀያሪ ድል እንዲሁም በቀላሉ በማይደፈረው ማራቶን የዓለም ቁጥር አንዷ አትሌት መሆኗ በምርጫው ብልጫ እንደሚያስገኝላት ይጠበቃል፡፡

በሌላ በኩል በዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና የ10ሺ ሜትር የወርቅ ሜዳሊያ ባለቤቷ እንዲሁም በ5ሺ ሜትር የክብረወሰን ባለቤቷ አትሌት ጉዳፍ ጸጋይ በዚህ ምርጫ በእጩነት ብትካተትም ያገኘችው ድምጽ ግን ከመጨረሻዎቹ አምስት አትሌቶች መካከል አንዷ እንድትሆን አላስቻላትም፡፡


### ማስታወቂያ

ኖፋኦ ኢንጅነሪንግ እምነበረድ አምራች ኃ/የተ/የግ/ማህበር በቤ/ጉ/ክ/መንግሥት መተከል ዞን ቡለን ወረዳ ማጣና እና ባጹሪ ቀበሌ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ የእምነበረድ ማእድን ምርመራ ለማካሄድ በቀን 27/2/2016 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ መ/ቤታችንን ጠይቀዋል፡፡ በመሆኑም በሚመለከተው የጂኦግራፊክ ኮኦርዲኔት ክልል፣

BLOCK 1

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. 36⁰ | 00' | 09.7''E | 10⁰ | 34' | 34.7'' | N |
| 2. 35⁰ | 59' | 57.1''E | 10⁰ | 34' | 47.8'' | N |
| 3. 35⁰ | 59' | 49.2''E | 10⁰ | 34' | 42.0'' | N |
| 4. 35⁰ | 00' | 0.01''E | 10⁰ | 34' | 30.2'' | N |

ውስጥ በሚገኘው ቦታዎች ላይ ይገባኛል የሚል ቢኖር ይህ ማስታወቂያ በወጣ በሰባት /7/ ተከታታይ ቀናት ውስጥ ተቃውሞውን ከነምክንያቱ ለቢሮአችን እንዲያቀርቡ እናሳስባለን፡፡

**የማዕድን ሀብት ልማት ቢሮ**

## አዲስ አበባ አስተዳደር

የባለንብረት ስም ኢስት ሴሜንት ኃላ/የተወ/የግል ማህበር የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-38609 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻንሲ ቁጥር LZ5N2DD346A005640 ሞዴል hn3509j የሞተር ቁጥር 6D24*385204* ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው በ27/2/2016 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካላቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን**
**የንፋስ ስልክ ላፍቶ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ማህሌት ሰይፉ ሰርቤሳ የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01- A24976 የተሽከርካሪው አይነት አውቶሞቢል የሻንሲ ቁጥር JTDKT923775035174 ሞዴል NCP1L-AHPRKK የሞተር ቁጥር 1NZ-4014787 የሊብሬ ቁጥር311833 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው በ23/2/2016 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካላቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን**
**የንፋስ ስልክ ላፍቶ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

በከሳሽ ቪዥን ፈንድ ማይክሮ ፋይናንስ አ.ማ እና በተከሳሽ እነ አቶ ሀይሉ ግርማ መካከል ስላለው የፍ/ብሔር ክስ ጉዳይ ተከሳሽ አቶ ሀይሉ ግርማ በደሳ በ10/03/2016ዓ.ም ለሆነው ቀጠሮ በ4፡50 ሰዓት የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ኮ/ቀ ምድብ 2ኛ ችሎት ልዩ ልዩ እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**

በከሳሽ/ሾች ቪዥን ፈንድ ማይክሮ ፋይናንስ አ.ማ እና በተከሳሽ/ሾች እነ አቶ ሀይሉ ግርማ መካከል ስላለው የፍ/ብሔር ክስ ጉዳይ ተከሳሽ/ሾች ወ/ሮ መሰረት በሀቁ ተመሚላ በ10/03/2016ዓ.ም ለሆነው ቀጠሮ በ4፡50 ሰዓት የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ኮ/ቀ ምድብ 2ኛ ችሎት ልዩ ልዩ እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**

በከሳሽ ቪዥን ፈንድ ማይክሮ ፋይናንስ አ.ማ እና በተከሳሽ እነ አቶ ሀይሉ ግርማ መካከል ስላለው የፍ/ብሔር ክስ ጉዳይ ተከሳሽ/ሾች አቶ እሱእንዳለ ሙሉጌታ ታደሰ በ10/03/2016ዓ.ም ለሆነው ቀጠሮ በ4፡50 ሰዓት የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ኮ/ቀ ምድብ 2ኛ ችሎት ልዩ ልዩ እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**

አመልካች ወ/ሮ ሰብለወንጌል ወርቁ እና ተጠሪ አቶ ሳሙኤል መስፍን መካከል ስላለው የቤተሰብ ክርክር ጉዳይ ፍ/ቤቱ በሰጠው ትዕዛዝ ተከሳሽ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ቂርቆስ ምድብ 1ኛ ቤተሰብ ችሎት እየታየ መሆኑን በዚህ ጋዜጣ ማስታወቂያ ጥሪ አውቀው መልሱን በጽሁፍ በኩል ለ10/03/2016 ዓ.ም 3፡30 ሰዓት እንዲያቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**